# ጥላና አካል

ጥንታውያንና ፍለጋቸውን የተከተሉ የዘመኑ ኦርቶዶክሳውያን
ሊቃውንት እንዳስተማሩት

በዲያቆን አግዛቸው ተፈራ

**መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው**
**All Rights Reserved**

**1995 ዓ.ም**

**የሽፋን ሥዕል**
**በወንድወሰን ገብረ ትንሣኤ**

**ስለ መጽሐፉ አስተያየትና ጥያቄ ቢኖርዎ ወይም ለማከፋፈል**
**ከፈለጉ በመ.ሣ.ቁ 56307 አ.አ ብለው ይጻፉልን**

## ማውጫ

ገጽ

መቅድም ........ 5
መግቢያ ........ 10
የገላውዴዎስ የሃይማኖት ውሳኔ ........ 13
የጥላና አካል ትርጉም ........ 17
**ክፍል 1 - የእግዚአብሔር ሕዝብ**
1.1 የእግዚአብሔር ሕዝብ በብሉይ ኪዳን ........ 20
1.2 የእግዚአብሔር ሕዝብ በዐዲስ ኪዳን ........ 23
1.3 የሁለቱ ሕዝቦች አንድነትና ልዩነት ........ 25
**ክፍል 2 - የእምነት ማኅተም**
2.1 የእምነት ማኅተም በብሉይ ኪዳን ........ 27
2.2 የእምነት ማኅተም በዐዲስ ኪዳን ........ 30
2.3 ከሥርዐትነት ያላለፈ ጥምቀት ........ 34
**ክፍል 3 - ቤዛ**
3.1 በብሉይ ኪዳን ለሕዝቡ የተከፈለ ቤዛ ........ 36
3.2 በዐዲስ ኪዳን ለሕዝቡ የተከፈለ ቤዛ........ 38
3.3 ከእግዚአብሔር ያልሆኑ ቤዛዎች ........ 41
**ክፍል 4 - ኪዳን**
4.1 ብሉይ ኪዳን ........ 47
4.2 ዐዲስ ኪዳን ........ 50
4.3 እግዚአብሔር ያልገባው ቃል ኪዳን ........ 53
**ክፍል 5 - ሕግ**
5.1 ሕግ በብሉይ ኪዳን ........ 58
5.2 ሕግ በዐዲስ ኪዳን ........ 60
5.3 የወንጌል አሪታውያን ........ 63
**ክፍል 6 - ታቦት**
6.1 ታቦት በብሉይ ኪዳን ........ 69
6.2 የዐዲስ ኪዳን ታቦት ........ 72
6.3 ጥላውንም አካሉንም የማይወክል ታቦት ........ 74
**ክፍል 7 - መካከለኛ**
7.1 የብሉይ ኪዳን መካከለኞች ........ 83
7.2 የዐዲስ ኪዳን መካከለኛ ........ 85
7.3 በሰዎች የቆሙ መካከለኞች ........ 88
**ክፍል 8 - የተቀደሰ ዘይት**
8.1 የተቀደሰ ዘይት በብሉይ ኪዳን ........ 92
8.2 ቅዱሱ ቅባት በዐዲስ ኪዳን ዘመን ........ 93
**ክፍል 9 - ቤተ መቅደስ**
9.1 ቤተ መቅደስና አገልግሎቱ በዘመነ ኦሪት ........ 97
9.2 የዐዲስ ኪዳን ቤተ መቅደስ ........ 101
9.3 ቤተ መቅደስና ሌሎች ኢየሩሳሌሞች በቤ/ክ ዘመን ........ 106
**ክፍል 10 - ካህናትና አገልግሎታቸው**
10.1 የካህናት አገልግሎት በብሉይ ኪዳን ........ 115
10.2 የሊቀ ካህናትና የካህናት አገልግሎት በዐዲስ ኪዳን ........ 117
10.3 ጊዜ ያለፈበትና ያልታዘዘ አገልግሎት ........ 120

**ክፍል 11 - መሥዋዕት**
11.1 መሥዋዕት በብሉይ ኪዳን ........................................ 125
11.2 መሥዋዕት በዐዲስ ኪዳን ........................................ 128
11.3 ሥጋሁ ወደሙ ........................................ 131
11.4 መንፈሳውያን መሥዋዕቶች ........................................ 136
**ክፍል 12 - ዕጣን**
12.1 ዕጣን በብሉይ ኪዳን ........................................ 138
12.2 ዕጣን በዐዲስ ኪዳን ዘመን ........................................ 140
**ክፍል 13 - የመንጻት ሥርዐት**
13.1 የመንጻት ሥርዐት በብሉይ ኪዳን ........................................ 144
13.2 የመንጻት ሥርዐት በዐዲስ ኪዳን ........................................ 145
**ክፍል 14 - በዓላት**
14.1 በዓላት በብሉይ ኪዳን ዘመን ........................................ 148
14.2 በዓላት በዐዲስ ኪዳን ........................................ 152
ማጠቃለያ ........................................ 156


# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን!

## መቅድም

«የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኦሪታዊት እንጂ ወንጌላዊት አይደለችም፤» የሚለው ትችት ከጥንት ጀምሮ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ሲሰነዘር መቈየቱና አሁንም ድረስ ያለ መሆኑ ይታወቃል።

በታሪክ ተመዝግቦ እንደሚገኘው፥ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ግራኝ መሐመድ የኢትዮጵያን ክርስቲያኖች ለመደምሰስ ታጥቆ በተነሣበት ወቅት፥ ጥቃቱን ለመከላከል ከፖርቱጋል ወታደሮች ጋር አብረው የመጡ የካቶሊክ ቀሳውስት፥ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ያቀረቡት ክስ በምሳሌነት ሊቀርብ ይችላል፤ (የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ታሪክ ከአባ ጎርጎርዮስ ገጽ 175-176)።

ክሱ ካቶሊካውያኑ ኢትዮጵያን የካቶሊክ ሀገረ ስብከት ለማድረግ ከነበራቸው ጽኑ ፍላጎት የተነሣ የቀረበ ነው የሚል አንድምታ እንዳለው በብዙዎች ዘንድ ይታመናል። ነገሩ እንደ ተባለው ከሆነ፥ በወቅቱ በካቶሊካውያኑ የተደረገውን የእኔ እበልጥ የሥልጣን ጥማት ማንነታችንን ማጣት የሌለብን ከመሆኑ አንጻር አንደግፈውም። ይህን አቋም ይዘንና አንድምታውን ለባለ ታሪኮች በመተው የክሱን መነሻ ነጥብ ከነባራዊው ሁኔታ ጋር ስናስተያየው ግን፥ ክሱ ከክስነቱ ሊሽፈንና ሊስተባበል የማይችል የአደባባይ ምስጢር ሆኖ እናገኘዋለን።

በወቅቱ ታዲያ ቤተ ክርስቲያናችንን በኦሪታዊነቷ ለተቿት ካቶሊካውያን፥ ንጉሡ የተከሰሰንባቸውና ያስተቹን ኦሪታዊ ነገሮች ሁሉ በሕዝቡ ዘንድ እንደ ባህል የሚታዩ እንጂ፥ እንደ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተደነገጉ አለመሆናቸውን የሚገልጽ የሃይማኖት ውሳኔ አረቀቁ። ይህም «የገላውዴዎስ የሃይማኖት ውሳኔ» በመባል ይታወቃል። ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ የሃይማኖት ውሳኔው በዚህ መጽሐፍ ላይ ከመግቢያው ቀጥሎ ቀርቧል።

ይሁን እንጂ ውሳኔው በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ አይታወቅም። ሊቃውንቱም ቢሆኑ ተመሳሳይ የሆነ ክስና ትችት ዛሬም ደግሞ ሲነሣ፥ እንዲያው ላለማፈርና አንገት ላለመድፋት ሲሉ ፈራ ተባ እያሉ ውስጥ ለውስጥ ይጠቅሱታል እንጂ፥ በግልጽ ዘርዝረውና አብራርተው አያስተምሩትም። በእርግጥ እናስተምራለን ቢሉም ውሳኔውን በሌላ ሁኔታ ራሳቸው አስቀድመው በመቃወም ስላስተማሩት ሕዝቡ አይቀበላቸውም፤ «መናፍቅ» ብሉም ያወግዛቸዋል።

ነበረ የሚባለውን የካቶሊካውያን ድብቅ ዐላማ፥ ወይም ደግሞ ተመሳሳይ ማንነትን የሚያሳጡ ዐላማዎችን በመደገፍ ባይሆንም፥ ክሱ ከውጭ ብቻ ሳይሆን ከውስጥ ከቤተ ክርስቲያን ልጆችም ይነሣል።

እኔን ጨምሮ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባላት ሆነው መጽሐፍ ቅዱስን ከሚያነቡ ብዙ ወገኖች እንደተረዳሁት፥ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እየተፈጸመ ያለው ኦሪታዊ ሥርዐት ብዙ ጊዜ

በዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ከምናነበው የእግዚአብሔር ቃል ጋር ይጋጭብናል:: ያለውን ኦሪታዊ ሥርዐት እንዳንቀበለው የእግዚአብሔር ቃል ይከለክለናል፤ እንዳንተወው ደግሞ ብዙ ከተነገረንና ከሰማነው አንጻር እንፈራለን:: ስለዚህ የብዙዎቻችን አእምሮ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያሳርፍ መልስ እስኪያገኝ ድረስ በፍርሃትና በጥያቄ እንደ ተወጠረ ይኖራል::

«ጥላና አካል» የተሰኘውን ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ የተነሣሁት፥ እኔ እንዲሁ በተነገረንና በሰማነው ብቻ መፍራትን ወደ ጎን በመተውና የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን አምኖ ለመቀበል በመዘጋጀት ምላሽ እንዳገኘሁ ሁሉ፥ ሌሎችም እንደ እኔ አእምሯቸው በጥያቄ የተወጠረ ወገኖቼ ቢኖሩ ምላሽ በማግኘት አእምሯቸው እንዲያርፍ በመርዳት የተቻለኝን ለማድረግ ነው::

ያለውንና የተረዳሁትን፥ ከአባቶቼም የተማርኩትን ሳልሸሽግ በዚህ ሁኔታ ለመጻፍ ሁኔታዎች ቢያስገድዱኝም፥ ዐላማዬ ቤተ ክርስቲያኔን በሌሎች ዘንድ ለመክሰስና ለማሳጣት አለመሆኑን አንባቢው በቅንነት እንዲረዳልኝ አሳስባለሁ:: የጻፍኩበት ዋና ዐላማም ቤተ ክርስቲያናችን በምን ሁኔታ ላይ እንደምትገኝ፥ በተለይ ለራሷ ለቤተ ክርስቲያን ማሳየትና ከዘላለማዊ ክስና ትችት የምትድንበትን መንገድ መጠቈም ነው::

መቼም እዚህ ላይ «ስንት ሊቃውንት አባቶች እያሉ፥ እነርሱ ካሁን ቀደም ያልተናገሩትንና ያላስተማሩትን እጽፋለሁ የምትል አንተ ማነህ? ወይም ደግሞ አጉል መመራመር ነው ወደዚህ የሚያደርሰው» የሚል ትችት ሊሠነዘርብኝ እንደሚችል ከወዲሁ ዐውቃለሁ::

ያልተገለጸውንና እግዚአብሔር ምስጢር ያደረገውን ነገር ተመራምሬ እደርስበታለሁ ብሎ ማሰብ ታላቅ ትዕቢት ነው:: በዚህ አቅጣጫ የተሰወረውን ለመግለጥ የሚደረገው ጥረትም ፍሬ የሌለው ከንቱ ድካም እንደሆነ ይታወቃል:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔርን ማወቅና መከተል እንዲሁ በጭፍን፥ ወይም በስማ በለው፥ አሊያም ደግሞ አንዳንድ አላዋቂዎች «እምነት በየዋህነት ነው» እንደሚሉት ሳይሆን፥ በቃሉ ውስጥ የተጻፈው በማወቅና እንደተጻፈውም በመኖር ነው:: በቃሉ ውስጥ የተጻፈውን አምኖ ለመቀበል በእርግጥ የዋህ መሆን ያስፈልጋል፤ያዕ. 1÷21::

ስለሆነም ይህን የእግዚአብሔር ፈቃድ ከቅዱስ ቃሉ አንብበንና ተምረን ለማወቅ የምናደርገው ጥረት ከአጉል መመራመር ሊቈጠርብን አይገባም:: ቅዱስ ቃሉ «ወኵሎ አመክሩ፤ ወዘሠናየ አጽንዑ::» «ሁሉን ፈትኑ፤ መልካሙንም ያዙ::» ይላልና፤ (1ተሰ. 5÷21):: ከዚህ ውጪ የሚያስቡ ቢኖሩ፥ ማስተዋል የሚጎድላቸውና ለሚጠየቁት ጥያቄ እንኳ መልስ የሌላቸው እንደሆኑ ግልጽ ነው::

በመሠረቱ እኔ ስለ ሃይማኖት በቅርበት በእግራቸው ሥር አስቀምጠውም ሆነ፥ በርቀት ሆነው በመጻሕፍቶቻቸው አማካይነት ያስተማሩኝን ኦርቶዶክሳውያን አባቶቼን በእጅጉ አከብራለሁ:: ይሁንና በቅርብም በሩቅም ያስተማሩኝን አባቶች ለክርስቶስ ወንጌል ካላቸው አመለካከት አንጻር በሦስት ጎራ መድቦ ለመመልከት ይቻላል::



በመጀመሪያው ጎራ የሚመደቡት አባቶች በመጻሕፍት ዕውቀትና በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ምንም የበረቱ ቢሆኑ፥ እውነትና ሐሰትን፥ ፍሬና ገለባን አደበላልቀው የያዙ ሆነው እናገኛቸዋለን:: ከእውነት እኩል ጊዜ የወለዳቸውን የሐሰት ትምህርቶችንም ስለያዙ፥ እነርሱን ላለማጣት ሲሉ ሳያውቁት በሌላ በኩል የያዙትን እውነት ተቃውመውት ይገኛሉ:: እነዚህ አባቶች ታዲያ ብዙ አድማጭና ተከታይ አላቸው::

በሁለተኛው ጎራ የሚመደቡት አባቶች ደግሞ፥ እንደ መጀመሪያዎቹ አባቶች በዕውቀት የበረቱና ምስጢር ያደላደሉ በመሆናቸው ላይ እውነትን ከሐሰት፥ ፍሬውን ከገለባ ለይተው የተረዱ ናቸው:: ከመጀመሪያዎቹ የሚለዩበት ይህ በጎ ነገር ቢኖራቸውም፥ በኀይል ሚዛን አሰላለፍ ከመጀመሪያዎቹ ያነሱ ናቸው:: ስለሆነም ከእነርሱ አካባቢ ሊነሣባቸው የሚችለውን ተቃውሞና ስደት በመፍራት፥ እንዲሁም እውነተኞች ሲሆኑ አሳቾች፥ ትክክለኛ የእምነት ሰዎች ሆነው ሳለ መናፍቃን ተብለው ላለመወገዝ ሲሉ፥ ስለ እውነት ከመመስከር ይልቅ ዝምታንና ተመሳስሎ መኖርን ይመርጣሉ:: እንዲያው በጥቅሉ እኒህ አባቶች፥ በክርስቶስ የማስተማር ዘመን አምነው እንደነበሩት፥ በኋላ ላይ ግን ከምኵራብ እንዳያስወጧቸው በፈሪሳውያን ምክንያት ለጌታ ሳይመሰክሩለት እንደቀሩት አለቆች ዐይነት ናቸው ለማለት ይቻላል፤ (ዮሐ. 12÷42-43)::

በሦስተኛ ጎራ የተመደቡት አባቶች ደግሞ በብዙው ሁኔታ በሁለተኛው ጎራ ከሚመደቡት አባቶች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው:: ከእነርሱ የሚለያቸው አንድ መሠረታዊ ነጥብ አለ:: ይኸውም እንደ እነርሱ እንሰደዳለን፥ እንወገዛለን ሳይሉ ያመኑትን እውነት ገልጠው በድፍረት መናገር መቻላቸው ነው:: በግብራቸውም «የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት እንደ ብዙዎቹ አይደለንምና፤ በቅንነት ግን ከእግዚአብሔር እንደተላክን በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ሆነን እንናገራለን::» (1ቆሮ. 2÷17) ያለውን ሐዋርያ ብፁዕ ጳውሎስን መስለውታል::

ከእነዚህ አባቶች መካከል ለአብነት ያህል የሚጠቀሱት ጥቂቶቹ: - በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የነበረውና በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያልተመሠረተውን የዐፄውን የፈጠራ ትምህርት ፊት ለፊት በመቃወም፥ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከገባችበት የስሕተት ትምህርት እንድትወጣ እስከ ሞት ድረስ የተጋደለው አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቹ፥ ታላቁ ሊቅ አለቃ ታየ፥ የተከበሩ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፥ እንዲሁም አቶ ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ፥ ታላቁ ሊቅ አለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ ናቸው::

እነዚህ አባቶች በነፍሳቸው ተወራርደው መጻሕፍትን በመጻፍ፥ እውነትና ሐሰትን እንድንለይ የረዱን የተመሰገኑ አባቶቻችን ናቸው::

የእውነት ተቃዋሚዎች ግን በየዐውደ ምሕረቱ፥ መናፍቃን ናቸው፤ መጻሕፍቶቻቸውን እንዳታነቡ፤ በደረሱበትም እንዳትደርሱ፤

ሰላም እንዳትሏቸው፣ ወዘተ... እያሉ በመለፈፋቸው ምክንያት፥ ሊያደምጧቸው የሚገባቸው ሰዎች ጆሮዎቻቸውን ነፈጓቸው፡፡ የእነዚህን አባቶች መጻሕፍት ብናነብ ግን፥ እኛ ዘወትር የምንነቀፍበት ትምህርት ትክክለኛና ደጋጎቹ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ያስተማሩት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

ታዲያ «ጠላት ይቀባል ጥላት» እንዲሉ እኒህ አባቶች «መናፍቅ»፥ «ከሐዲ»፥ «ጸረ ማርያም» ወዘተ... እየተባሉና አለስማቸው ስም እየተሰጣቸው ስደት ታወጀባቸው፣ ታሰሩ፣ ተገረፉ፣ እስከ ሞት ድረስም ተደበደቡ፣ በአሰቃቂ ሁኔታም ተገደሉ፡፡ ቢሆንም ለነፍሳቸው ሳይሳሱ ዛሬም ድረስ ተከታይ ልጆቻቸውን «መናፍቅ» እያሰኘ ከቤተ ክርስቲያን ስደት የሚያሳውጅባቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት አስተምረው ዐልፈዋል፡፡ እኛም ከእነዚሁ አባቶች በትምህርት የተወለድን ልጆቻቸው ነን፡፡ ዘወትር እንደ ጠላት የምንቈጠርበትን ትምህርት ያገኘነውም ከእነርሱ ነው እንጂ ከሌላ ከየትም አላመጣነውም፡፡

ከአባቶቻችን መካከል ስማቸውን ያነሣነው የጥቂቶቹን፥ ያውም በክብር ያለፉትን ብቻ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በብዙዎች ዘንድ ያልታወቁ ቢሆኑም፥ በተመሳሳይ ዐላማ ቤተ ክርስቲያናችን ያሉባትን ስሕተቶች አስተካክላ ወደ ቀደመው እውነተኛ መሠረቷ እንድትመለስ፥ የተጋደሉ ብዙ አባቶች ማለፋቸውና አሁንም በተጋድሎ ላይ የሚገኙ መኖራቸው ይታወቃል፡፡

በጥቅሉ በመጀመሪያው ጎራ የሚመደቡት አባቶች ካለማስተዋል የተነሣ ቢቃወሙትም፥ ሁለተኛዎቹ ደግሞ ከመፍራታቸው የተነሣ ደፍረው ሙሉ በሙሉ ባይመሰክሩትም፥ እኒህ አባቶች ግን ይህን እውነተኛ ትምህርት አስተምረውን እንዳለፉና ዛሬም በመጻሕፍቶቻቸው አማካይነት እያስተማሩን እንደሆነ ፈጽሞ ሊዘነጋ አይገባም፡፡

የአንድን ነገር ምንነት ሳያጣሩና ሳይመረምሩ እንዲያው ደርሶ መንቀፍ፥ ራስን አላዋቂ ከማድረግ ያለፈ ነገር የለውም፡፡ ሰው ደግሞ ክፉና ደጉን መለየት የሚችልበት አእምሮ ስለተሰጠው፥ ነገሮችን ሁሉ በኅሊናው ዳኝነት አመዛዝኖና በእግዚአብሔር ቃል አረጋግጦ እውነቱን ከሐሰት፥ የከበረውን ከተዋረደው ሊለይ ይገባዋል፣ (ኤር. 15፥19-21)፡፡

መቼም አእምሮ ያለው ሰው፥ እግዚአብሔር እንድናውቀው በቃሉ በኩል የገለጠልንንና አባቶቻችንም ያስተማሩንን እውነተኛ ትምህርት ለማወቅ ያለንን መሻት፥ እንደ አጉል ምርምር ይቈጥረዋል ብለን እናምንም፡፡ ምክንያቱም ክፉው ነገር፥ እንድናውቀው የተፈቀደልንን መርምሮ ማወቁ ሳይሆን «መመራመር መጥፎ ነው» በሚለው የአላዋቆች ተረት ታስሮ የእግዚአብሔርን እውነት ሳያውቁ መቅረቱ ነውና፡፡

ስለዚህ ይህን እውነት አባቶች ተቀምጠው እኛ ልጆቹ ድንገት በስሜት ተነሣሥተን ነገር ለማበለሻሸት መናገር እንደ ጀመርን ተደርጎ መታየት የለበትም፡፡ ሊከተልባቸው የሚችለውን ችግር ከመፍራት የተነሣ ዝምታን የመረጡ አባቶች ዝም ቢሉም፥ ተስፋቸውን በሚታየው በዚህ ዓለም ላይ ያላደረጉና የእውነተኞቹ ነቢያት፥ የጌታ ክርስቶስና የሐዋርያት



የተጋድሎ ታሪክ፥ ታሪክ ብቻ ያልሆነባቸው አበው ግን፥ እውነቱን ተናገረውና ስለ እውነት መከራን ተቀብለው ዐልፈዋል፡፡ ዛሬም በዚሁ የተጋድሎ መሥመር ውስጥ የገቡ ሁሉ ተመሳሳይ ዕጣ እየደረሰባቸው ይገኛል፣ (1ተሰ. 2፥15፣ ማቴ. 23፥29-32፣ የሐዋ. ሥራ 7፥52)፡፡ በዚህ አጋጣሚ እውነቱን እያወቃችሁ ዝምታን የመረጣችሁ አባቶችና ወንድሞች ባለዕዳ ናችሁና (ሮሜ 1፥14፣ 1ቆሮ. 9፥16)፥ ሕዝባችን የጠራውን የመዳን መንገድ እንዲያስተውል በጥበብና በማስተዋል ትረዱት ዘንድ ዛሬ ተነሡ እንላለን፡፡

ወንጌል ይኸው ነው፣ የሚሰበከውም በመከራና በስደት እንጂ ተቀባይነትን በማግኘት ብቻ አይደለም፡፡ ምናልባት ለተወሰነ ጊዜ ሰው ሊቀበለንና ሊደግፈን ይችላል፣ ዘላቂነት ግን የለውም፡፡ «በወንጌል እንደምሰብከው ከሙታን የተነሣውን፥ ከዳዊት ዘርም የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ዐስብ፣ ይህንም በመስበክ እንደ ክፉ አድራጊ እስከታሰር ድረስ መከራ እቀበላለሁ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ግን አይታሰርም፡፡ ስለዚህ እነርሱ ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን መዳን ከዘላለም ክብር ጋር እንዲያገኙ በነገር ሁሉ እጸናለሁ፡፡» (2ጢሞ. 2፥8-10)፡፡

ጥላና አካልም ይህንኑ የአባቶች ዱካ በመከተል በኅሊና ዳኝነትና በእግዚአብሔር ቃል ሚዛንነት እውነት የሆነውን ከሐሰት ለሚለዩና ለሚከተሉ ሁሉ ቀርቧል፡፡

## መግቢያ

በብዙ የዓለማችን ሕዝቦች ዘንድ ስም ያለ ምክንያት አይወጣም:: ከሚከሠቱ ነገሮች በመነሣት÷ ወይም ደግሞ ባለስሙ ባለው አካላዊ አቋምና የተለየ ባሕርይ መነሻነት÷ አሊያም አንድን ያለፈ ነገር በትዝታ ለማስታወስ ታስቦ÷ ወይም ወደፊት ተስፋ በሚደረግ ነገር ለመጽናናትሲባልና በመሰል ምክንያቶች ስም ይወጣል::

ለመጻሕፍት የሚሰጣቸውን ስም የተመለከትን እንደሆነም ምክንያታዊና ትርጕም ሰጭ መሆን ይኖርበታል:: መጻሕፍትን የማንበብ ልምድ ያላቸው ሰዎች ወደ መጽሐፉ ውስጠኛ ክፍል ገና ሳይገቡ÷ ስሙን ብቻ በማንበብ መጽሐፉ ምን ዐይነት መልእክት ለማስተላለፍ እንደ ተጻፈ በቀላሉ ለመረዳት ይችላሉ፤ «እስመ ስሙ ይመርሖ ኀበ ግብሩ» እንዲል::

ለዚህ መጽሐፍ «ጥላና አካል» የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል:: መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩት ኦሪታዊ ነገሮች በሙሉ÷ ይመጣ ዘንድ ላለው ለዐዲስ ኪዳን «ጥላ» እንደነበሩ ሲናገር÷ በዐዲስ ኪዳን በተስፋ ሲጠበቅ የነበረው ክርስቶስና ወንጌሉ ደግሞ «አካል» መሆናቸውን ይመሰክራል፤ (ቈላ. 2÷17፤ ዕብ. 10÷1)::

በዚሁ መሠረት እንግዲህ ኦሪትና ወንጌል ጥላና አካል ሆነው በሁለቱ ዘመናት ለነበረው የእግዚአብሔር ሕዝብ÷ በተለያየ ዘመን÷ በተለያየ ሁኔታና በተለያየ የአፈጻጸም ሥርዐት የተሰጡ መሆኑን ስለሚገልጽ÷ እንደገናም አንዱ ለሌላው ወይም ኦሪት ለወንጌል ጥላና ምሳሌ ሆኖ ከማገልገል በቀር÷ አንዱ በሌላው ጣልቃ እንደማይገባና ሁለቱም በየራሳቸው ዘመን እንዲያገለግሉ በእግዚአብሔር የተወሰኑ መሆኑን ስለሚያብራራ «ጥላና አካል» ተሰኝቷል::

መጽሐፉን መጻፍ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት÷ ከላይ እንደተገለጸው ኦሪትና ወንጌል በየራሳቸው ዘመን እንዲያገለግሉ በተሰጡበት ሁኔታ ማገልገል ሲገባቸው÷ አንዱ በሌላው (ኦሪት በወንጌል) ጣልቃ ገብቶ ስለሚታይ÷ በተለይም ኦሪት በጥላና በምሳሌነቷ አካልና አማናዊት የሆነችው ወንጌል በመጣች ጊዜ ስፍራዋን ለወንጌል መልቀቅ ሲገባት÷ በተቃራኒው ግን ወንጌልን ሸፍና በመገኘቷ÷ ይህን እውነት አሁን ያለውና መጪውም ትውልድ ተገንዝቦ÷ ከኦሪት ወደ ወንጌል ሙሉ በሙሉ ዘወር እንዲል ለማድረግ ሲባል ነው::

ኦሪት ለወንጌል ስፍራዋን ሙሉ በሙሉ ሳትለቅ ከወንጌል ጋር ተደበላልቃ÷ ዛሬም ያለ ምንም ጥቅም በከንቱ ደክማ እያደከመች ከምትገኝባቸው ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ አንዷ ናት::

በመሠረቱ እግዚአብሔር ኦሪትና ወንጌልን በአንድ ዘመን÷ በአንድ ላይ እንዲያገለግሉ አልሰጠም:: በአንድ ላይ ሊሄዱም አይችሉም:: አስቀድሞ ጥላና ምሳሌው÷ በኋላም አካሉና አማናዊው ነገር ይሆኑ ዘንድ በእግዚአብሔር የታቀደ ነው:: የተፈጸመውም በዚሁ ቅደም ተከተል መሠረት ነው::



ቤተ ክርስቲያን አስቀድሞ በጥላው ዘመን ያልነበረችና በአካሉ ዘመን የተመሠረተች እንደ መሆኗ÷ የአካሉ የሆኑትን ነገሮች ብቻ ይዛ መገኘት ተገቢዋ ነው:: እንደዚህች ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ማየት ቢያስፈልግ የሐዋርያትን ሥራ ማንበቡ ብቻ በቂ ነው:: በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የምናገኛት የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን÷ የወንጌልን አገልግሎት ከማገልገል በቀር አንድም የኦሪትን ተግባር ስትፈጽም አናያትም:: ይልቁንም ኦሪት በወንጌል መፈጸሟን በማወጅ አይሁድ ሁሉ ከኦሪት ወደ ወንጌል ዘወር ይሉ ዘንድ ታስተምር ነበር:: ከሐዋርያት የተላለፈልንና ልንቀበለው የሚገባ መጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነትና ትውፊት ይኸው ብቻ ነው::

ቤተ ክርስቲያናችን ግን ከዚህ ውጪ በመሆን ጥላውንም አካሉንም በአንድነት ይዛለች፤ ትኩረቷን ይበልጥ እየሳበ ያለውም ጥላና ምሳሌው ነው:: በጥላና ምሳሌው ላይ ተመሥርታ ከምትፈጽማቸው አያሌ ሥርዐቶች ባሻገር ባለው መንፈሳዊ ነገር ላይ ከማተኮር ይልቅ÷ ሥርዐት በመፈጸም ላይ ብቻ ማነጣጠሯ ለዚህ በቂ ምስክር ሊሆን ይችላል::

በእርግጥ በክርስትና ታሪክ እንደዚህ ባለው ቅይጥ ሕይወት ውስጥ በማለፍ÷ የኛዋ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያዋ አይደለችም:: ክርስትና በተሰበከባቸው በመጀመሪያዎቹ ክፍለ ዘመናት በነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥም÷ ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ተከሥቶ ያለው ኦሪታዊነት እንደ ገና ማንሰራራት ጀምሮ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል:: ለዚህም የዕብራውያን ክርስቲያኖችን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል::

ዕብራውያን በዘመነ ኦሪት ልጅነትና ክብር÷ ኪዳንና ሕግ÷ ተስፋም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣቸው÷ የመቅደስ ሥርዐት የነበራቸው የዕብራዊው አብርሃም ዘሮች ናቸው፤ (ሮሜ 9÷4-5፤ ዘፍ. 14÷13)::

በእነርሱ ዘንድ በተስፋ ሲጠበቅ የቆየው መሲሕ ሲመጣ አምነውበት ክርስቲያን ሆኑ:: ይሁን እንጂ በኋላ ላይ በተለያዩ ምክንያቶች÷ በወንጌል ፍጻሜን ወዳገኘችው ወደ ኦሪት ሥርዐት ፊታቸውን ለመመለስ በመፈለግ ብዙዎቹ ከወንጌል ወደ ኋላ አፈገፈጉ:: ስለዚህ ይህ አድራጎታቸው ትክክል አለመሆኑን ለማስገንዘብ ሲባል መልእክቱ ይጻፍላቸው ዘንድ ተገባ::

በዕብራውያን መልእክት ውስጥ እንደ ተገለጸው÷ በኦሪት ዘመን የነበረው አገልግሎትና አገልጋዮቹ÷ ቤተ መቅደሱና በውስጡ የነበሩት ንዋያተ ቅድሳት÷ መሥዋዕቶቹና ሥርዐቶቹ ሁሉ በአጠቃላይ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ ለእርሱ ጥላና ምሳሌ በመሆን በጊዜያዊነት እንዲያገለግሉ የተሰጡ ነበሩ:: በክርስቶስ መምጣትና እርሱ ለኦሪት ፍጻሜን ሰጥቶ ዐዲስ በመሠረተው መንፈሳዊና ሉዓላዊ የወንጌል አገልግሎት ምክንያት ግን ዛሬ የማይጠቅሙ ሆነዋል::

የዕብራውያን መልእክት የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ÷ መልእክቱ በዘመናት ሁሉ ክርስቲያኖችን በመገሠጽና በማስተማር እንደሚያገለግል እሙን ነው፤ የተጻፈው ሁሉ እኛ ልንመክርበት ጭምር ተጽፏልና፤ (ሮሜ 15÷4)::

ቤተ ክርስቲያናችን መልእክቱን ዘወትር እንደምታነበው ሁሉ ብታስተውለው÷ የዕብራውያን መልእክት ለእርስዋ የጊዜው ዋና መልእክት ነው ለማለት ይቻላል:: ምክንያቱም የመልእክቱ ጭብጥ ኦሪት÷ ለኦሪት ሁለተኛዋ አገር ነኝ ለምትለዋ ይቅርና ለዋናዋ ለእስራኤልም በዐዲስ ኪዳን ዘመን የማትጠቅም መሆኗን አመልካች ነው::

እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባን÷ ኦሪት ለወንጌል ጥላ በመሆኗ ዛሬ ስፍራዋን ለወንጌል ለቃለች ሲባል÷ በውስጧ ሲፈጸም የኖረው ኦሪታዊ ሥርዐት ሁሉ በወንጌል ተተክቷል ማለት ነው:: ሆኖም ይህ የኦሪት መጻሕፍት ወይም በጥቅሉ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተሽረዋል፤ ዛሬ እንደ እግዚአብሔር ቃል አያገለግሉም፤ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል::

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዘመን የማይሽራቸው የእግዚአብሔር ቃላት ናቸው:: ሰው እነርሱን በማንበብ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ እንደሚያገኝ÷ ከዚያም በክርስትና ጉዞው ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ እንዲሆን በማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መስክረዋል፤ (2ጢሞ. 3÷15-17፤ የሐዋ. ሥራ 8÷28-38፤ 17÷11)::

በዚህ በጥላና አካል መጽሐፍ ውስጥ በኦሪት ሕግ ተሰጥተው የነበሩ ዋና ዋና ጥላ ነገሮች÷ በዐዲስ ኪዳን ከሚያመለክቱት አማናዊ ነገር ጋር በየአርእስቱ ተነጻጽረው ቀርበዋል:: በየአርእስቱ ለቀረቡት ማብራሪያ ሐሳቦችም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች ከመቅረባቸው በተጨማሪ÷ ኦርቶዶክሳውያን አባቶች በጽሑፍ ካስተላለፉት እውነተኛ ትምህርትም በማስረጃነት ተጠቅሷል::

አንዳንዶቹ አርእስቶች በአንድም በሌላም መንገድ ተያያዥነት ስላላቸው÷ በአንድ ርእስ ሥር ተነሥቶ የነበረው ሐሳብ ምናልባት በሌላውም ርእስ ተነሥቶ ልናገኘው እንችላለን:: ይህም ነገሮችን በመደጋገም አንባቢን ለማሰልቸት ሳይሆን÷ እያንዳንዱን ርእስ ጉዳይ ለማብራራት ሲባል በሁኔታዎች አስገዳጅነት የሆነ ነው::

ካሁን በፊት ባሳተምኩት መጽሐፍ («የተቀበረ መክሊት») ውስጥ ተካተው የነበሩ አንዳንድ ነገሮች በዚህ መጽሐፍ ውስጥም ዳግም ተነሥተዋል:: ለዚህም ዋናው ምክንያት በመጠኑ ተነካክቶ የነበረውንና ተበታትኖ ያለውን ሐሳብ በአንድ ዋና ሐሳብና በአንድ መጽሐፍ ውስጥ አጠቃልሎ ማቅረቡ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ ስለታመነበት ነው:: ይሁን እንጂ በድጋሚ ሲቀርብ አስቀድሞ በቀረበበት ሁኔታ ሳይሆን ተሻሽሎና ብዙ ዐዳዲስ ሐሳቦችና ማስረጃዎች ታክለውበት ነው::

መጽሐፉ ኦሪትና ወንጌልን አደበላልቀው ለያዙና በአጠቃላይም ለሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ በረከት እንዲሆን እመኛለሁ::

ዲያቆን አግዛቸው ተፈራ



# የገላውዴዎስ የሃይማኖት ውሳኔ
## በግእዝ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ ዝንቱ ውእቱ ሃይማኖትየ÷ ወሃይማኖተ አበውየ ነገሥት እስራኤላውያን÷ ወሃይማኖተ መርዔትየ እለ ሀለዉ በዐጸደ መንግሥትየ::

ንሕነ ነአምን በአሐዱ አምላክ÷ ወበወልዱ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ÷ ውእቱ ቃሉ÷ ወውእቱ ኃይሉ÷ ውእቱ ምክሩ÷ ወውእቱ ጥበቡ:: ዘሀለወ ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም፤ ወበደኃሪ መዋዕል መጽአ ኀቤነ እንዘ ኢየዐርቅ እመንበረ መለኮቱ:: ወተሰብአ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል:: ወተጠምቀ በዮርዳኖስ በ፴ ክረምት ወኮነ ብእሴ ፍጹመ:: ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል በመዋዕለ ጲላጦስ ጰንጤናዊ:: ሐመ÷ ወሞተ÷ ወተቀብረ÷ ወተንሥአ በሣልስት ዕለት:: ወእምዝ በ፵ ዕለት ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት፤ ወነበረ በየማነ አቡሁ:: ወካዕበ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ÷ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ::

ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ÷ እግዚእ ማሕየዊ÷ ዘሠረጸ እምአብ:: ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለስርየተ ኀጢአት:: ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን÷ ለሕይወት ዘይመጽእ ለዓለም፤ አሜን::

ንሕነሰ ነሐውር በፍኖተ ንጉሥ ጽዱሕ አማናዊ:: ወኢናጸንን ኢለየማን ወኢለፀጋም እምትምህርተ አበዊነ:: ዐሠርቱ ወክልኤቱ ሐዋርያት÷ ወጳውሎስ ፈልፈለ ጥበብ÷ ወሰብዓ ክልኤቱ አርድዕት÷ ወሠለስቱ ምዕት ዐሠርቱ ወሰመንቱ ርቱዓነ ሃይማኖት ዘተጋብኡ በኒቅያ÷ ወምዕት ወኀምሳ በቍስጥንጥንያ÷ ወክልኤቱ ምዕት በኤፌሶን::

ከመዝ እሰብክ÷ ወከመዝ እሜህር አነ ገላውዴዎስ ንጉሥ ዘኢትዮጵያ÷ ወስመ መንግሥትየ አጽናፍ ሰገድ ወልደ ወናግ ሰገድ ወልደ ናዖድ::

ወበእንተ ምክንያተ አክብሮትነ ዕለተ ቀዳሚት ሰንበት÷ አኮ ዘናከብራ ከመአይሁድ እለሰቀልዎ ለክርስቶስ÷ እንዘ ይብሉ ደሙ ላዕሌነ ወላዕለ ውሉድነ:: እስመ እሙንቱስ አይሁድ ኢይቀድሑ ማየ÷ ወኢያነድዱ እሳተ÷ ወኢያበስሉ ጸብሐ÷ ወኢየኀብዙ ኅብስተ÷ ወኢይትፋለሱ እምቤት ውስተ ቤት::

ወባሕቱ ንሕነሰ ናከብራ እንዘ ናዐርግ ባቲ ቍርባነ÷ ወንገብር ባቲ ምሳሐ÷ በከመ አዘዙነ አበዊነ ሐዋርያት በዲድስቅልያ:: አኮ ዘናከብራ ከመ ሰንበተ እሑድ÷ እንተ ይእቲ ዕለት ሐዳስ፤ ዘይቤ ዳዊት በእንቲአሃ÷ «ዛቲ ዕለት እንተገብረ እግዚአብሔር፤ ንትፈሣሕ ወንትሐሠይ ባቲ::» እስመ ባቲ ተንሥአ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ:: ወባቲ ወረደ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ሐዋርያት በጽርሐ ጽዮን:: ወባቲ

ተሰብአ ውስተ ከርሠ ቅድስት ማርያም ድንግል በኵሉ ጊዜ፡፡ ወባተ ይመጽእ ዳግመ ለዕሴተ ጻድቃን÷ ወለፍዳ ኀጥአን፡፡

ወበእንተ ሥርዐተ ግዝረትኒ አኮ ዘንትገዘር ከመአይሁድ፡፡ እስመ ንሕነ ናአምር ቃለ ምህሮሁ ለጳውሎስ ፈልፈለ ጥበብ ዘይቤ «ተገዝሮሂ ኢይበቍዕ፤ ወኢተገዝሮሂ ኢያሰልጥ፤ ዘእንበለ ዳዕሙ ሐዳስ ፍጥረት÷ ዝ ውእቱ አሚን በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡» ወካዕበ ይቤ ለሰብአ ቆሮንቶስ «ዘሂ ነሥአ ግዝረተ÷ ኢይንሣእ ቍልፈተ፡፡»፡፡ ኵሉ መጽሐፈ ትምህርቱ ለጳውሎስ ሀለወ በኀቤነ፤ ወይሜህረነ በእንተ ግዝረት ወበእንተ ቍልፈት፡፡ ወባሕቱ ግዝረትሰ ዘኮነ በኀቤነ በልማደ ሀገር ከመ ብጥሐተ ገጽ ዘኢትዮጵያ ወኖባ÷ ወከመስቍረተ ዕዝን ዘሰብአ ሕንድ፡፡ ዘንተሰ ዘንገብር አኮ በዐቂበ ሕገገ ኦሪት÷ ዳዕሙ በልማደ ሰብእ፡፡

ወበእንተ በሊዐ ሐራውያኒ አኮ ዘንትከላእ በዐቂበ ሕገገ ኦሪት ከመ አይሁድ፡፡ ለዘኒ በልዐ ኢናስቄርሮ÷ ወኢናረኵሶ፤ ወለዘኒ ኢበልዐ ከመ ይብላዕ ኢናጌብሮ፡፡ በከመጻሐፈ አቡነ ጳውሎስ ለብሔረ ሮሜ እንዘ ይብል «ዘኒ በልዐ ኢይመንኖ ለዘኢይበልዕ፤ ወለኵሎሙ እግዚአብሔር ተወክፎሙ፡፡ መንግሥተ እግዚአብሔርሰ ኢኮነት በመብልዕ ወበመስቴ፡፡ ኵሉ ንጹሕ ለንጹሓን፤ ወለእኩይሰ ለሰብእ በሊዐ ምስለ ዕቅፍት፡፡» ወማቴምስ ወንጌላዊ ይቤ «አልቦ ዘይክል አርኵሶቶ ለሰብእ ዘእንበለ ዘይወጽእ እም አፉሁ፡፡ ወዘሰ ውስተ ከርሥ ይበውእ፤ ወይትገመር ጽመ፤ ወይትገደፍ፤ ወይትከዐው፡፡ ወያነጽሕ ኵሎ መባልዕተ፡፡» ወብሂለ ዝንቱ ቃሉ ነሠተ ኵሎ ሕንጻ ስሕተቶሙ ለአይሁድ እለተምህሩ እመጽሐፈ ኦሪት፡፡

ሊተሰ ሃይማኖትየ÷ ወሃይማኖተ ካህናት ማእምራን እለይሜህሩ በትእዛዝየ በዐጸደ መንግሥትየ፡፡ ወኢይትገሐሡ እምፍኖተ ወንጌል÷ ወእምትምህርተ አቡነ ጳውሎስ ኢለየማነ ወኢለፀጋም፡፡

ወበመጽሐፈ ታሪክኒ ጽሑፍ ሀሎ በመጽሐፈ ዚአነ÷ እስመ ቈስጠንጢኖስ ንጉሥ አዘዘ በመዋዕለ መንግሥቱ ለኵሎሙ እለተጠምቁ አይሁድ ከመ ያብልዕዎሙ ሥጋ ሐራውያ በዕለተ ትንሣኤሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡

ወባሕቱ በከመ አደሞ ልቡ ለሰብእ ይትሔረም እምበሊዐ ሥጋ እንስሳ፡፡ ቦ ዘያፈቅር ሥጋ ዓሣ÷ ወቦ ዘያፈቅር በሊዐ ሥጋ ዶርሆ÷ ወቦ ዘይትሔረም እምበሊዐ ሥጋ በግዕ÷ ወኵሉ ዘከመ አደሞ ልቡ ይተሉ÷ ከመዝ ውእቱ ሥምረቱ ወፈቃዱ ለሰብእ፡፡ በእንተ መብልዐ ሥጋ እንስሳ አልቦ ሕግ÷ ወአልቦ ቀኖና ውስተ መጽሐፍ ሐዳስ፡፡ ኵሉ ንጹሕ ለንጹሓን፡፡ ወጳውሎስኒ ይቤ «ዘሰ የአምን ኵሎ ለይብላዕ፤»፡፡

ዘንተ ኵሎ ጽሕቀ ለጽሒፍ ከመ ታእምር ጽድቀ ሃይማኖትየ፡፡ ተጽሕፈ በዐሠርቱ ወኀምስቱ ምዕት በኀምሳ ወኀምስቱ ዓመት እም ልደተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ አመ እስራ ወሠሉሱ ለሠኔ በሀገረ ዳሞት፡፡



## በአማርኛ

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድ አምላክ፤ ሃይማኖቴና የእስራኤላውያን ነገሥታት ሃይማኖት÷ በመንግሥቴም (በረት) ግዛት ውስጥ የሚገኙ ምእመናን (የመንጋዬ) ሃይማኖት ይህ ነው፡፡

እኛ በአንድ አምላክ÷ በአንድ ልጁም በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን፡፡ ይኸውም ቃሉ÷ ኃይሉ÷ ምክሩ÷ ጥበቡ ነው፡፡ ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር የነበረ ነው፡፡ በኋለኛው ዘመን ከመለኮታዊ መንበሩ ሳይለይ ወደኛ መጣ፡፡ ከመንፈስ ቅዱስና ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆነ፡፡ በሠላሳ ዓመቱ በዮርዳኖስ ተጠመቀ፤ ፍጹም (ምሉዕ) ሰው ሆነ፡፡ በጳንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን በዕንጨት ላይ ተሰቀለ፤ ታመመ፤ ሞተ፤ ተቀበረ፤ በሦስተኛውም ዕለት ተነሣ፡፡

ከዚህ በኋላ በአርባ ቀን በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ፡፡ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ላይ ይፈርድ ዘንድ በክብር ይመጣል፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም፡፡

ከአብ በሠረጸ÷ ጌታ÷ አዳኝ በሆነ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን፡፡ ኀጢአትን ለማስተስረይ በአንዲት ጥምቀትም እናምናለን፡፡ ለዘላለም ሕይወት የሙታንን መነሣት ተስፋ እናደርጋለን፤ አሜን!

እኛስ እውነተኛ በሆነው በጥርጊያውና በንጉሥ መንገድ እንሄዳለን፤ ከአባቶቻችን ትምህርት ወደ ግራም ወደ ቀኝም አናዘነብልም፡፡ ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት÷ የጥበብ ምንጭ ጳውሎስ÷ ሰባ ሁለቱ አርድእት÷ በኒቅያ የተሰበሰቡ ሃይማኖታቸው የቀና ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንቱ÷ በቍስጥንጥንያ የተሰበሰቡ አንድ መቶ ኀምሳው÷ በኤፌሶን የተሰበሰቡ ሁለት መቶው፡፡

የናዖድ ልጅ÷ የወናግ ሰገድ ልጅ÷ በመንግሥቴ አጽናፍ ሰገድ የምባል÷ የኢትዮጵያ ንጉሥ እኔ ገላውዴዎስ÷ እንዲህ እሰብካለሁ፤ እንዲህ አስተምራለሁ፡፡

ሰንበትን የምናከብርበት ምክንያት÷ «ደሙ በልጆቻችን ላይ ይሁንብን» (ማቴ. 27÷25) ብለው ክርስቶስን እንደሰቀሉት እንደ አይሁድ የምናከብራት አይደለንም፡፡ እነዚህ አይሁድ ውሃ አይቀዱም፤ እሳት አያነዱም፤ ወጥ አይሠሩም፤ እንጀራ አይጋግሩም፤ ከቤት ወደ ቤት አይሄዱም፡፡

እኛ ግን የምናከብራት ሐዋርያት በዲድስቅልያ እንዳዘዙ ቅዳሴን በመቀደስና ግብር (ማዕድ) በመሥራት ነው እንጂ እንደ እሑድ ሰንበት አይደለም፤ ይህችውም ዐዲሲቱ ዕለት ናት፡፡ «እግዚአብሔር የሠራት ዕለት ይህች ናት፤ እንደሰትባት፤ ሐሤትም እናድርግባት፡፡» ብሎ ዳዊት ስለርሷ ተናገረ፤ (መዝ. 117(118)÷21)፡፡ በዚህች ዕለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተነሥቶባታልና÷ በዚህች ዕለት መንፈስ ቅዱስ በጽርሐ ጽዮን ለሐዋርያት ወርዶአልና÷ በዚህች ዕለት ሁልጊዜ ድንግል በሆነች በቅድስት ማርያም ማሕፀን ሰው ሆኖአል፤

በዚህች ዕለት ለጻድቃን ሽልማት ለመስጠት፤ ኀጥአንን ለመቅጣት ዳግመኛ ይመጣል::

ስለ ሥርዐተ ግዝረትም እንደ አይሁድ የምንገዘር አይደለንም፤ የጥበብ ምንጭ የጳውሎስን ትምህርት እናውቃለንና፤ «መገዘር አይጠቅምም፤ አለመገዘርም ግዳጅ አይፈጽምም:: ዐዲስ ፍጥረት ነው እንጂ፤ ይኸውም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው::» (ገላ. 5÷6፤ 6÷15):: ዳግመኛም ለቆሮንቶስ ሰዎች «የተገዘረ ቍልፈትን (አለመገዘርን) አይሻ::» አለ፤ (1ቆሮ. 7÷18):: የጳውሎስ የትምህርቱ መጽሐፍ ሁሉ በኛ ዘንድ አለ:: ስለ ግዝረትና ስለ ቍልፈት ያስተምረናል:: ነገር ግን በኛ ዘንድ ያለው ግዝረት÷ እንደ ኢትዮጵያና እንደ ኖባ የፊት መተልተል÷ እንደ ሕንድ ሰዎች የጆሮ መነደል ያለ የአገር ልማድ ነው:: ይህን የምናደርገው በኦሪት ሕግ አይደለም፤ በሰው ልማድ ነው እንጂ::

ዐሣማንም ስለመብላት ከመብላት የተከለከልነው÷ እንደ አይሁድ የኦሪትን ሕግ ለመጠበቅ ብለን አይደለም:: የሚበላውን አንጸየፈውም፤ አናረክሰውም፤ የማይበላውንም ብላ ብለን አናስገድደውም:: አባታችን ጳውሎስ ለሮም እንደጻፈው «የሚበላ የማይበላን አይንቀፈው (አይናቀው)፤ እግዚአብሔር ሁሉንም ተቀብሏቸዋልና:: የእግዚአብሔር መንግሥት በመብልና በመጠጥ አይደለችም:: ለንጹሓን ሁሉ ንጹሕ ነው:: ለሰው ክፉው ከጥርጣሬ ጋር መብላት ነው::» (ሮሜ 14÷3፤ 17፤ ቲቶ 1÷15፤ 1ቆሮ. 8÷9-13):: ወንጌላዊ ማቴዎስም «ከአፉ ከሚወጣው በቀር ሰውን የሚያረክሰው የለም፤ ወደ ሆድ የሚገባ ጥቂት ቆይቶ ይወድቃል፤ ይፈሳል፤ ምግቦችን ሁሉ ያነጻል::» አለ፤ (ማቴ. 15÷11፤ 17፤ ማር. 7÷15):: ይህ አባባሉ ከኦሪት መጽሐፍ የተማሩ የአይሁድን የስሕተት ሕንጻ ሁሉ አፈረሰው:: እኔና በግዛቴ ውስጥ ያሉ÷ በትእዛዜ የሚያስተምሩ ዐዋቂዎች ካህናት ሃይማኖት ይህ ነው:: ከወንጌል መንገድ÷ ከጳውሎስም ትምህርት ወደ ቀኝና ወደ ግራ አይሉም:: በኛም የታሪክ መጽሐፋችን ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ በግዛት ዘመኑ የተጠመቁትን አይሁድ ሁሉ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ዕለት የዐሣማ ሥጋ እንዲያበሏቸው አዘዘ የሚል ጽሑፍ አለ::

ነገር ግን ሰው በልቡ ደስ እንዳለው የእንስሳትን ሥጋ ከመብላት ይወሰናል:: የዓሣ ሥጋ የሚወድ አለ፤ የዶሮ ሥጋ መብላት የሚወድ አለ፤ የበግ ሥጋ ከመብላት የሚወሰን አለ:: ሁሉ ለልቡ ደስ ያለውን ይከተላል:: የሰው ውዴታውና ፈቃዱ እንደዚህ ነው:: ስለ እንስሳት ሥጋ መብል በዐዲሲቱ መጽሐፍ (በዐዲስ ኪዳን) ውስጥ ቀኖናም ሥርዐትም የለም:: ለንጹሓን ሁሉ ንጹሕ ነው:: ጳውሎስም «የሚያምን ሁሉን ይብላ::» አለ፤ (ሮሜ 14÷22-23):: የሃይማኖቴን እውነት ታውቅ ዘንድ ይህን ለመጻፍ ተጋሁ:: ዳሞት በሚባል ሀገር በሠኔ 23 ቀን 1555 ዓ.ም ተጻፈ::



# የጥላና አካል ትርጉም

ጥላ ብርሃን ባለበት ስፍራ የሚገኝ÷ የሚታይ÷ የአካል ቅርጽ (አምሳል) ነው:: ጥላ ምን ጊዜም ሊኖር የሚችለው አካል ሲኖር ብቻ ነው፤ አካል በሌለበት ጥላ የለም::

ብዙ ጊዜ ቤት ውስጥ ተቀምጠን ሳለን ከውጭ አንድ ሰው ቢመጣ÷ የሰውዬውን ማንነትና አካሉን ከማየታችን በፊት አስቀድሞ የምናየው ጥላውን ነው:: ወይም ደግሞ የኮቴውን ድምፅ እንሰማለን:: ከዚያም አካሉ ተገልጦ እስከምናየው ድረስ ትኩረታችን ሁሉ በጥላው ላይ ያርፋል:: ጥላ በዚህ ስፍራ አካሉን በናፍቆት እንድንጠብቅ ከሚያደርገን በቀር ሌላ ለምንም አይጠቅመንም:: በመሆኑም ጥላን መመልከት የሚቻለው አካሉ እስኪገለጥ ድረስ ብቻ ይሆናል:: አካሉ ከተገለጠ በኋላ ግን ጥላን አተኩሮ የሚመለከተው ቀርቶ ልብ የሚለው እንኳ አይኖርም::

ጥላ ከራሱ ባሕርይ የሚገኝ ሳይሆን ከአካል መኖር የተነሣ የሚመጣ ነው:: ያውም ቢሆን የአካልን ቅርጽ ብቻ እንዲሁ በደፈናው የሚያሳይ እንጂ በራሱ ሕይወት ያለው አይደለም:: ይህም የሰው አትኩሮትና መሻት የአካሉ ቅርጽ ብቻ በሚታይበት በጥላው ላይ ሳይሆን ጥላውን ባስገኘው አካል ላይ እንዲያርፍ ያስገድደዋል::

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚመሰክረው ሰው በኀጢአት ከወደቀ በኋላ÷ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ባለው ታሪክ ለሰው ልጆች በሁለት የተለያዩ ዘመናት÷ በተለያዩ ስልቶችና መንገዶች ተናግሯል:: እነዚህም ከጥንት ጀምሮ በብዙ ዐይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶች በነቢያት የተናገረበትና በዚህ ዘመን መጨረሻ ሁሉን ወራሽ ባደረገውና ዓለማትን በፈጠረበት በአንድያ ልጁ የተናገረበት ዘመናት ናቸው፤ (ዕብ. 1÷1-2)::

እነዚህ እግዚአብሔር ለሰው ለጆች የተናገረባቸው ሁለት ዘመናት በጥላና አካል÷ በምሳሌና አማናዊ ነገር መገለጻቸውን የእግዚአብሔር ቃል ያስረዳናል:: «የጥንት ዘመን» የተሰኘው ብሉይ ኪዳን «የዘመኑ መጨረሻ» ለተሰኘው ዐዲስ ኪዳን ጥላና ምሳሌው ነው:: ዐዲስ ኪዳን ደግሞ አካልና አማናዊ ነገር ነው፤ (ቈላ. 2÷17፤ ዕብ. 8÷5፤ 10÷1)::

ይህ አካልና አማናዊው ነገር ዐዲስ ኪዳን ከመምጣቱ በፊት÷ ቀድሞ የመጣውና የታየው ጥላና ምሳሌ የሆነው ብሉይ ኪዳን ነው:: ጥላና ምሳሌ የሆነውን ያዩት የብሉይ ኪዳን ሰዎችም÷ የጥላውና የምሳሌው ቀድሞ መታየት የአካሉንና የአማናዊውን ነገር መምጣት አብሣሪ መሆኑን ስለተረዱ÷ በጥላው ዘመን ሆነው አካሉን ለመመልከት በናፍቆት ይጠብቁ ነበር:: ሆኖም አረፍተ ዘመን ስለገታቸው ሳይመለከቱት በርቀት ተሳልመውት ብቻ አንቀላፉ፤ (ማቴ. 13÷17፤ ዕብ. 11÷13)::

ለዐዲስ ኪዳን ምእመናን ግን አሁን ተገልጧልና ጥላውን ሳይሆን አካሉን እየተመለከቱና ከበጎ ነገሩ ነፍሳቸውን እያጠገቡ ይገኛሉ።

ብሉይ ኪዳን በዘላለም ሥርዐት ስም ለእስራኤል ዘሥጋ የተሰጠ ኪዳን መሆኑ ይታወቃል። ብዙ ምድራዊ አገልግሎቶቹና ሥርዐቶቹ «የዘላለም ሥርዐት ይሁንላችሁ» በሚል ድንጋጌ መመሥረታቸው ግን ብሉይ ኪዳንን ዘላለማዊ አያሰኘውም፤ (ዘፀ. 28÷43፤ 12÷17-24፤ ዘሌ. 10÷12-15፤ 23÷14፤ 21፤ 31፤ 41)።

በነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ «ዘላለም» የሚለው ቃል÷ እስከ መጨረሻው ለዘላለም መኖርን ሳይሆን እስከ ዐዲስ ኪዳን ጅማሬ ድረስ ያለውን ዘመን አመልካች ነው። ምክንያቱም በሌላ በኩል ብሉይ ኪዳንን ተክቶ ያለውና ክርስቶስ ሰው የሆነበት ዐዲስ ኪዳን÷ የዘመኑ መጨረሻ (ፍጻሜ ዘመን) ተሰኝቷልና፤ (ገላ. 4÷4፤ ኤፌ. 1÷10፤ ዕብ. 1÷2፤ 1ቆሮ.10÷11)።

እንዲህማ ባይሆን «ለዘላለም ሥርዐት ይሁኑ» የተባሉትን የብሉይ ኪዳን ሥርዐቶች ዛሬም እየፈጸምናቸው በተገኘን÷ ባለመፈጸማችንም ተጠያቂነትን ባስከተሉብን ነበር።

እነዚህ የጥላ አገልግሎቶች ከመጀመሪያው ፍጹማን ያልሆኑና ነቀፌታ ያለባቸው ከመሆናቸውም በላይ÷ የአገልግሎት ዘመናቸው አካሉ እስኪመጣ ድረስ ብቻ ነበር። አሁን ግን ዘላለማዊነታቸው አክትሞ የሚሻሩት ተሽረው÷ የሚተኩት ተተክተው እንደማይጠቀሙ ተቈጥረዋል፤ (ዕብ. 7÷18-19፤ 8÷7)።

ይህን ሐሳብ ግልጽ ለማድረግ በምሳሌነት ግዝረትን ለመመልከት ይቻላል። የጥላው ክፍል የነበረው የግዝረት ሥርዐት በቅድሚያ ለአብርሃም ሲሰጠው «የዘላለም ቃል ኪዳን ይሁንላችሁ» ተብሎ ነው፤ (ዘፍ. 17:1-14)። ይሁን እንጂ የግዝረት ዘላለማዊነት ብሉይ ኪዳን እስከሚያበቃበት ጊዜ ድረስ ብቻ መሆኑ÷ በአይሁድ ዘንድ ብቻ ካልሆነ በቀር ክርክር አያስነሣም። ምክንያቱም በዐዲስ ኪዳን መገዘርም ሆነ አለመገዘር የዘላለም ሕይወትን ለማስጠትም ይሁን ለማስከልከል ባለመብት አለመሆኑ ተጽፎአል፤ (የሐዋ. ሥራ 15÷1-5፤ 28-29፤ 1ቆሮ. 7÷18-19፤ ገላ. 5÷2-6)።

በጥላውና በአካሉ መካከል ያለውን አንጻራዊ ልዩነት የተረዱ ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሁለቱንም በማነጻጸር÷ አካሉ ከጥላው÷ አማናዊው ከምሳሌው በብዙ መንገድ ብልጫ እንዳለው÷ እኛም በዚህ በመጨረሻው ዘመን የምንገኝ ክርስቲያኖች ከጥላውና ከምሳሌው አገልግሎት ወጥተን÷ የአካሉና የአማናዊው ነገር አገልጋዮች መሆናችንን በየድርሳናቸው መስክረዋል፤ ሊቁ ዮሐንስ አፈ ወርቅ የሰጠውን ምስክርነት ቀጥሎ እንመልከት: -

> «ኀበ አይሁድ ተብህለ ከመድንግል ትፀንስ፤ ወበኀቤነሰ ኮነ እሙነ፤ እስመ መጽሐፍሰ ለምኵራብ፤ ወተዐውቆ ለቤተ ክርስቲያን። እንታክቲ ነሥአት ሰደፈ፤ ወዛቲ አጥረየት ባሕርየ። ምኵራብ አነመት ፀምረ፤ ወቤተ ክርስቲያን ተዐጽፈቶ። ምኵራብ ወለደቶ፤ ወቤተ ክርስቲያን ተወከፈቶ። ምኵራብ ሐፀነቶ፤ ወአልሐቀቶ፤ ወቤተ ክርስቲያን ተእኀዘት ቦቱ፤ ወረብሐቶ። ውስተ እንታክቲ ተተክለ ሐረገ ወይን፤ ወበኀቤነሰ ኮነ አስካለ ጽድቅ። እንታክቲ ዐጸረት አስካለ ውስተ ምክያድ፤ ወአሕዛብ ሰትዩ ስቴ ምስጢር። እንታክቲ ዘርዐት ኀጠተ ሥርናይ፤ ወአሕዛብ ዐጸድዎ በማዕጸደ ሃይማኖት። አሕዛብ አስተጋብኡ ጽጌረዳ በኂሩቱ፤ ወሦኩሰ ተርፈ ኀበ አይሁድ፤ ዘውእቱ ሕጸተ ሃይማኖት። ሠረረ ዖፍ ንኡስ÷ አብዳን እንዘ ይነብሩ ኀበ ጽላሎቱ። አይሁድ ይተረጕሙ ክርታሰ ጽሕፈት፤ ወአሕዛብ ይቀስሙ ፍሬሁ ለጽሕፈት።»
>
> ትርጓሜ: - «በአይሁድ ዘንድ ድንግል እንድትፀንስ ተነገረ፤ በኛ ዘንድ ግን እውነት ሆነ፤ አምላካዊው ንባብ ለምኵራብ÷ ንባቡን መረዳት ለቤተ ክርስቲያን ነውና። ያቺ ዕንቍ የሚወልደውን (ሰደፍን) ገንዘብ አደረገች፤ ይህች ግን የባሕር ዕንቍን አሷጀች። ምኵራብ በምሳሌ ፀምርን (የበግ ጠጕርን) ሸመነች፤ ቤተ ክርስቲያን ግን ተጐናጸፈችው። ምኵራብ ወለደችው፤ ቤተ ክርስቲያን ግን ተቀበለችው። ምኵራብ አጥብታ አሳደገችው፤ ቤተ ክርስቲያን ግን ጸናችበት፤ ብዙ አተረፈችበት። በዚያች ውስጥ (በምኵራብ) የወይን ሐረግ ተተከለ፤ በኛ ዘንድ ግን የጽድቅ ፍሬ ሆነ። ያቺ ወይንን በውድማ ረገጠች፤ አሕዛብ ግን የምስጢሩን ገፈታ ጠጡ። ያቺ የስንዴን ቅንጣት ዘራች፤ አሕዛብም በሃይማኖት ማጨጃነት ዐጨዱት። በቸርነቱ አሕዛብ ጽጌረዳን ሰበሰቡ፤ እሾኹ ግን በአይሁድ ዘንድ ቀረ። ይኸውም የሃይማኖት ጐድለት ነው። ሰነፎች በጥላው አጠገብ ተቀምጠው ሳሉ ትንሽ ወፍ በርሮ ሄደ። አይሁድ በብራና የተጻፈውን ይተረጕማሉ፤ አሕዛብ ግን የንባቡን ምስጢር ይረዳሉ።»፤ (ሃይ.አበ. ምዕ.66 ክፍ.9 ቁ.21-24)።



እንግዲህ ብሉይ ኪዳን ጥላ በመሆኑ በውስጡ የያዛቸው የተለያዩ የሥጋ ሥርዐቶች÷ ቍሳቍሶች (ንዋያተ ቅድሳት)÷ መሥዋዕቶች÷ ሕንጻ÷ ቦታና የመሳሰሉት ሁሉ አካሉንና በአካሉ የሚገኘውን ሰማያዊ ነገር የሚያሳዩ እንጂ ቋሚ ነገሮች ስላልሆኑ÷ መጽሐፍ ቅዱስ ጥላውን ከአካል÷ ምሳሌውን ከአማናዊ ነገር በመለየት ዘመናቸው የተለያየ መሆኑንና አንዱ በሌላው ጣልቃ እንዳልገባ÷ ለወደፊቱም እንደማይገባ አብራርቶ ያስረዳናል።

አካል በሌለበት ጥላ ሊኖር እንደማይችል ግልጽ ነው። ጥላ በሌለበት ግን አካል ሊኖር ይችላል። አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም አካል ቦታውን ይዞ ሲቀመጥ የማይኖር ጥላ አለ። እንደዚሁም ሁሉ ዐዲስ ኪዳንን በጥላነቱ ሲያሳይ የኖረው ብሉይ ኪዳን÷ አሁን አካሉ መጥቶ ስፍራውን ስለያዘ ለእርሱ ለጥላው ስፍራ እስከማይገኝለት ድረስ የማይጠቅም ሆኗል። በዐዲስ ኪዳን ውስጥም አገልግሎቱን ሊቀጥል የሚችልበት አንድም ስፍራ አልተሰጠውም።

# ክፍል 1 - የእግዚአብሔር ሕዝብ

## 1.1 የእግዚአብሔር ሕዝብ በብሉይ ኪዳን

የመጀመሪያው ሰው አዳም በኃጢአት ከወደቀ በኋላ የእግዚአብሔርና የሰው ግንኙነት የተቋረጠ መሆኑ ቢታወቅም፥ የአዳም ዘር ከሆኑት መካከል አንዳንዶቹ አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጋቸውና በእምነታቸው መሠረት ተመስክሮላቸው ጽድቅን የወረሱ አበው ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል አቤል፥ ሄኖክና ኖኅ ግንባር ቀደሞቹ ናቸው፤ (ዕብ. 11÷4-7)። ሆኖም በነዚህ አበው ዘመን እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ በይፋ አልመረጠም።

የራሱን ሕዝብ ለማዘጋጀት በወደደ ጊዜ በሉዓላዊ ፈቃዱና በዘላለማዊ ዕቅዱ መሠረት ለሚያዘጋጀው ሕዝብ አባትና ቀዳሚ የሚሆነውን አብርሃምን ጠራው። ሲጠራውም ብዙ በረከት የሚያስወርሱ ተስፋዎችን በመስጠት ነበር። አብርሃምም የተሰጠውን ተስፋ በእምነት ጨብጦ ከአገሩ፥ ከዘመዶቹና ከአባቱ ቤት ለእግዚአብሔር ተለይቶ ወጣ፤ (ዘፍ. 12÷1-4)።

አብርሃም በመጀመሪያ ከአጋር በኋላም ከኬጡራ የወለዳቸው በጠቅላላው ሰባት ልጆች ነበሩት። እንደ ተስፋው ቃል ያልተወለዱ በመሆናቸው ግን የተስፋው ቃል ወራሾች ለመሆን አልበቁም፤ (ዘፍ. 16÷15፤ 25÷1-2)። ምንም እንኳ ከአብርሃም አብራክ የተከፈሉ ልጆቹ ቢሆኑም የእግዚአብሔር ቃል: - «እነዚህ ከእስራኤል የሚወለዱ ሁሉ እስራኤል አይደሉምና፥ የአብርሃምም ዘር ስለሆኑ ሁላቸው ልጆች አይደሉም። ነገር ግን በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል ተባለ። ይህም የተስፋ ቃል ልጆች ዘር ሆነው ይቈጠራሉ እንጂ እነዚህ የሥጋ ልጆቹ የሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች አይደሉም ማለት ነው።» (ሮሜ 9÷6-8) በማለት እንደመሰከረው፥ በእግዚአብሔር ሕዝብ መሥመር ውስጥ ያልገቡ ናቸው።

ይስሐቅ ብቻ ግን እንደ ተስፋው ቃል የተወለደ በመሆኑ የተስፋው ቃል ወራሽ ዘር ነው፤ (ዘፍ. 15÷4፤ 17÷19)። ስለዚህ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ተስፋ ዐደሰለት፤ (ዘፍ. 20÷3-5)።

እርሱም ለጥቆ ተስፋውን የሚወርስ ልጅ ያዕቆብን ከርብቃ ወለደ። ርብቃ የፀነሰችው መንታ ልጆችን ነበር። መንትዮቹ ገና በእናታቸው ማሕፀን ሳሉ እግዚአብሔር ለራሱ የሆነውን ያዕቆብን መረጠ። የያዕቆብ መንትያና በኵር የነበረው ኤሳው ግን በሥጋ ልደት የአብርሃም ዘር፥ የይስሐቅ ልጅ ቢሆንም ቅሉ በእግዚአብሔር ሕዝብ መሥመር ውስጥ አልተካተተም፤ (ዘፍ. 25÷21-26፤ ሚል. 1÷2፤ ሮሜ 9÷10-13)። ስለዚህ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውንና ለይስሐቅ ያጸናውን ቃል ኪዳኑን፥ ለያዕቆብም ደግሞ በማደስና በማጽናት ለሚያዘጋጀው ለራሱ ሕዝብ የነገድ አባቶች የሚሆኑ 12 ወንድ ልጆችን ሰጠው፤ (ዘፍ. 28÷13-15፤ 35÷23-26)።

የእግዚአብሔር ሕዝብ «እስራኤላውያን» የተሰኙበትን ስም ያስገኘውም ይኸው ያዕቆብ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ ካሸነፈ በኋላ «ካልባረክኸኝ አልለቅህም» ባለው ጊዜ፥ «ያዕቆብ» የነበረውን ስሙን ለውጦ «እስራኤል» ብሎ ጠራው፤ (ዘፍ. 32÷24-28)።



ከዐሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች አንዱ የሆነውን ዮሴፍን፥ የገዛ ወንድሞቹ በቅንአት ሸጠው ወደ ግብጽ ቢሰዱትም፥ በኋለኛው ዘመን በረኀብ ምክንያት ተሰደው ለሚመጡት ወገኖቹ መድኀኒት በማድረግ እግዚአብሔር ተጠቀመበት፤ (ዘፍ. 45÷4-8)። በምድር ሁሉ ላይ ለሚሆነው ረኀብ መፍትሔ ያመጣ ዘንድ በፈርዖን ግዛት ሁሉ ላይ በግብጽ የተሾመው ዮሴፍም፥ የረኀቡ ሰለባ ላለመሆን ወደ ግብጽ የወረዱትን ወንድሞቹን፥ አባቱንና ጠቅላላ ቤተሰቦቻቸውን በድምሩ ሰባ የሚሆኑ ወገኖቹን በግብጽ እንዲቀመጡ አደረገ፤ (ዘፀ. 1÷1-5)።

እነዚህ ጥቂት የሆኑ የአብርሃም ዘሮች በረኀብ ምክንያት ወደ ግብጽ ይውረዱ እንጂ፥ ነገሩ የሆነው እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ ለመፈጸም ነው፤ (ዘፍ. 15÷13-14)።

ይህ የእግዚአብሔር ዐላማ መፈጸም የሚጀምርበት ሰዓት ሲደርስ ዮሴፍ ሞተ። ከዚህ በኋላ ዮሴፍንና ውለታውን የማያውቅ ሌላ ንጉሥ እስኪነሣ ድረስ ሰባ ነፍሳት ሆነው ወደ ግብጽ የወረዱት የአብርሃም ዘሮች በምድረ ግብጽ እየበዙና እየበረከቱ ሄዱ። ይህም በጊዜው የነበረውን ፈርዖን ታላቅ ሥጋት ላይ ጥሎታል። ስለዚህ ሰልፍ በተነሣበን ጊዜ ጠላቶቻችንን ረድተው እንዳይወጉን በሚል ምክንያት በተለያዩ መከራዎች ሕዝቡን ማስጨነቅና ማሠቃየቱን ቀጠለበት። የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር ግን «ነገር ግን እንዳስጨነቋቸው መጠን እንዲሁ በዙ፥ እጅግም ጸኑ።» ይላል፤ (ዘፀ. 1÷12)።

እግዚአብሔር አብርሃምን በእምነት ለማጽደቅ ሲል እርሱን ወደ ሜዳ አውጥቶ፥ ከዋክብተ ሰማይን መቍጠር ይችል እንደሆ «ቍጠር» ካለው በኋላ «ዘርህም እንደዚሁ ይሆናል» በማለት ተስፋ ሰጥቶት ነበር። በሌላም ስፍራ ዘሩን በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ እንደሚያበዛ ነግሮታል። በምድረ ግብጽ የሕዝቡ ቍጥር እየበዛ መሄዱ፥ ይኸው ተስፋ መፈጸሙን ያሳያል፤ (ዘፍ. 15÷5-6፤ 22÷17)።

በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር ለራሱ የለያቸውንና የአብርሃም ዘር የሆኑትን ሕዝበ እስራኤልን፥ በጽኑ እጅና በተዘረጋች ክንድ ከባርነት ቤት ከግብጽ ነጻ አወጣ። ለአብርሃም እስጥሃለው ብሎ ወደ ማለለት ምድር በማምጣትም ለእርሱ ብቻ በመገዛት እንዲያመልኩት አደረገ።

እነዚህ እስራኤላውያን በጥላው ዘመን ከሌላው ሕዝብ የተለዩ በመሆናቸው፥ ለሌላው ያልተሰጡና ለሚመጣው አካል ጥላ የሆኑ ምድራዊ በረከቶች ተሰጥተዋቸው ነበር፤ (መዝ. 147÷8-9፤ ሮሜ 9÷4-5)። የሚበዙቱ ግን እግዚአብሔርን ከመከተል ፈቀቅ በማለት በተለያዩ ጊዜያት ቅዱሱን ኪዳን በማፍረሳቸው የበረከቱ ወራሾች ለመሆን አልበቁም። ይልቁንም መሲሕ ሆኖ ከእነርሱ በሥጋ የመጣውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማመንና ከጥላው ወደ አካሉ ዘወር ለማለት ፈቃደኝነታቸውን ባለማሳየታቸው (ዮሐ. 1÷11)፥ እነርሱ ቸል ያሉትን መዳን አሕዛብ በእምነት ተቀብለው ጸደቁበት፤ (ሮሜ 11÷7-12)።

በዚህም ምክንያት በሥጋ የሆኑ እስራኤል (እንደ ቤተ ክርስቲያናችን አጠራር «እስራኤል ዘሥጋ») ተሰኝተዋል፤ (1ቆሮ. 10፥18)።

እንግዲህ በጥላው ዘመን የእግዚአብሔር ሕዝብ መሠረታዊ አመጣጥ እስካሁን እንዳየነው ከአብርሃም የሚጀምር ነው። የብሉይ ኪዳንም ሆነ የዐዲስ ኪዳን ሰዎች፥ ስለ እስራኤል ሕዝብ ከሥር ጀምሮ ለመናገር ሲፈልጉ ብዙ ጊዜ መነሻ የሚያደርጉት አብርሃምን ነው። ምክንያቱም የሕዝብነታቸው መሥራች እርሱ ነውና፤ (ኢሳ. 41፥9፤ 51፥2፤ ዮሐ. 8፥33፤ 39፤ የሐዋ. ሥራ 7፥2፤ 13፥26)።

በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተመዘገበው ታሪክም ከተስፋው ዘር ውጪ የሆኑትን ሰዎች ታሪክ እንደ አስፈላጊነቱ ነካክቶ ሲያልፍ፥ ትኩረት ሰጥቶ በስፋት የሚናገረው ከአብርሃም በመነሣት በይስሐቅና በያዕቆብ በኩል ስለ ተቈጠረው ዘር ነው። የዚህም ግብ የአብርሃም የቃል ኪዳን ፍጻሜና የተስፋው ሙላት ወደሆነው ክርስቶስ መድረስ ነው፤ (ማቴ. 1፥2-18)።



## 1.2 የእግዚአብሔር ሕዝብ በዐዲስ ኪዳን

እንደ ብሉይ ዘመን ሕዝብ የዐዲስ ኪዳን ዘመን የእግዚብሔር ሕዝብ ከአንድ ከተወሰነ ዘር ወይም ነገድ የተውጣጣ አይደለም። የዘር፥ የቀለም፥ የሀብትና የሹመት ልዩነት ሳይደረግ ሁሉን ዐቀፍ የሆነና በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑትን ሁሉ ያካተተ መንፈሳዊ ጉባኤ ነው፤ (ገላ. 3፥26-28፤ 1ቆሮ. 12፥13፤ ሮሜ 10፥12)።

ቀድሞ ግን ከአይሁድ ወገን ያልሆኑት አሕዛብ በተገረዙት አይሁድ ዘንድ ያልተገረዙ ተብለው የሚናቁ፥ ከእስራኤል መንግሥት ርቀውና ለተስፋውም ቃል እንግዶች ሆነው፥ በዚህም ዓለም ተስፋ ዐጥተው፥ ከእግዚአብሔርም ተለይተው ያለ ክርስቶስ የነበሩ ወገኖች ነበሩ። ክብር ምስጋና ይግባውና መድኀኒ ዓለም ክርስቶስ ቤዛ ሆኖ በመሞቱ፥ ይህን በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ተፈጥሮ የቈየውን ልዩነት አስወግዶ። በመካከላቸው የቆመውን የጥል ግድግዳም አፈራርሶ፥ ሁለቱን ሕዝቦች በማዋሐድ ከሁለታቸው አንድን ዐዲስ ሰው (ቤተ ክርስቲያንን) በአንድ አካል ፈጥሯል፤ (ኤፌ. 2፥11-17)።

ባለፈው ክፍል እንደተመለከትነው እግዚአብሔር አብርሃምን የሕዝቡ አባትና መሥራች ይሆን ዘንድ ሲጠራው፥ አባትነቱ በብሉይ ኪዳን ዘመን ለነበሩት ሕዝቡ ብቻ ሳይሆን ወደፊት በዘመኑ ፍጻሜ ለሚነሡት የዐዲስ ኪዳን ሕዝብም ጭምር ነው። አስቀድሞ ለአብርሃም በሰጠው የተስፋ ቃል ውስጥ «... የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።» (ዘፍ. 12፥3)፥ በሌላም ስፍራ «... ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁ።» (ዘፍ. 17፥5፤ ሮሜ 4፥17) የሚለው፥ በዐዲስ ኪዳን የእምነቱን ፍለጋ ተከትለው ለሚነሡ ሁሉ አብርሃም አባት መሆኑን አመልካች ነው፤ (ሮሜ 4፥11-12)።

ስለሆነም አይሁድ የአብርሃም ዘር ነን፥ የተገረዝን ነን፥ ወዘተ... በሚሉት ነገሮች ላይ መሥርተውት የነበረውን ሥጋዊ ትምክሕታቸውን መና በማስቀረት፥ እነርሱ ከሚንቋቸው አሕዛብ መካከል እንደ ተስፋ ቃሉ ለአብርሃም ልጆችን አስነሣ፤ (ማቴ. 3፥9)።

አብርሃም ሳይገረዝ በፊት በነበረው እምነት ጽድቅን እንደተቀበለ ሁሉ፥ ከአሕዛብ ወገን የሆኑቱ ልጆቹም ሳይገረዙ በእምነት ብቻ ጽድቅን የተቀበሉ ናቸው፤ (ሮሜ 4፥11-12)። ስለዚህም የእግዚአብሔር እስራኤል (እንደ ቤተ ክርስቲያናችን አጠራር «እስራኤል ዘነፍስ (ዘመንፈስ)») ተሰኝተዋል፤ (ገላ. 6፥16)።

በዐዲስ ኪዳን የሚገኙ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ ብሉይ ኪዳን ሕዝብ በተስፋ ሳይሆን በተጨበጠ ነገር፥ በጥላው ሳይሆን በአካሉ፥ በምሳሌ ሳይሆን በአማናዊ ነገር ያመኑ፥ እግዚአብሔር በዘላለማዊ ፍቅሩ የወደዳቸውና በአንድያ ልጁ ሞት የዋጃቸው፥ በሚታዩና በሚዳሰሱ ቍሳዊ በሆኑ ጥላ ነገሮች ሳይሆን፥ በእውነትና በመንፈስ ሆነው በሰማያዊቱ ቅድስተ ቅዱሳን ተገኝተው እግዚአብሔርን

የሚያመልኩ፥ ከጨለማው (ከዲያብሎስ) መንግሥት ሥልጣን ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት የፈለሱ የሰማያዊቱ አገር ዜጎች ናቸው፤ (ሮሜ 7፥6፤ ኤፌ. 2፥6፤ ዮሐ. 4፥24፤ ቈላ. 1፥13-14፤ ዕብ. 12፥22-24)::

አካሉ በተገለጠበት ዘመን ያመኑ ቅዱሳን በመሆናቸውም የጥላውን ዘመን ቅዱሳን ፍጹማን አድርገዋል:: እግዚአብሔር አስቀድሞ በእምነታቸው ተመስክሮላቸው ሳሉ የተሰጠውን ተስፋ ያላገኙ የነበሩትን እኒያን፥ ያለ ዐዲስ ኪዳን ቅዱሳን ፍጹማን እንዳይሆኑ ስለ ዐዲስ ኪዳን ቅዱሳን የሚበልጥ ነገርን አይቶ ነበርና፤ (ዕብ. 11፥39-40)::



## 1.3 የሁለቱ ሕዝቦች አንድነትና ልዩነት

በብሉይ ኪዳንና በዐዲስ ኪዳን የሚገኙት የእግዚአብሔር ሕዝብ አንድ ከሚያደርጓቸው ነጥቦች መካከል መሠረታዊ የሆኑትን ቀጥሎ እንመለከታለን::

እግዚአብሔር በጥላው ዘመን የአብርሃም ዘርን ለእርሱ የተለየ ሕዝብ እንዲሆን የመረጠው፥ ከሌሎች አሕዛብ ይልቅ እነርሱ የተለየ ጽድቅ ስለነበራቸው፥ ወይም በቍጥር ስለበለጡና በመሳሰሉት ምክንያቶች አይደለም:: እግዚአብሔር በዘላለማዊ ፍቅሩ እንዲሁ ስለወደዳቸውና ለአባቶቻቸው ለነአብርሃም የማለላቸው ቅዱሱን መሐላ ስለጠበቀ ብቻ ነው፤ (ዘዳ. 4፥37፤ 7፥6-8፤ 10፥15)::

በዐዲስ ኪዳንም የእግዚአብሔር ሕዝብ በዚያው መስፈርት መሠረት የተመረጡ ናቸው፤ (2ጢሞ. 1፥9፤ ቲቶ 3፥5፤ ኤፌ. 1፥4)::

ይህም በሁለቱም ዘመናት የነበሩት የእግዚአብሔር ሕዝብ ኀጢአተኞች የነበሩና በእግዚአብሔር የተወደዱ መሆናቸውን ያመለክታል:: ሁለቱን ሕዝቦች የሚያመሳስል የመጀመሪያው መሠረታዊ ነጥብ ይህ ነው::

ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ ሁለቱንም ሕዝቦች እግዚአብሔር ያጸደቃቸውና ለእርሱ የተለዩ ወገኖች ያደረጋቸው በእምነት ብቻ መሆኑ ነው፤ (ሮሜ 3፥30፤ ዕብ. 11፥7):: የእግዚአብሔር ሕዝብ አባት የሆነው አብርሃም ጽድቅን ያገኘው በእምነት ሲሆን (ዘፍ.15፥6፤ ሮሜ4፥3)፥ እምነቱም ሕያው የሆነና የሚሠራ በመሆኑ በመልካም ሥራው ተፈጽሟል፤ (ያዕ. 2፥22-23):: ከዚህ የተነሣ አብርሃምን አባት ብለው ሊጠሩ የተገባቸው በሥጋ ልደት የአብርሃም ዘር የሆኑቱ ሁሉ አይደሉም:: ከአይሁድም ከአሕዛብም የእምነቱን ፍለጋ የተከተሉት ብቻ ናቸው፤ (ሮሜ 4፥11-12)::

ለአንዳንዶች ክርስቶስ በቤዛነቱ የተቤዠው በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረውን የሰው ዘር በሙሉ ይመስላቸዋል:: ይህ አመለካከት የተሳሳተ ሲሆን በዐዲስ ኪዳን ዘመን ያሉትን ሰዎች፥ «ምነው እኔም በብሉይ ኪዳን ዘመን በነበርኩኝ! ክፉም ሠራሁ ደግ ክርስቶስ በሞተበት ሰዓት ከሲኦል ወደ ገነት እዛወር ነበር» ብለው እንዲያስቡ ሊያደርግ ይችላል:: በተጨማሪም የብሉይ ኪዳንን ሕዝብ ዕድለኞች፥ የዐዲስ ኪዳንን ሕዝብ ግን ዕድለ ቢሶች እንደሆኑ ያስቈጥራል:: ከምንም በላይ ደግሞ በሥራው ሁሉ ጻድቅ የሆነውን እግዚአብሔርን አድሎአዊና በዘፈቀደ የሚሠራ አምላክ ያስመስለዋል::

በ1ጴጥ. 3፥19 ላይ ክርስቶስ በሥጋ ቢሞትም በመንፈስ ግን ሕያው በመሆኑ፥ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት መስበኩን የሚናገረው ክፍል የሚወክለው የሰውን ዘር በሙሉ አይደለም:: በእምነት ጸድቀው በሕፅነ አብርሃም (በአብርሃም አጠገብ) የተቀመጡትንና የሲኦል ስቃይ ያላገኛቸውን ጻድቃነ ብሊትን (የብሉይ ኪዳን ቅዱሳንን) ነው:: ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረው የሰው ዘር በሙሉ

የእግዚአብሔር ፍጥረት ቢሆንም÷ ከሕዝበ እስራኤል በቀር ሁሉም የተመረጠ የእግዚአብሔር ሕዝብ አልነበረም፡፡

ከላይ የተገለጸውን ሐሳብ ሰዎቹ በሚሉት መንገድ እንየው ቢባል እንኳ ትክክል ሆኖ አናገኘውም፡፡ ለምሳሌ በኀጢአተኝነታቸውና ባለማመናቸው ጠንቅ በእሳትና በዲን ተቃጥለው የጠፉትን ሰዶምና ገሞራን÷ ክርስቶስ በሞቱ ከሞት ወደ ሕይወት አሸጋግሯቸዋል (እንደ እነዚህ ወገኖች አመለካከት)፤ ታዲያ አስቀድሞ ካዳናቸው ዳግም ሊፈርድባቸው በፍርድ ቀን እንዴት ቀጠራቸው? (ማቴ. 10÷15፤ 11÷24፤ 2ጴጥ. 2÷6፤ ይሁ. 7)፡፡

የእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት እንዲህ ይላል: –

«ወአዕረጎሙ እግዚአብሔር ለአዳም ወለኵሉ ዘርዑ እም ሲኦል፤ ወአግብኦ ኀበ ዘቀዳሚ ንብረቱ ውስተ ገነተ ፍግዐ፤ ወአኀለፎሙ ለጻድቃን ምስሌሁ እምኀጕል ኀበ ፍትሐ ጽድቅ ወርትዕ፤ ወኀደጎሙ ለእኩያን ህየ ውስተ ትውክልና ምስለ መላእክቲሆሙ፡፡»

ትርጓሜ: - «እግዚአብሔር አዳምንና ልጆቹን ከሲኦል አወጣቸው፤ ተድላ ደስታ ወደሚያደርግበት ወደቀደመ አኗኗሩ መለሰው፡፡ ጻድቃንን ከርሱ ጋር ከጥፋት÷ ቅንነትና እውነተኛ ፍርድ ወዳለበት አሻገራቸው፡፡ እኩያን ነፍሳትን ግን በሲኦል በቍራኝነት እንዳሉ ከአለቆቻቸው (አጋንንት) ጋር እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ተዋቸው፡፡» (መቅድመ ወንጌል)

ሊቁ ዮሐንስ አፈ ወርቅም በበኩሉ: - «ወተንሥአ በስብሐተ አቡሁ፤ ወዒወወ ነፍሳተ ቅዱሳን እለ ሀለዉ ውስተ ሲኦል÷ እስመ ንጉሥ ወእግዚእ ዘኢይትመዋዕ፡፡»

ትርጓሜ : - «በአባቱ ክብር ተነሣ÷ በሲኦል ተግዘው የነበሩ የቅዱሳንን ነፍሳት አዳነ፤ ንጉሥ÷ ድል ሊነሡት የማይቻል ገዢም ነውና፡፡» (ሃይ. አበ. ም. 62 ክ.1 ቁ.9 ገጽ 219፤ እንዲሁም ገጽ 126 ቁ.30፤ ገጽ 262 ቁ. 16ንም ተመልከት)፡፡

ወደተነሣንበት ነጥብ ስንመለስ በዚህ ክፍል እስካሁን የተመለከትናቸው ሁለት መሠረታዊ ነጥቦች ብቻ ተነሡ እንጂ÷ በሁለቱም ዘመናት ያሉትን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያመሳስሉ ብዙ ነጥቦች ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

ወደ ልዩነቶቹ ስንመጣ ደግሞ የብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደፊት በዘመኑ መጨረሻ ሊመጣ ያለውን÷ ሰማያዊ ነገር ያመለክቱ በነበሩት ጥላና ምሳሌ በሆኑት ምድራዊ ነገሮች መሠረት አምነው የጸደቁ ናቸው፡፡ በዐዲስ ኪዳን ዘመን ያሉት የእግዚአብሔር ሕዝብ ግን በጥላው ሳይሆን በአካሉ÷ በምሳሌው ሳይሆን በአማናዊው÷ በምድራዊው ሳይሆን በሰማያዊው ነገር አምነው የጸደቁ ናቸው፡፡ እኒያ በጥላው÷ እኒህ በአካሉ ይመኑ እንጂ የሁለቱም ሕዝቦች ግብ አንድና በክርስቶስ ማመን ነው፡፡ በተለይም የብሉይ ኪዳን ሕዝበ እግዚአብሔር በቅዱስ መጽሐፍ «ስለ ክርስቶስ የሚነቀፍ ሕዝብ» «በክርስቶስ ያሉ» መሰኘታቸው ይህንኑ የሚያመለክት ነው፤ (ዕብ. 11÷25፤ ኤፌ. 2÷12)፡፡



# ክፍል 2 - የእምነት ማኅተም

## 2.1 የእምነት ማኅተም በብሉይ ኪዳን

ማኅተም እንደ ዘይቤያዊ አፈታቱ የተለያየ ትርጉም ይኖረዋል፡፡ በዚህ ክፍል የምንመለከተው ለትክክለኛነቱ ወይም ለእውነተኛነቱ ማረጋገጫነት÷ ሥልጣን ካለው አካል በደብዳቤ ወይም በሰነድ ላይ ከሚያርፈው ማኅተም ጋር ተያያዥነት ያለውን ሐሳብ ይሆናል፡፡

ማኅተም ለሰነዶች ተአማኒነት ማረጋገጫ ከመስጠቱም በላይ ለሰነዱ በባለቤትነት ተጠያቂ መሆንንም ያመለክታል፡፡

ለእምነት ማኅተም ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት የተስፋን ቃል የሰጠው የታመነ ቢሆንም (ዕብ. 10÷23)÷ እምነትን የተቀበለው ሰው ከተስፋው መዘግየት የተነሣ በእምነቱ እንዳይደክም÷ ጥርጣሬ እንዳይገባውና እርግጠኛ ይሆን ዘንድ ነው፡፡

እውነተኛ እምነት በማየትና በመዳሰስ ሳይሆን በእውነተኛ ተስፋ ላይ ተመሥርቶ÷ ያላዩትንና ያልጨበጡትን ነገር እንደሚያዩትና እንደሚጨብጡት እርግጠኛ መሆን ነው፡፡ እንዲህም ሲባል የሌለውን ነገር ሁሉ በመላ ምት እንዳለ ቈጥሮ ማመን ማለት አይደለም፡፡ ያለውን÷ ለጊዜው ግን ያላዩትን ነገር እንዳለና እንደሚያዩት አድርጎ ማመን÷ ወይም ደግሞ የተገባልን እውነተኛ ተስፋ እንደሚፈጸም እርግጠኛ መሆን ማለት ነው፤ (ዕብ. 11÷1)፡፡

እንዲህ ያለው እምነት በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደና ብፁዕ የሚያሰኝ እምነት ሲሆን (ዮሐ. 20÷29፤ 1ጴጥ. 1÷8)÷ ለብዙዎች የተመሰከረላቸውም እንደዚህ ባለው እምነት ነው፤ (ዕብ.11)፡፡

እነዚህ ቅዱሳን ሳያዩ በተስፋ ብቻ ያመኑ ናቸው፡፡ ማንኛውም ሰው እንደሚያደርገው÷ «ካላየሁ አላምንም» በሚለው የሰው ዐሳብ ሳይያዙና ሳይጠላለፉ «አይ ዘንድ አምናለሁ» በሚለው እምነት ጸኑ፤ (መዝ. 26(27)÷13፤ 2ቆሮ. 4÷17-18፤ 5÷6)፡፡

እግዚአብሔር ለሕዝቡ የእምነት አባት ይሆን ዘንድ አስቀድሞ የጠራው ሰው አብርሃም÷ ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ የተሰጠው ተስፋ እንደሚፈጸም እርግጠኛ ሆኖ አምኗል፡፡ በእምነት መሠረት የሚገኘውን ጽድቅም ወራሽ ሆኗል፤ (ዘፍ. 15÷6፤ ሮሜ 4÷1-3)፡፡

አብርሃም በዐይኑ ሳያይና በእጁ ሳይጨብጥ የተገባለት ቃልና የተሰጠው ተስፋ እንደሚፈጸም ለማመኑ ማረጋገጫ ወይም ማኅተም ያስፈልገው ነበር፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔር ለማመኑ ማረጋገጫ የሚሆን ግዝረትን በምልክትነት ተቀበለ፤ (ዘፍ.17÷10፤ ሮሜ 4÷11)፡፡

የግዝረትን ምልክት ሲቀበል እርሱና ከእርሱ የሚወለዱት ልጆቹ÷ በሥጋ ልደት ዘሮቹ ያልሆኑና በብር የተገዙ÷ ወይም በቤት የተወለዱ ባሮቹ ሁሉ እንዲገዘሩ እግዚአብሔር አዟል፡፡ ትእዛዙ የሚመለከተውም ትእዛዙ በተሰጠበት ወቅት በተለያየ የዕድሜ ክልል የነበሩትንና በጾታቸው ወንድ የሆኑትን ነበር፡፡ ለዘለቄታው ግን

ከተወለዱ ስምንት ቀን የሞላቸውን ወንዶች ልጆች ሁሉ ያጠቃልላል፤ (ዘፍ. 17÷9-14፤ 21÷3-4፤ ዘፀ. 4÷24-26፤ ዘሌ. 12÷3፤ ሉቃ. 1÷58-59፤ 2÷21)፡፡

አብርሃም ሲገዘር የ99 ዓመት ሰው ነበር፡፡ ልጁ እስማኤል ደግሞ የዐሥራ ሦስት ዓመት ልጅ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ከራሱ በመጀመር በቤቱ ያሉትን ወንዶች ሁሉ በመግዘር የቃል ኪዳኑን ምልክት ተቀበለ፤ (ዘፍ. 17÷22-27)፡፡

እግዚአብሔር ለአብርሃም በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ዘሩ ሁሉ በቃል ኪዳኑ የታቀፈ እንደመሆኑ÷ የግዝረትን ምልክት መቀበል አስፈላጊው ብቻ ሳይሆን ግዴታውም ጭምር ነበር፡፡ በቃል ኪዳኑ የታቀፈ ሆኖ ሳለ የግዝረትን ምልክት ያልተቀበለ እስራኤላዊ ሁሉ ከወገኑ ተለይቶ እንዲጠፋ አምላካዊ ትእዛዝ ተላልፎ የነበረውም ለዚህ ነው፤ (ዘፍ. 17÷14)፡፡

በዚህ መንገድ የእምነት ማኅተም ተደርጎ ለአብርሃም የተሰጠው የግዝረት ምልክት ወደ ዘሮቹ ሁሉ በመተላለፍ እስከ ሙሴ ዘመን ደርሷል፡፡

ግዝረት በሙሴ ዘመንም ከግብጽ ባርነት ነጻ ለወጡት የአብርሃም ዘሮች ምልክትና ከሌሎች አሕዛብ ዋና መለያ ሆኖ አገልግሏል፤ (ኢያ. 5÷2-8)፡፡ ይሁን እንጂ በክርስቶስ የማስተማር ዘመንና ከዚያም በኋላ ባለው ዘመን የነበሩ የአይሁድ መምህራን÷ ግዝረት በሙሴ እንደ ተሰጠ አድርገው ተቀብለው ነበር፤ (የሐዋ. ሥራ 15÷1)፡፡ ጌታ ግን ግዝረት ከሙሴ ሳይሆን ከአባቶች መሆኑን በመናገሩ ግዝረት ለመጀመሪያ ጊዜ ለአብርሃም የተሰጠ ምልክት መሆኑን አረጋግጧል፤ (ዮሐ. 7÷22)፡፡

ስለ ፋሲካው ሕግ በተጻፈበት ክፍል በዘር እስራኤላዊ ያልሆነ እንግዳ ሰውና በብር የተገዛ ባሪያ ከእስራኤላውያን ጋር መተባበር ቢፈልግ÷ ወይም ደግሞ ፋሲካን አብሮ ሊያደርግ ቢያስብ አስቀድሞ መገዘር ያስፈልገው ነበር፤ (ዘፀ. 12÷43-45)፡፡

በኦሪት ዘመን አሕዛብ «ያልተገዘሩ» ተብለው በተገዘሩት እስራኤላውያን ዘንድ ይጸየፉ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሣ ከእስራኤል መንግሥት ርቀው÷ ለተስፋው ቃል ኪዳንም እንግዶች ሆነው÷ ተስፋ ዐጥተውና ከእግዚአብሔር ተለይተው ኖረዋል፡፡ ይኸውም በቃል ኪዳኑ ባለመታቀፋቸውና÷ የግዝረትን ምልክት የእምነት ማኅተም አድርገው ባለመቀበላቸው ምክንያት ነው፤ (መሳ. 14÷3፤ 1ሳሙ. 14÷6፤ 17÷26፤ 36፤ ኤፌ. 2÷11፤ ቈላ. 2÷13)፡፡

ይሁን እንጂ አብዛኞቹ አሕዛብ የግዝረት ልማድ ነበራቸው፡፡ ልማዱን ይፈጽሙ የነበረው ግን እንደ እስራኤላውያን የእምነት ማኅተም አድርገው አልነበረም፤ (ኤር. 9÷25-26)፡፡

መገዘር የሚያመለክተው÷ የተገዘረው ሰው ለእግዚአብሔር የተመረጠ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ለተገዘረው ሰው እግዚአብሔር አምላክ ይሆናል ማለት ነው፡፡

አብርሃም ሲገዘር ከዚያን ጊዜ አንሥቶ የሚገዛለትና የሚያመልከው አምላክ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን መሰከረ፤ (ዘፍ. 17÷8፤ 11)፡፡ ይህም



የሥጋን ሸለፈት በመገዘር ውጫዊ ሥርዐት ከመፈጸም በስተጀርባ÷ ለእግዚአብሔር በታማኝነት መታዘዝን÷ ከኀጢአት ሕይወት ተለይቶ በጽድቅ ሕይወት መመላለስን ሁሉ የሚያጠቃልል መሆኑን ያስረዳል፡፡

የሥጋውን ሸለፈት በግዝረት ያስወገደ÷ ነገር ግን ሕይወቱን ለጌታ ያልለየ (ያልቀደሰ) እስራኤላዊ÷ ውጫዊ የግዝረት ሥርዐትን መፈጸሙ ብቻ አይበቃውም፡፡ እንዲያውም በዚህ ሁኔታ ብቻ ያለ እስራኤላዊ መገዘሩ እንደ አለመገዘር እንደሚቈጠርበት የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል፤ (ሮሜ 2÷25-29)፡፡

ስለሆነም ማንኛውም እስራኤላዊ በመገዘር አፍአዊ ሥርዐትን ፈጽሞ የእምነት ማኅተምን እንደተቀበለ ሁሉ÷ በቀጣይ አኗኗሩ ልባዊ መገዘርን ሊያከናውን ይገባል፡፡ ይህም በግዝረት አምሳል የልብን የኀጢአት ሸለፈት በንስሓና በጽድቅ ሕይወት በመኖር ማስወገድ ነው፤ (ዘሌ. 26÷41፤ ዘዳ. 10÷16-17፤ 30÷6፤ ኤር. 6÷10፤ 9÷25)፡፡

## 2.2 የእምነት ማኅተም በዐዲስ ኪዳን

እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመን ሁሉ በዐዲስ ኪዳን ዘመንም በእግዚአብሔርና እርሱ በሰጠው ተስፋ ተፈጻሚነት ማመን እምነት ይባላል::

በእግዚአብሔር ማመን ማለትም እግዚአብሔር ራሱን በሦስትነት (ሥላሴ) የገለጸ አንድ አምላክ መሆኑን÷ ፈጣሪነቱን÷ ጌትነቱን÷ መግቦቱን÷ በአጠቃላይም የእግዚአብሔርነቱን ባሕርያት አምኖ እርሱን ብቻ ማምለክ÷ ለእርሱም ብቻ መገዛት ማለት ነው::

እንዲሁም እግዚአብሔር በኋላኛው ዘመን ለድኅነተ ዓለም የላከው አንድያ ልጁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: - የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ ከመጠፋፋትና ከመቀላቀል ልዩ በሆነ የተዋሕዶ ምስጢር ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ሆኗል፤ አዳኝ ነው፤ ስለ እኔ ቤዛ ሆኖ በምትክነት ሊያድነኝ ሞቷል፤ እርሱን በማመኔ የእርሱ ጽድቅ ለኔ ተቈጥሮልኝ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አገኛለሁ ብሎ ማመን ነው::

የእግዚአብሔርን አምላክነት÷ አዳኝነቱን÷ ፈጣሪነቱን÷ ከማመን ባሻገር ለሚያምኑት ሁሉ በአጠቃላይና ለያንዳንዱም በግሉ የሰጠው ተስፋ እንደሚፈጸም ማመንም እምነት ነው፤ (ዕብ. 11÷6):: በጥቅሉ ግን እምነት የወል ጉዳይ ሳይሆን እያንዳንዱ ሰው በግሉ አምኖ የሚከተለውና ሊኖርበት የሚገባ እውነት ነው::

ዛሬ ግን አብዛኛው ሰው እምነት (ሃይማኖት) የሚለውን ቃል ይበልጥ የሚጠቀምበት÷ ይህን ምስጢር ለመግለጽ ሳይሆን የአንድ ሃይማኖታዊ ድርጅትን ማንነት ለማመልከት ነው:: በመሠረቱ ይህም ስሕተት ላይሆን ይችላል:: ነገር ግን ከላይ በተገለጸው መንገድ የእምነትን ምንነት አለማወቅ ትልቅ መንፈሳዊ ክስረት ነው::

እግዚአብሔር በዐዲስ ኪዳን ለሚገኙ ምእመናን እንዲህ ላለው እምነታቸው ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ የሰጣቸው ማኅተም ጥምቀት ነው፤ (ቈላ. 2÷11-12):: በጥምቀት አማካይነትም የእግዚአብሔር ልጅነታቸውን የሚያረጋግጥ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲታተምባቸው አዝዟል፤ (ማቴ. 28÷19)::

ምእመናን በጥምቀት የሚቀበሉት የሚታየው ማኅተም÷ ለማይታየውና በመንፈስ ቅዱስ ለሚሆነው መታተም ምልክት ነው:: በዚህም ማኅተም የእግዚአብሔር ወገኖች መሆናቸውንና ለዘላለም መዳናቸውን ያረጋግጡበታል፤ (2ቆሮ. 1÷22፤ ኤፌ. 1÷13፤ 4÷30)::

ማንኛውም ሰው በልማድ ወይም በአፈ ታሪክ ሲነገር የሰማውን ስለሚያውቅና አንዳንድ ሥርዐቶችን በሥርዐትነታቸው ስለፈጸመ ብቻ÷ በክርስቶስ የሆነው ድኅነት በእምነት የደረሰለት ሰው ነው ሊባል አይችልም:: ነገር ግን ክርስቶስ እንዴት ባለ የቤዛነት ሥራ እንደ አዳነው በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ዐውቆና ተረድቶ ሲያምን÷ ከአሮጌው የኀጢአት ኑሮ ወደ ዐዲሱ የጽድቅ ኑሮ ይገባል::



ጥምቀት አሮጌውን ሰዋችንን ከክርስቶስ ጋር በእምነት ሰቅለን በመግደል÷ የምንቀብርበትንና በዐዲስ ኑሮ ለመመላለስ ትንሣኤ ልቡና የምንነሣበትን የማይታይ ክንውን የምንመሰክርበት ሥርዐት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል:: ምእመኑ ለመጠመቅ ወደ ውሃው ሲገባ ከክርስቶስ ጋር መሞቱን (በሞቱ መተባበሩን) መመስከሩ ነው:: ከውሃው ሲወጣ ደግሞ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ እንደ ተነሣ ሁሉ÷ እርሱም ከእርሱ ጋር በዐዲስ ሕይወት ለመመላለስ መነሣቱን ያውጃል፤ (ሮሜ 6÷4-5፤ ቈላ. 2÷12)::

የቤተ ክርስቲያናችን የቀኖና መጽሐፍ የሆነው ፍትሐ ነገሥት በውሃ የምንጠመቅበት ዐላማ ምን እንደሆነ ሲያስረዳ: -

> «ወተጠምቆትነሰ በማይ ውእቱ ተሳትፎትነ በሞተ ክርስቶስ፤ ወዕርገትነሂ እምነ ማይ ካዕበ ውእቱ አምሳለ ተንሥኦትነ ምስሌሁ::»
>
> ትርጓሜ: - «በውሃ መጠመቃችን በክርስቶስ ሞት አንድ መሆናችን ነው፤ ከውሃውም መውጣታችን ከእርሱ ጋር የመነሣታችን ምሳሌ ነው::» ይላል፤ (አንቀጽ 3 ቍጥር 27)::

ሌላው የመጠመቃችን ምክንያት የውሃ ጥምቀት ወደ ማኅበረ ምእመናን (ቤተ ክርስቲያን) አባልነት የምንቀላቀልበት ሥርዐት በመሆኑ ነው::

በኦሪት ዘመን በቃል ኪዳኑ ለመታቀፍና የማኅበረ እስራኤል ወገን ለመሆን መገዘር አስፈላጊ ነገር እንደነበረ ሁሉ÷ የጥምቀትን ሥርዐት መፈጸምም በዐዲስ ኪዳን አስፈላጊ ነገር ነው::

አንድ ሰው አምኖ ሲጠመቅ በቃል ኪዳኑ የመታቀፉን ማረጋገጫ ማኅተም ይቀበላል:: በምድር ላይ የእግዚአብሔር መንግሥት በሆነችው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም አባል ይሆናል:: እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን በኩል ከሚሰጠው የጸጋ ስጦታና መንፈሳዊ በረከት÷ እንዲሁም በአገልግሎት ሊሳተፍ ይችላል፤ (የሐዋ. ሥራ 2÷41-42፤ 8÷15-16፤ 9÷18-22፤ 19÷2-7)::

የጥምቀት ነገር ሲነሣ ሊጠመቅ የሚገባው ማነው? የሚለው የተለመደ ጥያቄም መነሣቱ አይቀርም:: በመሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚጠመቁ ሰዎች የዕድሜ ገደብ አላስቀመጠም፤ በመሆኑም በዚህ ሐሳብ ዙሪያ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የአመለካከት ልዩነት አለ:: አንዳንዶቹ አብያተ ክርስቲያናት ማር.16÷16ንና የመሳሰሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በመጥቀስ ሰው ሳያምን መጠመቅ እንደማይገባው ያስተምራሉ:: በመሆኑም የሕፃናትን መጠመቅ አይደግፉም:: ሌሎቹ ደግሞ ሌሎች ማስረጃዎችን በማቅረብ የሕፃናትን ጥምቀት ይቀበላሉ::

የሕፃናትን ጥምቀት ከሚቀበሉት አብያተ ክርስቲያናት መካከል የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ አንዷ ናት:: ቤተ ክርስቲያናችን ለዚህ አመለካከቷ የምታቀርበው ማስረጃ አለ:: ይኸውም በብሉይ ኪዳን የቃል ኪዳኑ ማኅተም የሆነው ግዝረት ማመን ለሚችሉ ዐዋቂዎች ብቻ ሳይሆን÷

ራሳቸውን ችለው ማመን ለማይችሉ የስምንት ቀን ሕፃናት ጭምር የተሰጠ መሆኑ፥ ሕፃናት በቃል ኪዳኑ መታቀፍ እንዳለባቸው ያስረዳል የሚል ነው።

አብርሃም የግዝረትን ምልክት የተቀበለው ካመነ በኋላ ሲሆን (ሮሜ 4፥9-11)፥ ልጁ ይስሐቅ ግን የተገዘረው በተወለደ በስምንተኛው ቀን ነው፤ (ዘፍ. 21፥4)። መቼም የስምንት ቀን ሕፃን ማመን እንደማይጠበቅበት አያከራክርም። ነገር ግን በዕድሜው በስሎ የሕይወቱን ኀላፊነት እስኪረከብ ድረስ፥ በአብርሃም ሞግዚትነት ሥር ያለ በመሆኑ በቃል ኪዳኑ ለመታቀፍ ሲባል ተገዘረ፤ በኋላም አመነ። ይሁን እንጂ ክፉና ደጉን መለየት ሲጀምር፥ አስቀድሞ የተቀበለውን የግዝረት ምልክት ባለማስተዋል አማኝ መሆኑ ቀርቶ የቃል ኪዳኑ ከሐዲ ሊሆን ይችላል። የወደደውን ምርጫ የሚከተለው ግን ካደገ በኋላ ነው።

ስለሆነም በብሉይ ኪዳን ሕፃናት የቃል ኪዳኑን ማኅተም በመቀበል የተስፋው ወራሾች ተደርገዋል፤ (ዘፍ. 17፥7)።

በዐዲስ ኪዳንም ከዚህ የተለየ ሁኔታ አይኖርም። ተስፋው በራሳቸው ውሳኔ ማመን ለሚችሉ ብቻ ሳይሆን ለልጆችም ጭምር ነው፤ (1ቆሮ. 7፥14፤ ገላ. 3፥29)። በዚሁ መሠረት በቤተ ክርስቲያናችን ሕፃናት በወላጆቻቸው ሞግዚትነት ተጠምቀው በቃል ኪዳኑ ይታቀፋሉ፤ (የሐዋ. ሥራ 2፥39፤ 16፥15፤ 33)።

ጥምቀት የማትደገም የማትሠለስ አንዲት በመሆኗም (ኤፌ. 4፥5)፥ ቤተ ክርስቲያናችን ሕፃናቱ ካደጉ በኋላ ዳግም ይጠመቁ አትልም። ያን ጊዜ የተጠመቁት ክርስቶስን በሞቱና በትንሣኤው ለመተባበር መሆኑን አምነው በዐዲስ ሕይወት እንዲመላለሱ ታስተምራለች።

ከቤተ ክርስቲያን አባቶች መካከል አንዱ የሆነው ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዲህ ብሏል፦ -

> «ወበከመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞተ በተሰቅሎ ከማሁ ንሕነኒ በጥምቀት፤ ወአኮ በሥጋ፥ አላ እምገቢረ ኀጢአት። ነጽር አ! ፍቁር ኀበ ሥርዐተ ሞት፤ ውእቱሰ ሞተ በሥጋነ ዘበእሲ ብሉይ፤ ወተንሥአ በሐዲስ አርአያ ዘኢይደሉ ለሞቱ። እንከሰኬ ይትፌቀድ በግብር ከመይጠመቁ በማየ ጥምቀት ውእቱ ዘያኤምር ኀበ ሞቱ። እስመ ተጠምቆ ኢኮነ ካልዐ ግብሩ፤ አላ ያኤምር ኀበ አሚኖቱ ለዘተጠምቀ ወኀበ ሞቱ ወተንሥኦቱ፤ እስመ ዘይጠመቅ ዳግመ ውእቱኬ ዘረስዐ ሀብተ ጸጋ ዘቀዲሙ፤ ወአበሰ አበሳ ምኑነ፤ ወዘይገብር ከመዝ ይከውን ከመ ዘየአምን በካልዕ ጥምቀት ወበእንተዝ ናስተሐይፅ በሠናይ ወንትዐቀብ።»
>
> ትርጓሜ፦ - «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል እንደ ሞተ፥ እንዲሁ እኛ በጥምቀት ሞትን። ሞትን ስንል ግን በሥጋ ሳይሆን ኀጢአትን ከመሥራት ነው። ወዳጄ ሆይ! ወደ ሞቱ ሥርዐት ታያለህን? እርሱ ግን አሮጌ ሰውነት ባለበት ሥጋችን ሞተና ለሞት ተገቢ በማይሆን በዐዲስ አርአያ ተነሣ። እንኪያስ መሞቱን አመልካች በሚሆን በውሃ ጥምቀት ይጠመቁ ዘንድ የግድ አስፈላጊ ነው። የመጠመቅ ተግባርም የሚጠመቀው ሰው እምነቱን ወደ ሞቱና መነሣቱ እንዲያደርግ የሚያመለክት ነው እንጂ ከዚህ ሌላ አይደለምና። ዳግመኛ የሚጠመቅ ሰው የመጀመሪያውን የጸጋ ስጦታ የረሳ፥ የተናቀውንም በደል የበደለ መሆኑ ነው። እንደዚህ ያለውን ሥራ የሚሠራም በሌላ ጥምቀት እንደሚያምን ይሆናል።» (ስምዐ ጽድቅ ብሔራዊ ከመሠረት ስብሐት ለአብ ገጽ 160)



ቤተ ክርስቲያናችን የሕፃናትን ጥምቀት በዚህ ሁኔታ ስትቀበል፥ ካደጉ በኋላ የሚመጡትን ግን አስተምራና አሳምና ታጠምቃቸዋለች።

## 2.3 ከሥርዐትነት ያላለፈ ጥምቀት

ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ጥምቀት ያላት አቋም ከላይ የተመለከትነው ነው:: አቋሟ በአቋም ደረጃ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ ያለው ቢሆንም፥ አፈጻጸሙ እያስገኘ ካለው ውጤት በመነሣት ከተመለከትን ግን ብዙ ሊስተካከሉ የሚገባቸው መሠረታዊ ነገሮች እንዳሉ ግልጽ ነው::

ሕፃናት እንዲጠመቁ ሲደረግ ነፍስ ዐውቀው የሕይወታቸውን ኀላፊነት እስኪረከቡ ድረስ፥ ኀላፊ ሆነውና በእግዚአብሔር ቃል ኮትኩተው ለሚያሳድጓቸው የክርስትና አባት (እናት) ወይም አበ ልጅ ይሰጣሉ:: ይህም ለሚጠመቁ ሕፃናት መንፈሳዊ እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ቤተ ክርስቲያናችን የሠራችውን መልካም ሥርዐት ያሳያል::

በዚህ ረገድ ቤተ ክርስቲያናችን አሁን የምትገኝበትን ሁኔታ ካየን ግን፥ ሥርዐቱ በሥርዐትነት ከመቀመጡ በቀር እየተሠራበት አይገኝም:: የሥርዐቱ መንፈሳዊ አገልግሎትም ቀርቷል ለማለት ያስደፍራል:: ለምሳሌ: - ለሕፃናቱ የክርስትና አባት (እናት) የሚሆኑት ሰዎች፥ በክርስትና አባትነታቸው ሕፃኑን ትምህርተ ሃይማኖት እያስተማሩ ለማሳደግ በቤተ ክርስቲያን ፊት የገቡትን ቃል ሲፈጽሙ አይታይም:: ለዚህም ብዙ ምክንያቶች አሉ:: ዋናው ግን ራሳቸው የክርስትና አባቶች (እናቶች) እንኳን ለክርስትና ልጃቸው የሚተርፍ ቀርቶ፥ ለራሳቸውም የሚበቃ የእግዚአብሔር ቃል ዕውቀትና የተለወጠ መንፈሳዊ ሕይወት የሌላቸው መሆኑ ነው:: ከዚህ የተነሣም በልማድ የገቡትን ቃል አይፈጽሙም:: የተረከቡትንም መንፈሳዊ ዐደራ በኀላፊነት አይወጡም:: እንዲያውም የክርስትና አባትነቱን ከሕፃኑ ቤተሰቦች ጋር ለመቀራረብና ሥጋዊ ዝምድናን ለማጠናከር ዐላማ ብቻ ይጠቀሙበታል::

እንግዲህ ከመንፈሳዊ ነገር ርቆ የሚያድገው ሕፃን የሕይወቱን ኀላፊነት መረከብ ሲጀምር፥ ሥርዐት ከመፈጸም በቀር ያገኘው አንዳችም መንፈሳዊ ነገር ባለመኖሩ፥ የሕይወት ለውጥ ሳያደርግ፥ በእግዚአብሔር ቃልና በቅዱስ መንፈሱ ዳግም ሳይወለድ (ዮሐ. 1፥12-13፤ 3፥5-6፤ 1ጴጥ. 1፥23፤ ያዕ. 1፥21)፥ የስም ብቻ ክርስቲያን ሆኖ ቀሪ ዘመኑን ያሳልፋል::

ቤተ ክርስቲያናችን እንደዚህ ያሉ ብዙ አባላት እንዳሏት ይታወቃል:: ደግሞም በውሃ ከመጠመቅ በኋላ በእግዚአብሔር ቃልና በቅዱስ መንፈሱ አማካይነት፥ ዳግም የመወለድን መንፈስ አግኝተውና ሕይወታቸው ተለውጦ የሚኖሩ ምእመናንም እንዳሉ ፈጽሞ አይካድም:: ከሚበዙቱ ሕይወት አንጻር ሲታይ ግን፥ ጥምቀት መንፈሳዊ ዐላማው ተዘንግቶ እንደሚፈጸም እንደ አንድ ሥርዐት ብቻ እየተቈጠረ ነው::

ደጋግመን እንደተመለከትነው በዐይን በሚታይ የጥምቀት ሥርዐት የምንመሰክረው፥ በሕይወታችን የተከናወነውን የማይታይ የሕይወት ለውጥ ነው:: ይኸውም በክርስቶስ በማመናችን የኀጢአታችንን ስርየት መቀበላችንን (የሐዋ. ሥራ 10፥43፤ 22፥16፤ ቲቶ3፥5)፥ የልብ ለውጥ ማግኘታችንንና (ማር. 1፥4-5፤ ሉቃ. 3፥7-14፤ 1ጴጥ. 3፥18-22)፥ ከክርስቶስ ጋር በሞቱና በትንሣኤው መተባበራችንን ነው፤ (1ቆሮ. 10፥2፤ ገላ. 3፥27፤ ሮሜ6፥3-4)::



ሰው ከማመኑ አስቀድሞም ሆነ ካመነ በኋላ ቢጠመቅ፥ እነዚህ ለውጦች በሕይወቱ ካልተከናወኑና መንፈሳዊ ፍሬን ካላፈራ መጠመቁ ብቻውን ምንም አይረባውም:: ወይም ቃል ኪዳኑን ሳይጠብቁ የቃል ኪዳኑ ምልክት የሆነውን ግዝረትን እንደተቀበሉት አይሁድ መሆን ነው:: እንደዚህ ያለው መገዘር ለእነርሱ እንዳልጠቀማቸው ሁሉ፥ ሥርዐት ለማድረስ ተብሎ ብቻ የሚፈጸም ጥምቀትም እንዲሁ አይጠቅምም::

በዐዲስ ኪዳን ዘመን ላይ ሆነው የብሉይ ኪዳንን የእምነት ማኅተም ለመጠቀም የሚዳዳቸው ወገኖች ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ እንደ ነበሩ ይታወቃል:: ዛሬም ባለማወቅ ግዝረት እንደ ልማድ ሳይሆን እንደ ሕግ መጠበቅ አለበት የሚሉ አይጠፉም:: ነገር ግን ግዝረት በዐዲስ ኪዳን በእምነት ማኅተምነት ለክርስቲያኖች አያገለግልም፤ (1ቆሮ. 7፥18-19፤ ገላ. 5፥6፤ 6፥15)::

መቼም በአንድ ሰነድ ላይ የተለየ ምክንያት ከሌለ በቀር አሁን ሕጋዊነት ያለው ማኅተም እንጂ፥ የቀድሞውና አሁን በሥራ ላይ የማይውለው ማኅተም ቢደረግበት ተቀባይነት አይኖረውም:: ወይም ደግሞ በማኅተምነት ያገለግለኛል በሚል ከዐዲሱ ማኅተም ጋር ቢታተም፥ «ዐዲሱ ማኅተም ብቻ በቂ ነው፤ ለምን አሮጌውን ጨምረህ አደረግህ?» የሚል ጥያቄ አስነሥቶ አላዋቂ ያሰኛል::

አስተምህሮዋን ጠልቀው ያልተረዱ ወገኖች ባያስተውሉትም፥ ቤተ ክርስቲያናችን ግዝረትን እንደ አይሁድ የሚጠበቅ ሕግ አድርጋ ሳይሆን በልማድ የሚፈጸም ሥርዐት መሆኑን ታምናለች::

> «ኢንትገዘር እንከ ከመ አይሁድ፤ ነአምር ከመ መጽአ ዘይፌጽም አሪተ ወነቢያተ፤ ዘኪያሁ ይሴፈዉ ምጽአቶ ኵሎሙ አሕዛብ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘሠረጸ እም ይሁዳ ወእምሥርወ እሴይ::»
>
> ትርጓሜ: - «አሕዛብ ሁሉ መምጣቱን በተስፋ ሲጠባበቁት የነበሩት፥ ከነገደ ይሁዳና ከእሴይ ሥር የተገኘው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ መጣ እናውቃለንና፥ ከእንግዲህ ወዲህ እንደ አይሁድ አንገዘር::» (አመክንዮ ዘሐዋርያት)::

# ክፍል 3 - ቤዛ

## 3.1 በብሉይ ኪዳን ለሕዝቡ የተከፈለ ቤዛ

በሌላ የተያዘን ወይም የተወሰደን ንብረት መልሶ የራስ ለማድረግ ዋጋ መክፈል የግድ ነው። ለዚህ ጉዳይ የሚከፈለው ዋጋ፥ ካሳ፥ ወይም ለውጥ፥ ቤዛ ይባላል።

የአብርሃም ዘር የሆኑት ዕብራውያን ለ400 ዓመታት ያህል ባሮች ሆነው ከተገዙላቸው ከግብጻውያን የአገዛዝ ቀንበር ነጻ እንዲወጡና፥ ባርነታቸው ቀርቶ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲሆኑ፥ እግዚአብሔር ቤዛ መስጠት ነበረበት። በመሆኑም አስጨናቂዎቻቸውን በሞተ በኩር በቀጣበት በዚያ ሌሊት፥ አጥፊው ሕዝቡን እንዳያጠፋ በእያንዳንዱ እስራኤላዊ ቤት ነውር የሌለበት የአንድ ዓመት ተባት ጠቦት እንዲታረድና፥ ደሙ በቤታቸው በር መቃንና ጉበን ላይ እንዲቀባ በማድረግ የእስራኤልን በኩራት ከአጥፊው እጅ አዳነ፤ (ዘፀ. 12፥7፤ 12-13፤ 21-23)። ስለዚህም ከሰውም ሆነ ከእንስሳ ማሕፀንን የሚከፍት በኩር ሁሉ በዋጋ ተገዝቷልና እግዚአብሔር የኔ ነው አለ፤ (ዘፀ. 13፥1)።

ምንጊዜም እንስሳት ሲሠዉ ወይም የመሥዋዕት ደም ሲፈስ፥ ሌላው በሕይወት ይኖር ዘንድ የአንዱ ስለሌላው ምትክ ሆኖ መሞትን ያመለክታል። ኀጢአቱም በፈሰሰው ደም መሠረት ይሰረያል። ደም ሳይፈስ ስርየት እንደማይኖር ተጽፎአልና፤ (ዘሌ. 5፥17-19፤ ዕብ. 9፥22፤ዘሌ. 17፥11)።

ለሚመጣው ዋና ነገር ጥላ በሆነው በፋሲካው በግ እግዚአብሔር ሕዝቡን ተቤዥቶታል። ሕዝቡ አንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ሆኗልና፥ ዋጋም ተከፍሎለታልና ከእንግዲህ ወዲህ የእግዚአብሔር የግሉ ንብረት ነው። ስለዚህም በብዙ ስፍራ እግዚአብሔር ሕዝቡን «ተቤዥቼሃለሁ፤ አንተ የኔ ነህ።» በማለት ባለንብረትነቱን ይገልጻል፤ (ኢሳ. 35፥10፤ 41፥14፤ 43፥1፤14፤ 52፥3፤ 62፥12፤ 63፥9)።

ቤዛ የተሰጠለት ሕዝብም የሌላ ልሁን ቢል ከቶ የማይሆን ነው፤ እንቢ ብሎ በተቤዠው አምላክ በእግዚአብሔር ላይ ቢያምፅ እንኳ፥ በእግዚአብሔር ሥር ሆኖ ተገቢውን ቅጣት ይቀበላል እንጂ የሌላ ሊሆን ከቶ አይችልም። በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ የታየውም ይኸው ነው።

በድንቅና በተአምራት ከባርነት ቤት ከግብጽ ነጻ ያወጣቸውን የአምላካቸውን ትድግና ረስተው ብዙ ጊዜ በማጉረምረም፥ «ኑ! አለቃ ሾመን ወደ ግብጽ እንመለስ» እስከ ማለት ደርሰው (ዘኁ. 14፥4) ባርነትን ዳግም ቢናፍቁም፥ አንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ሆነዋልና ቢመኙትም እንደገና ተመልሰው የግብጻውያን መሆን አልቻሉም። ስለዚህ እግዚአብሔር በየጊዜው እንደ ዐመፃቸውና እልከኛ ልባቸው በሥሩ አድርጎ በመቅጣት ያን ሕዝብ በምድረ በዳ ወድቆ ወድቆ እንዲቀር አደረገ፤ (ዘኁ. 14፥2፤ 22-24፤ 26-35፤ ዘዳ. 17፥16፤ መዝ. 94(95)፥8-11፤ ዕብ. 3፥16-19፤ 1ቆሮ. 10፥7-10)።



ከዚያም በኋላ ባሉት ዘመናት ትውልድ ዐልፎ ትውልድ ሲተካ፥ ብዙ ጊዜ እስራኤላውያን አምልኮተ እግዚአብሔርን ትተው ወደ አምልኮተ ጣዖት ፊታቸውን ሲመልሱ፥ ዘላለማዊ ንብረቱ ይሆኑ ዘንድ አንድ ጊዜ ተቤዥቷቸዋልና ስለ ሕዝቡ እግዚአብሔር ይቀና ነበር። ገንዘቡን ከፍሎ የገዛው ንብረቱ የሌላ ሲሆንበት የማይቀና ማን አለ? ስለዚህም እግዚአብሔር ጣዖትን በማምለክ ያስቀኑትን ሕዝቡን፥ ሕዝቡ ባልሆኑት በሌሎች በማስቀናትና በእነርሱ ላይ በጠላትነት በማስነሣት ሕዝቡን ወደ ራሱ ይመልሳል። ይህ ሁኔታ በተለይም በዘመነ መሳፍንት ተደጋግሞ የታየ ክሥተት እንደነበረ የመጽሐፈ መሳፍንትን ታሪክ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል።

ሕዝቡም በሠሩት ኀጢአት ለቅጣት ሲዳረጉ ሌላ ተስፋ አልነበራቸውም፤ ወደ ተቤዣቸው ጌታ በንስሐ ይመለሳሉ፤ በበደላቸውም ምክንያት ቢሰብራቸውም የሚፈውሳቸው፥ ቢመታቸውም የሚጠግናቸው፥ እርሱ ብቻ መሆኑንና ለዘላለምም እንደማይጥላቸው ምንጊዜም አይረሱትም ነበር፤ (ሆሴ. 6፥1-3፤ ሰቈ. ኤር. 3፥31-32፤ 40-41)።

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔርም እንዲሁ፥ ቢበድሉትም ለዘላለም አልጣላቸውም። በምሕረት ዐይኑ ተመልክቶ ከወደቁበት በማንሣትና ተስፋቸውን በማደስ እንደገና ያቆማቸው ነበር፤ (ኢሳ. 54፥4-10፤ 49፥14-16፤ መዝ. 102(103)፥9)።

የእግዚአብሔርና የሕዝቡ ግንኙነት ምንጊዜም ቢሆን፥ በአባትና በልጅ መካከል እንዳለው ግንኙነት ያለ ነው፤ (ዘጸ. 4፥22፤ ኢሳ. 63፥16፤ 64፥8፤ ሆሴ. 11፥1)።

አባት ልጁ ምን ቢያጠፋ ይቀጣዋል እንጂ ከእንግዲህ እኔ አባትህ አይደለሁም፤ አንተም ልጄ አይደለህም ሊለው ከቶ አይችልም። ልጅም አባቱ የቱንም ያህል ተቈጥቶ ቢቀጣው በዚህ ተቀይሞ ከእንግዲህ አንተ አባቴ አይደለህም፤ እኔም ልጅህ አይደለሁም ለማለት አይችልም፤ ቢል እንኳ አባትነትና ልጅነት የተሳሰረበትን ገመድ ሊበጥስ ፈጽሞ አይችልም።

እግዚአብሔርና ሕዝቡ እንደ አባትና ልጅ በማይበጠስ ጽኑ የፍቅር ገመድ ተሳስረዋል። እናም እግዚአብሔር ቤዛ ሰጥቶ የግሉ ያደረጋቸውን ሕዝቡን፥ ማንኛውም ያልገዛቸው እንዲነዳቸውና እንዲገዛቸው የፈቀደበት ጊዜ ፈጽሞ የለም። እርሱ በዋጋ የገዛቸው የእርሱ ብቻ እንዲሆኑ፤ ለእርሱ ብቻም እንዲገዙ ነው።

ከላይ እንደተመለከትነው እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ከሕዝቡ ጋር በነበረው ታሪክ፥ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር ያጣላቸው ዋናውና ግንባር ቀደሙ ምክንያት የተቤዣቸውን ጌታ ትተው ለሌሎች አማልክት መገዛታቸው ነው፤ (ዘዳ. 32፥15-20)።

ዛሬም በዐዲስ ኪዳን በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ያለውን ግንኙነት ሊያበላሽ የሚችለው ትልቁ ዕንቅፋት ይኸው ነው።

## 3.2 በዐዲስ ኪዳን ለሕዝቡ የተከፈለ ቤዛ

ሕዝበ እስራኤል ከግብጽ ባርነት የተዋጁበት የፋሲካው በግ ነውር የሌለበት ንጹሕ በመሆኑ÷ በዚያ ሌሊት ይታረድና ይሞት ዘንድ ተገቢው አልነበረም፡፡ ይሁን እንጂ ሞት የተገባው ሌላው በሕይወት እንዲኖር ካስፈለገ÷ አስቀድሞ ሞት ያልተገባው ስለእርሱ ምትክ ሆኖ ይሞትለት ዘንድ የግድ ነው፡፡

አጥፊው ሞተ በኵር የግብጻውያንን በኵራት ሲቀጥፍ÷ የእስራኤልንም እንዳይደግም ምትካቸው ሆኖ የሚሞት ንጹሕ ቤዛ በማስፈለጉ÷ ሞት አይገባው የነበረ ነውር አልባ ንጹሕ በግ እንዲሞትና÷ ሞት የተገባቸው በኵራተ እስራኤል በሕይወት እንዲኖሩ የሚጠበቅ ጉዳይ በመሆኑ÷ የበጉ ደም በያንዳንዱ እስራኤላዊ ቤት በበሩ መቃንና ጉበን ላይ ተቀባ፡፡ የንጹሑ በግ ደም በበራቸው መቃንና ጉበን ላይ መታየቱ የበጉን «ለያንዳንዱ ቤዛ ሆኛለሁና እነርሱ ነጻ ናቸው፡፡» የሚል ድምፅ አልባ ምስክርነቱንና ፋሲካነቱን አረጋግጧል፤ (ዘፀ. 12÷13)፡፡

የእስራኤል በኵራት ከግብጽ የባርነት ኑሮ የተቤዡበት የፋሲካው በግ ለክርስቶስ ጥላና ምሳሌ ነበር፡፡ ለዚህም ሐዋርያው ብፁዕ ጳውሎስ የኛ ፋሲካ ክርስቶስ በመታረዱ÷ የቀድሞው ጥላና ምሳሌ የነበረው በግ÷ የዓለምን ኀጢአት ለማስወገድ በመጣውና የእግዚአብሔር በግ በተሰኘው በክርስቶስ ፋሲካነት መተካቱን አብሥሮናል፤ (1ቆሮ. 5÷7፤ ዮሐ. 1÷29፤ 36፤ ኢሳ. 53÷7)፡፡

በአንዱ ሰው በአዳም በደል ምክንያት ወደ ዓለም የገባው ኀጢአትና ውጤቱ ሞት÷ የሰውን ዘር በሙሉ ስላዳረሰ ሁሉን በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ገዛ፡፡ በዚህ ባርነት ውስጥ ያሉትን ነጻ ማውጣት የሚችል በዚህ ባርነት ያልተያዘ÷ ራሱ ነጻ የሆነ ሰው ነው፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው አንድስ እንኳ ጻድቅ ስለታጣና ሁሉም የሰው ዘር የእግዚአብሔር ክብር ስለ ጎደለው (ሮሜ 3÷11፤23)÷ አንዱ ሰው እንደ እርሱ ያለውን ሌላውን ሰው ሊያድን ከቶ አልቻለም፤ (መዝ. 49(50)÷7-8)፡፡ መሞት ለተፈረደበት ለሰው ዘር በሙሉ በቂ የሆነ ቤዛ ሰጥቶም ሊቤዥ የሚችል ፍጡር አልተገኘም፤ (መዝ. 49(50)÷7፤ ኢሳ. 59÷15-16፤ ሮሜ 7÷24)፡፡ ሕግም እንዲሁ ለማዳን አልተቻለውም፤ (ሮሜ 8÷3)፡፡

ስለዚህ እግዚአብሔር ሰውን ከኀጢአት ባርነትና ከሞት ፍርሀት ነጻ የሚያወጣበትንና የራሱ ንብረት የሚያደርግበትን ቤዛ ያዘጋጅ ዘንድ በማስፈለጉ÷ አንድያ ልጁን ልክ ሰው እንዲሆንና ለሰውና ለሕግ ያልተቻለውን እንዲፈጽም÷ ብሎም ምትክ ሆኖ ስለ ሰዎች እንዲሞት አደረገ፤ (ዕብ. 2÷14-15፤ ሮሜ 8÷3፤5)፡፡

እኛ በፈቃዳችን ለኀጢአትና ለዲያብሎስ ያለ ዋጋ ከተሸጥንበት እግዚአብሔር ልጁን ቤዛ ሰጥቶ ዋጀን፡፡ ይህ ስለ እኛ መቤዠት የተከፈለው ዋጋ በሌላ ተመጣጣኝ ዋጋ ሊተመንና ሊመዘን የማይችል ነው፡፡ ቢቻልማ ኖሮ ሰው ለነፍሱ የሚሰጠውን ቤዛ ማዘጋጀት በቻለና ነፍሱን ባለው ሀብት በተቤዠ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ አይቻልምና የእግዚአብሔር ቃል «ሰውስ ስለ



ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?» ሲል ይጠይቃል፡፡ ይህም ሰው በራሱም ሆነ አለኝ በሚለው ነገር÷ ሕይወቱን ከኀጢአት ባርነትና ከሞት ፍርሀት ነጻ ሊያወጣ አለመቻሉን ጠቋሚ ነው፤ (ማር. 8 ÷36-37)፡፡

ከዚህ የምንረዳው የሰውን ነፍስ ለመቤዠት የተጠየቀው ዋጋ እጅግ ታላቅ የሆነና በሰው ወይም ከሰው ሊገኝ የማይችል መሆኑን ነው፡፡ ሐዋርያውም ይህንን ሊያስረዳ÷ «ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር÷ በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን÷ ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደተዋጃችሁ ታውቃላችሁ፡፡» ብሏል፤ (1ጴጥ. 1÷18-19)፡፡ ይህም ቤዛነታችን የተከናወነው በደሙ ብቻ መሆኑን ያሳያል፤ (ኤፌ. 1÷7)፡፡

የተከፈለልንን ዋጋ ታላቅነት ስናስብ÷ የዋጋውን ታላቅነት ብቻ ሳይሆን÷ ይህንን ታላቅ ዋጋ እንዲከፈልልን ያደረገውን የበደላችንን ታላቅነትም ጭምር መሆን ይኖርበታል፡፡ እንደገናም በዚህ ውስጥ እኛ ለእርሱ የነበረን ጠላትነት ያላገደውን÷ ኀጢአተኝነታችንና ድካማችን ያላደፈረሱትን÷ ለሚወደውና ለአንድ ልጁ እስካለመራራት ያደረሰውን ጥልቅ ፍቅር እናስብበታለን፤ (ሮሜ 5÷6፤ 8፤ 10፤ 8÷32፤ ኤፌ. 2÷5)፡፡

እግዚአብሔር ቤዛ የሰጠላቸውና በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የእግዚአብሔር ገንዘቦች መሆናቸውን አምነው የተቀበሉ ሁሉ÷ ከኵነኔ ነጻ የሆኑ የእግዚአብሔር ብቻ ናቸው፤ (ሮሜ 8÷1)፡፡ ከዚህ በኋላ የሌላ መሆን ቀርቶ የራሳቸውም መሆን አይችሉም፤ (1ቆሮ. 7÷23፤ 6÷20፤ ሮሜ 14÷7-8፤ 2ቆሮ. 5÷15)፡፡

የቀደሙት እስራኤል ባርነትን ፈልገው አለቃ ሾመን ወደ ግብጽ እንመለስ በማለት እንዳመፁ ሁሉ÷ በክርስቶስ ደም የተዋጁት ክርስቲያኖችም በእግዚአብሔር ላይ ዐምፀው የሌላ እንሁን ቢሉ ፈጽሞ የማይሞከር ነው፡፡ በዐመፃቸው ከገፉም በሥሩ ሆነው በአስፈሪው የእግዚአብሔር እጅ ይቀጣሉ እንጂ የሌላ ባርያ አይሆኑም፡፡ ወይም ከዓለም ጋር አይኰነኑም፤ (1ቆሮ. 11÷32)፡፡ ጌታ «አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፤ ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም፡፡» በማለት በክርስቶስ ደም የተዋጁ የክርስቲያኖችን ዋስትና አረጋግጧል፤ (ዮሐ. 6÷37)፡፡

ነገር ግን በትክክል በአብ ተስበው ወደ ክርስቶስ ያልመጡትን÷ ይህ ዋስትና ዋስትናቸው አይሆንላቸውም፡፡ ስለዚህ የአምልኮን መልክ ይዘው ዐውቀናል÷ እውነትን ተረድተናል እያሉ በተረዱት እውነት መሠረት የማይኖሩትን የስም ክርስቲያኖች÷ እዚህ ስፍራ ውስጥ ለማስገባት በመሞከር÷ በኛ የተሳሳተ ግንዛቤ የእግዚአብሔርን አሠራር የተበላሸ አድርገን እንዳንቈጥር ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባናል፡፡

እግዚአብሔር በእኛ ሥራ ሳይሆን በልጁ በክርስቶስ ደም ያጸደቀን÷ ለሌላ ሳይሆን የዘላለምን ሕይወት እንድናገኝና÷

እግዚአብሔር አስቀድሞ የዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ ነው፤ (ኤፌ. 2÷10)። በክርስቶስ አምኖ የጸደቀ ሰው የመጽደቁ ማረጋገጫ ይኸው ብቻ ነው።

አንባቢ ሆይ! ይህ እንዴት ያለ አስደናቂ ነገር ነው! እንግዲህ በውድ ዋጋ ተገዝተሃልና÷ ከእንግዲህ የራስህ ወይም የሌላው መሆን አትችልም። በዋጋ የመገዛትህና የእግዚአብሔር መሆንህ የሚለካበት መስፈርቱ ግን ከላይ እንዳየነው÷ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ያለህ ዕውቀትና የስም ብቻ የሆነው ክርስትናህ ሳይሆን በሁለንተናህ እግዚአብሔርን ማክበርና ማስከበር መቻልህ ነው።



## 3.3 ከእግዚአብሔር ያልሆኑ ቤዛዎች

በብሉይ ኪዳን ለክርስቶስ ምሳሌ የነበረው የፋሲካው በግ÷ በዐዲስ ኪዳን ደግሞ ራሱ ክርስቶስ ቤዛ ሆኖ በመስጠቱ የእግዚአብሔር ሕዝብ ድኗል። እግዚአብሔር በሁለቱም ዘመናት የሰጠው ቤዛ ይኸው ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ለሰው ቤዛ ይሰጥ ዘንድ ያስፈለገው÷ ሰው ራሱን ለማዳን ስለ ነፍሱ የሚሰጠው ቤዛ ባለመኖሩ ነው። አሁን ያለውን ሰው የተመለከትን እንደሆነም ከቀደሙት በምንም የማይሻልና ስለ ነፍሱ ቤዛ መስጠት የማይችል ነው። ስለዚህ ድካሙን የተረዳለት አምላኩ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ዘላለማዊ ቤዛ አድርጎ በመስጠት ስለ ድኅነቱ ሌላ ተጨማሪ ነገር የማያስፈልገው በቂ ዋጋ ከፍሏል።

በቤተ ክርስቲያናችን ይህን ርቱዕ ሃይማኖት የሚያጣምም ኑፋቄ ሥር እየሰደደ ከመጣ ዘመናት ተቈጥረዋል። እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ከፍጥረት መዋጮ እንደ ጠየቀ በማስመሰል÷ ከክርስቶስ በተጨማሪ ሌሎች ቤዛዎችን በማቆም ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሊዋጁለት ላይ ታች የሚሉ እንዳሉም ግልጽ ነው።

እነዚህ ክፍሎች ከልማድና የመዳንን ዕውቀት ከማጣት የተነሣ «እግዚአብሔር እርዱኝ እረዳችኋለሁ ብሏል።» እያሉ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል አስመስለው ለሚናገሩ አንዳንድ ባልቴቶች ሌላ ገጽታዎች ናቸው። የእግዚአብሔርን ቤዛ ትተው÷ ወይም የኛን ቤዛ ካላከልንበት የእግዚአብሔር ቤዛ ብቻውን ፋይዳ አይኖረውም ብለው÷ የራሳቸውን ቤዛ ሊያቆሙ የሚፈልጉ ሁሉ ለእነርሱ ይመስላቸው ይሆናል እንጂ መቼውንም ቢሆን በዚህ መንገድ የእግዚአብሔር መሆን አይቻልም።

በቤተ ክርስቲያናችን ከክርስቶስ ሌላ ተጨማሪ ሆነው በሰዎች ከቆሙት ቤዛዎች መካከል ጎላ ብለው የሚታዩት እመቤታችን ቅድስት ማርያምና ጌታ የተሰቀለበት መስቀል ናቸው። በተለይም ለእመቤታችን «ቤዛዊተ ዓለም» የሚል ቅጽል ተሰጥቷት በተለያዩ ድርሰቶች ውስጥ እናነባለን። ለምሳሌ «ማርያም ቤዛ ብዙኀን÷ ሕይወተ ኮነት ለኵሉ ዓለም፤ ፍሥሓነ ለእለ አመነ።» «የብዙዎች ቤዛ ማርያም ለዓለሙ ሁሉ ሕይወት ሆነች፤ ላመንን ለእኛ ተድላ ደስታችን ናት።» (የመጋቢት ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዚቅ)። ይህም የሷን ቤዛነት በክርስቶስ ላይ ከመጨመር ያለፈና የክርስቶስን ስፍራ ለእሷ በቀጥታ የሰጠ ድርሰት ነው። እንዲህ የሚሉት መናፍቃን እሷ ለኛ ቤዛ ሆና የተሰጠችበትን ወቅት÷ የሷን ቤዛነት የጠየቀውን የኀጢአታችንን ዐይነትና ለዚህ ኀጢአታችን በምን ዐይነት ሁኔታ ቤዛ እንደ ሆነች÷ ወይም መቼ ተሰቅላ እንደሞተችልን እውነትነት ያለውን ማስረጃ ለማቅረብ አይችሉም።

ያልሆነችውን ሆናለች እየተባለ በስሟ ብዙ ቢዋሽባትም÷ እመቤታችን ግን አስቀድማ እኔ የዓለም ቤዛ ነኝ ብላ የተናገረችበት ጊዜና የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ፈጽሞ የለም። ወደ እርሷ መጥታ ስላምታ ስታቀርብላት የማርያምን የሰላምታዋን ድምፅ በሰማችበት ጊዜ÷ በማሕፀኗ የነበረው ፅንስ (ዮሐንስ) ሲዘል÷ በሷም መንፈስ ቅዱስ

ሲሞላባት ኤልሳቤጥ የሰጠችው ምስክርነትም «የጌታዬ እናት» የሚል ነበር እንጂ፥ «ቤዛዊተ ዓለም» ስትል አልጠራቻትም፤ (ሉቃ. 1፥40-45)።

መልአኩ ገብርኤልም ባበሠራት ጊዜ ቤዛዊተ ዓለም መሆኗን የሚጠቁም ቃል ፈጽሞ አልተናገረም፤ (ሉቃ. 1፥28-35)። ይልቁንም በሌላ ስፍራ የጌታ መልአክ ለዮሴፍ በሕልም እንደነገረው፥ ድንግል ማርያም ሳትሆን ከእሷ የሚወለደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሕዝቡ ቤዛ መሆኑን አስረድቷል፤ (ማቴ. 1፥21)።

ቅድስት ድንግል ማርያምም በመንፈስ ቅዱስ የሆነውን የኤልሳቤጥን ምስክርነት ተከትላ፥ የዓለሙ ሁሉ ቤዛ የእሷም ቤዛ መሆኑን «መድኃኒቴ» ብላው በመጥራት ቤዛ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን አረጋገጠች፤ (ሉቃ. 1፥46)።

መቼም እግዚአብሔር በእርሷ ታላቅ ሥራ ከማድረጉ የተነሣ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት እንደሚላት መናገሯ፥ ቤዛዊተ ዓለም የሚያሰኝ አንድምታ የለውም። ስለዚህ እሷንም ሆነ ሌሎቹን ቅዱሳን ቤዛችን አድርጎ ማቆም ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ በመሆኑ፥ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል መሠረት አድርገውና ጠቅሰው የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት በእውነተኛው ገጽታቸው ኑፋቄውን ያወግዙታል።

ኑፋቄውን ከድርሳነ ሚካኤል እንጥቀስ: - «... በዚህ ዓለም ሳለች ዋስ ጠበቃ ያላዘጋጀች ሰውነት፥ በሞተች ጊዜ በሰማይ የሚዋሳት አታገኝም። ... በሕይወት ባለንበት ጊዜ ዋስ ጠበቃ ካላዘጋጀን፥ በሰማይ የሚዋሰን አናገኝም። መላእክትን፥ ጻድቃን ሰማዕታትን በዚህ ዓለም ካላከበርናቸውና ሰውነታችንን ለእነርሱ ዐደራ ካላስጠበቅናቸው፥ <u>በፍርድ አደባባይ የሚዋሰን ወይም ቤዛ ሆኖ የሚያልፍልን የለም። በልዑል እግዚአብሔር ፊት ነፍሳችንን ለማዳን ችሎታ ያለው የለምና</u>።» (ድር. ዘጥቅምት ቍ. 30)

ይህ የድርሳነ ሚካኤል ክፍል የክርስቶስን ቤዛነት ገደል የሚጨምር፥ ክርስቶስ የዐዲስ ኪዳን ዋስ (ዕብ. 7፥22) መሆኑንም የሚያስተባብል፥ በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በነፍሱ ምስክር እንዳለው የሚናገረውን የእግዚአብሔር ቃልም ፊት ለፊት የሚቃወም ክሕደት መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው፤ (1ዮሐ. 5፥12)።

ይህን ክሕደት የሚያወግዙ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ደግሞ እንዲህ ይላሉ: -

> «ወሕይወትነሂ ኢኮነ በሰብእ፤ ወኢእምነትነ በሰብእ፤ እስመ ይቤ መጽሐፍ ይኩን ርጉመ ዘይትአመን በዕጓለ እመሕያው፤ ... ወኢክህለ መኑሂ እምኵሉ ዘኮነ እም አዳም እስከ ይእዜ ይግበር መድኀኒተ ዘእንበለ እግዚአብሔር ቃል ከመኢይኩን ተስፋነ ሙሱነ።» (መዝ. 59፥11፤ ኤር. 17፥5)።
>
> ትርጓሜ: - «ድኅነታችንም በዕሩቅ ብእሲ አይደለም፤ እምነታችንም በዕሩቅ ብእሲ አይደለም፤ መጽሐፍ በዕሩቅ ብእሲ የሚያምን ርጉም ይኹን ብሏልና። ... ከአዳምም ጀምሮ እስከ ዛሬ ከተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ማንም ማን ሊያድነን አልቻለም፤ ከእግዚአብሔር ቃል



> (ከኢየሱስ ክርስቶስ) በቀር፤ በሰው ቢሆን አለኝታችን ከንቱ እንዳይሆን።» (ሃይ. አበ. ም. 58 ክፍ. 13 ቍ. 46፤49)።

ከዚህ የአባቶች ምስክርነት፥ የኛ አዳኝ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ሆኖ ቢመጣም፥ አለኝታችን ከንቱ እንዳይሆን ዕሩቅ ብእሲ (ሰው ብቻ) ሆኖ እንዳልመጣና ፍጹም አምላክ እንደሆነም እንረዳለን። በሰውነቱ ቤዛ ሆኖ ሲሰጥልን በአምላክነቱ የሚያድነን ሆኗልና።

> ሊቁ ኤጲፋንዮስ ይህን ሲያስረዳ: - «ወበእንተ ዝንቱ እግዚእ መጽአ ወተሠገወ እም ዕጓለ እመሕያው፤ ወኮነ እግዚአብሔር ቃል ሰብአ፥ ከመ የሀበነ መድኀኒተ በመለኮቱ፥ ወይሙት ቤዛነ በትስብእቱ።»
>
> ትርጓሜ: - «... ጌታ ከወዲያ ዓለም ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከሰው ወገን ተወለደ፤ እግዚአብሔር ቃል ሰው ሆነ። አምላክ በመሆኑ ያድነን ዘንድ፥ ሰው በመሆኑም ቤዛ ሆኖ ይሞትልን ዘንድ።» ብሏል፤ (ሃይ. አበ. ም. 58 ክ.13 ቁ 50)።

ሌላው ኑፋቄ ደግሞ በመስቀሉ ላይ የተሰቀለውን ቤዛ ቸል ብለው የተሰቀለበትን ዕፅ (1ጴጥ. 2፥24) «ቤዛችን» በማለት የመሰየሙ ጉዳይ ነው።

ዐዲስ ኪዳን መስቀልን «መመኪያ፥ ጥልን መግደያ ወዘተ...» አድርጎ የሚያቀርብ ቢሆንም፥ እዚህ ላይ መስቀል የተባለው ክርስቶስ ስለኛ ድኅነት የተቀበለውን መከራ እንጂ የተሰቀለበትን ቍሳዊ ነገር አለመሆኑን ማስተዋል ይገባል፤ (ገላ. 6፥14፤ ኤፌ. 2፥16፤ ፊልጵ. 3፥18፤ ቈላ. 1፥20፤ 1ቆሮ. 1፥18)። ይህንንም ሊቃወንተ አርቶዶክስ በተረጐሙት የቅዱስ ጳውሎስ አንድምታ ላይ ለእነዚህ ጥቅሶች የተሰጣቸውን ትርጉም በመመልከት ለማረጋገጥ ይቻላል። «መስቀል» የሚለውን ቃል «መከራ መስቀሉ» ብለው ነው የተረጐሙት፤ በመስቀል ላይ የተቀበለው መከራ በማለት።

ለአምልኮተ ዕፀ መስቀል የቆሙ ወገኖች ግን ይህን እውነት ተጋፍተው መስቀል ኃይልነ፥ ጽንዕነ፥ ቤዛነ፥ መድኀኒተ ነፍስነ ወዘተ... በማለት የመከራ መስቀሉን ስፍራና ክብር፥ ክርስቶስ አንድ ጊዜ ለተሰቀለበት ብቻም ሳይሆን፥ እነርሱም በተለያየ መጠንና ቅርጽ ከተለያዩ ቍሳቍሶችና ማዕድናት ለቀረጹት የመስቀል ቅርጽ ሰጥተውት እናገኛለን። እንዲህ ማድረግ ግን በእግዚአብሔር ቃል የተከለከለ ነው፤ (ዘዳ. 27፥15)።

መቼም አእምሮ የጎደለው ካልሆነ በቀር፥ ሰዎች የሠሩት ግዑዝ የሆነ የእደ ጥበብ ውጤት ለኛ ቤዛ ሊሆን እንደማይችል ያውቃል። የኛ ቤዛ ሊሆን የሚችለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምትካችን ሆኖ የተቀበለው መከራ ብቻ ነው። ለዚህም የእግዚአብሔር ቃል «በመገረፉ ቍስል ተፈወሳችሁ።» ሲል የመከራ መስቀሉን ቤዛነት ያረጋግጥልናል፤ (1ጴጥ. 2፥25)።

ከድንግል ማርያምና ከመስቀል በቀርም ሌሎች: - በተለያዩ ቅዱሳን ስም የዝክር ድግስ መደገስ፥ ምጽዋት መመጽወት፥ ጾምና የመሳሰሉት ምግባራተ ሠናይም ለነፍስ ቤዛ እንደሚሆኑ ተቈጥረው እየተሠራባቸው ይገኛል።

በተለይም ከድግሱ የተቋደሱ ሁሉ መጨረሻ ላይ ሲመርቁ «የነፍስ ዋጋ ያድርግላችሁ» ማለታቸው ድግስ ደግሶ ማብላት የነፍስ ቤዛ ይሆናል ተብሎ ስለ ታመነ ነው። በብዙ ገድላትና ድርሳናት ውስጥ ሰው የቱንም ያህል ኀጢአተኛ ቢሆን በመላእክቱና በቅዱሳኑ ስም ዝክር ለመዘከር ደግሶ ካበላ፥ ወደ ሲኦል ቢጣል እንኳ መላእክቱ በክንፋቸው፥ ቅዱሳኑ በቃል ኪዳናቸው ወደ ገነት እንደሚያስገቡት በሰፊው ተጽፏል። ሕዝባችንም ዘወትር ይኸው ስለሚሰበክለት፥ በክርስቶስ ቤዛነት ለመዳን ከማሰብ ይልቅ ይህንን አማራጭ በመውሰድ በድግስ ነፍሱን ለማዳን ሲሟሟት፥ ሀብት ንብረቱን ትርፍ ለሌለው ነገር ሲከስር እናያለን።

የተቀሩት ምግባራት እንድንፈጽማቸው በጌታ የታዘዝን መሆኑ ቢታወቅም፥ እኛ የምንፈጽማቸው ግን ለነፍስ ድኅነት ያስጡናል ብለን አይደለም፤ ስለ ሁለት ምክንያት ነው።

የመጀመሪያው በክርስቶስ የዘላለም ሕይወት ስላገኘን ነው፤ እርሱ ያዳነን ከኀጢአት ርቀን መልካሙን ሥራ እንድንሠራ ነውና፤ (ኤፌ. 2፥10)። አምነን የዳንን መሆናችን የሚመሰክረው፥ በዐዲስ ሕይወት መመላለሳችንም የሚረጋገጠው እምነታችን በመልካም ሥራ ሲገለጽ ብቻ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፤ (ገላ. 5፥6፤ ያዕ. 2፥14-26)።

ሁለተኛው በእርሱ አምነን የጸደቅን ሁሉ ስለሠራነው መልካምም ሆነ ክፉ ሥራ በጌታ የፍርድ ወንበር ፊት ስለምንቆም ነው፤ (2ቆሮ. 5፥10)። ለያንዳንዱ እንደ ሥራው ዋጋውን ለመስጠት ጌታ ይመጣልና፤ (ራእ. 22፥12)።

እስካሁን የዳሰስነው ብቻም አይደለም፤ ከሞት በኋላ ደግሞ ቤዛ ሆኖ ከሞት ወደ ሕይወት እንዲያሸጋግራቸው ብለው ጸሎተ ፍትሐትንና ተዝካርን ለቤዛነት አቁመዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው አንድ ጊዜ ሞት፥ ተከትሎም ፍርድ ብቻ መመደቡን ሲናገር (ዕብ. 9፥27)፥ እነርሱ ደግሞ ይህን ለውጠው በጸሎተ ፍትሐትና በተዝካር ብዛት ወደ ሲኦል እንድትወርድ ተፈርዶባት በሲኦል ያለች ነፍስ፥ ባልሞቱ ወገኖቿ ይህ ቤዛ ነፍስ ቢሰጥላት ከሞት ወደ ሕይወት እንደምትሸጋገር ታምኖበት እየተሠራበት ይገኛል። አሁን አሁን እንኳ ይህቺ እነሆድ አምላኩ ለጥቅማቸው ሲሉ የሠሯት ሥርዐት እንደሆነች ሁሉም እየደረሰባት ነው።

የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትም በእውነተኛ ገጽታቸው ለሞተ ሰው ምንም ዓይነት ንስሓ የመግባትና የመዳን ዕድል እንደሌለው በግልጽ ስለሚናገሩ ከሞት በኋላ የሚደረግ የፍትሐትና የተዝካር ቤዛነት ረብ የለሽ ይሆናል።



ጸሎተ ፍትሐት በሚደርስበት በመጽሐፈ ግንዘት ውስጥ የሰፈረው ጽሑፍ እንዲህ ይላል: - «እምድኅረ ሞቱ ለሰብእ አልቦቱ ንስሓ» «ሰው ከሞተ በኋላ ንስሓ የመግባት ዕድል የለውም።»

ሊቁ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ደግሞ: - «ወበእንተዝ ይቤ ንቅረብ በሞገስ ከመ ንርከብ ሣህሎ፥ ወኵሎ ዘነኀሥሥ። እስመ ዝንቱ ሀብት ውእቱ፤ ወዝቢረ ምሕረት እምኀበ ንጉሥ ሰማያዊ፤ ይቤ ከመንርከብ ጸጋሁ ለጊዜ ረድኤቱ፤ ዝብሂል ለእመ ንሕነ ቀረብነ ይእዜ ንረክብ ጸጋ ወሣህለ። እስመ ቀረበነ በጊዜ መፍትው፤ ወበደኃሪሰ ለእመ ቀረብነ አልቦ ዘይበቁዐነ። እስመ ኀለፈ ጊዜ ተሣህሎ።»

ትርጓሜ:- «ስለዚህም ይቅርታውንና የምንሻውን ሁሉ ለማግኘት በባለሟልነት እንቅረብ አለ። ይህም ከሰማያዊው ንጉሥ የሚገኝ ሀብትና ይቅርታ ነው፤ ረድኤቱ በሚያስፈልገን ጊዜ ሀብቱን እናገኝ ዘንድ አለ። ይህም ማለት ዛሬ ብንቀርብ ሀብቱንና ይቅርታውን እናገኛለን ማለት ነው። በተገቢው ጊዜ (በሕይወተ ሥጋ ሳለን) ቀርበናልና፤ ኋላ ግን (ከሞትን በኋላ) ንስሐ ብንገባ የሚረባን የሚጠቅመን የለም፤ ይቅር የምንባልበት ጊዜ ዐልፏልና» (ድር. 7 ቍ. 175-183)።

በዚህ መሠረት እንግዲህ እነ እገሌ በክንፋቸው፥ እነ እገሌ በቃል ኪዳናቸው፥ ዝክር የዘከረላቸውን ከሲኦል ያወጡታል የሚለውና የወገኔን ልብ የሰረቀውን የገድላትና የድርሳናት ስብከት ዕርቃኑን ሲቀር ነው።

በመሠረቱ እኒህ ሁሉ ቤዛዎች ለሰው ነፍሱን ሊቤዡለት ቢችሉ ኖሮ ጌታ አስቀድሞ «ሰውስ ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?» ብሎ መናገር አስፈላጊው አልነበረም። ይሁንና ሰዎች በርካሽ ዋጋ ክብርት ነፍሳቸውን አራክሰው ሊዋጇት ቢመኙም፥ የሷ ተመን የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ደም ብቻ ነው እንጂ ኀላፊ የሆነ ብርና ወርቅ አይደለም፤ (1ጴጥ. 1፥18-19)።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በቂና ለዘላለም የሚያገለግል ፍጹም ስለሆነ ተጨማሪ ወይም ተለዋጭ ሌላ ቤዛ አያስፈልገንም፤ (ዕብ. 9፥12)።

እንደሚታወቀው ብዙዎች የክርስቶስን ቤዛነት በሌሎች ቤዛዎች ለመተካት የተገደዱት፥ ክርስቶስ የመጣው የጥንቱን በደል (ጥንተ አብሶን) ለማስወገድ እንጂ ዛሬ ስለምንሠራው ኀጢአት አይደለም ብለው ራሳቸውን ስላሳመኑት ነው። እንዲህ ከሆነማ ክርስቶስ የአዳምና የሔዋን ቤዛ ብቻ እንጂ የእኛ ቤዛ ሊባል አይቻልም። እኛም አምነን ልንድንበትና አንድ ጊዜ ለዘላለም ባቀረበው መሥዋዕት ዕለት ዕለት ከምንሠራው ኀጢአት ስርየትን ልንቀበል ባልቻልንም ነበር። ትክክለኛው ትምህርት ግን ከዚህ የሰዎች ፍልስፍና የተለየ ነው።

ሊቁ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ለጥንተ አብሶ ነው የመጣው ባዮችን በእግዚአብሔር ቃል ስሕተታቸውን ያሳያቸዋል፤ እንዲህ እያለ: -

«ወሶበ መጽአ በጥንተ አበሶ÷ እምኢአምኑ ቡቱ÷ ወእም ኢኮነ ሥርዐተ ሞቱ በእንተ ኀጢአተ ብዙኀን፤ እስመ ይቤ ውስተ ካልእ ገጸ መካን÷ ወለዘበዝኀ ኀጢአቱ ይፈደፍድ ሎቱ ጸጋ፤ ወበእንተዝ ይቤ ምዕረ አስተርአየ በፍጻሜ ዓለም÷ ከመይሠዐራ ለኀጢአት በመሥዋዕተ ዚአሁ።»

ትርጓሜ: - «በጥንቱ በደል መጥቶስ ቢሆን÷ የብዙዎች ቤዛ እንደሆነ ባላመኑበትም ነበር። በመስቀል ላይ የሆነው ሞቱም የብዙዎችን ኀጢአት ስለ ማስተስረይ ባልሆነ ነበር። በሌላው ስፍራ ኀጢአት በበዛበት የእግዚአብሔር ጸጋ ይበዛል ብሏልና። ስለዚህም በሱ መሥዋዕትነት ኀጢአትን ያጠፋ ዘንድ በዘመኑ ፍጻሜ አንድ ጊዜ ተገለጠ።» (ድር. 17 ቍ. 50-53)።



# ክፍል 4 - ኪዳን

## 4.1 ብሉይ ኪዳን

ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ከግብጽ ባርነት በመካከለኛ እጅ ቤዛ ሰጥቶ ከዋጀው ሕዝብ ጋር በቀድሞው ዘመን የገባው ኪዳን ነው። እግዚአብሔር ይህን ቃል ኪዳን የገባው ከእስራኤል ጋር ብቻ በመሆኑ÷ በቃል ኪዳኑ ሌሎች ሊታቀፉበት ወይም ሊሸፈኑበት አይችሉም፤ (መዝ. 147÷8-9፤ ሮሜ 9÷4)።

እግዚአብሔር መቼም ቢሆን ከሰው ልጆች ጋር ቃል ኪዳንን እንዲገባ የሚያደርገው÷ ለሰው ለጆች ያለው ጽኑ ፍቅር÷ የምሕረቱና የቸርነቱ ብዛት እንጂ÷ የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳንን ለማድረግ የሚችሉበት ብቃትና ቅድስና ኖሮአቸው አይደለም፤ (ኤር. 30÷21)። ሆኖም የሰው ልጆች ቃል ኪዳኑን ተቀብለው ቢታዘዙ በረከት ይመጣላቸዋል፤ ባይታዘዙ ደግሞ መርገም ይመጣባቸዋል።

በሙሴ መካከለኛነት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባው ብሉይ ኪዳን ዐሥሩን የቃል ኪዳን ቃላት የያዘ ነው፤ (ዘፀ. 34÷28)። ቃል ኪዳኑ በደም ተመርቆ መጽናት ነበረበትና (ዕብ. 9÷18)÷ ሕዝቡ እግዚአብሔር የተናገራቸውን ቃሎች ሁሉ እናደርጋቸዋለን በማለት ማረጋገጫ ሲሰጡ÷ ሙሴ መሥዋዕት ሠውቶ ደሙን በሕዝቡ ላይ በመርጨት ቃል ኪዳኑን አጸና፤ (ዘፀ. 24÷1-8)። ለቃል ኪዳኑ አፈጻጸም አስፈላጊ ነገሮች በመሆናቸው ሌሎች ትእዛዛት÷ ሥርዐቶችና ፍርዶችም ተሰጥተዋል።

ቃል ኪዳን ሲደረግ ሌላው አስፈላጊ ነገር ደግሞ ምልክት ነውና ሰባተኛው ቀን (ቀዳሚት ሰንበት) ለብሉይ ኪዳን ምልክት ሆኖ ተሰጥቷል፤ (ዘፀ. 31÷13፤16)።

በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ለተደረገው ቃል ኪዳን አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች ሁሉ በቃል ኪዳን ሰጪው በእግዚአብሔር በኩል ተሟልተው በዚህ ሁኔታ ስለቀረቡ÷ ቀጣይ ምላሽ ቃል ኪዳኑን ከተቀበሉት ከእስራኤል ልጆች የሚጠበቅ ነው።

ያም ቢሆን ብሉይ ኪዳን በራሱ ዘላለማዊ ቃል ኪዳን አይደለም። ጊዜያዊነቱን ወይም ፍጹም የሆነው ዐዲስ ኪዳን እስኪመጣ ድረስ የሚያገለግል ጥላ መሆኑን (ዕብ. 10÷1) የተረዳው ነቢዩ ሙሴ: - «... ጌታ አምላክ እኔን እንዳስነሣኝ÷ ነቢይን ከወንድሞቻችሁ ያስነሣላችኋል፤ በሚነግራችሁ ሁሉ እርሱን ስሙት፤ ያንም ነቢይ የማትሰማው ነፍስ ሁሉ ከሕዝብ ተለይታ ትጠፋለች።» በማለት መናገሩ እግዚአብሔር ሌላ የተሻለ ኪዳን ከሕዝቡ ጋር እንደሚገባ በሩቅ ሆኖ ማመላከቱ ነው። ይህም ትንቢታዊ ቃል በክርስቶስ የተፈጸመ መሆኑን ሐዋርያው ጴጥሮስ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ጠቅሶ በማረጋገጡ ሙሴ ትንቢቱን የተናገረበትን ዐላማ ግልጽ አድርጎታል፤ (ዘዳ. 18÷15፤18-19፤ የሐዋ. ሥራ 3÷22-23)።

እግዚአብሔር ከሙሴ በኋላ ብዙ ዘመናት ቆይቶ በተነሣው በነቢዩ በኤርምያስ አፍ፥ ከሕዝበ እስራኤል ጋር ገብቶ የነበረውን ቃል ኪዳን ሕዝቡ አፍርሶት በመገኘቱ፥ ሌላ ዐዲስ ኪዳን እንደሚገባ ተናገረ። በትንቢቱ ውስጥ የቀደመው ጊዜያዊ ኪዳን ከነተሰጠበቱ መንገድና ሁኔታ ጋር ተለውጦ፥ ዐዲስ ኪዳን በዐዲስ መንገድና ሁኔታ እንደሚሰጥ በግልጽ ተቀምጧል፤ (ኤር. 31፥31-34)።

ይኸውም ብሉይ ኪዳን ሕጉ በድንጋይ ጽላት ተጽፎ የተሰጠበት ኪዳን እንደ ነበረና፥ ዐዲስ ኪዳን ግን በድንጋይ ጽላት መሆኑ ቀርቶ በልብ ጽላት የሚጻፍበት ኪዳን እንደሚሆን፥ በዐዲስ ኪዳን እግዚአብሔር የሕዝቡን ኀጢአት ይቅር የሚልበትና ደግሞ የማያስብበት ኪዳን መሆኑ፥ በትንቢታዊ ቃሉ ውስጥ ጎላ ብለው የተቀመጡ ናቸው።

የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ቢያስተምርም በተለይም በኤር. 31፥31-34 ላይ የተጻፈውን ቃል፥ ከብሉይ ኪዳን ጥገኝነት ለመላቀቅ የማይፈልጉ ወገኖች ቃሉን ገርምመውት ወይም የጎሪጥ እያዩት፥ አሊያም ደግሞ እንቶ ፈንቶ ትርጉም ሰጥተውት ከሚያልፉ በቀር፥ ትኩረት ሰጥተው እውነቱን ለመረዳት አይፈልጉም።

ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክት ይህን የኤርምያስን ትንቢት ሁለት ጊዜ ጠቅሶታል፤ (ዕብ. 8፥8-12፤ 10፥15-16)። መልእክቱ የተጻፈላቸውን ዕብራውያንን ከብሉይ ኪዳን ወደ ዐዲስ ኪዳን በከፊል ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ዘወር እንዲሉ ለማድረግ ሲባል ተደጋግሞ መጠቀስ አስፈልጎታልና። ይህም ትንቢቱ የብሉይ ኪዳንን በዐዲስ ኪዳን መተካት የሚያስረዳና ልዩ ትኩረት የሚሻ ቍልፍ ትንቢት መሆኑን አመልካች ነው።

ለመጀመሪያ ጊዜ ሐዋርያው ትንቢቱን ጠቅሶ ሲናገር ነቢዩ ኤርምያስ እነርሱን (ብሉይ ኪዳንን የተቀበሉትን) «እየነቀፈ» የተናገረው ትንቢት መሆኑን አብራርቶ ጽፏል፤ (ዕብ. 8፥8)።

ስሙ እንደሚያስረዳው ብሉይ ኪዳን አሮጌ ውል ነው። አሮጌ የተሰኘውም ከቃል ኪዳኑ ማርጀት የተነሣ አይደለም። እስራኤላውያን የአገልግሎት ዘመኑ ገና ሳያበቃ ስላፈረሱትና ከእርሱ በብዙ መንገድ የተሻለው ዐዲስ ኪዳን ስላስረጀው ነው። የተሻለው ዐዲስ ሲመጣ የቀደመው አሮጌ መሰኘቱ የግድ ነውና፤ (ዕብ. 8፥13)።

ብሉይ ኪዳን ቀዋሚ ኪዳን ባለመሆኑ በዐዲስ ኪዳን መተካቱን ማንም እሌ ሊለው አይችልም። ውሸቶች ከያሉበት ተጠረቃቅመው ቦታውን አስለቀቁት እንጂ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ትምርህትም ብሉይ ኪዳን (ኦሪት)፥ ዐዲስ ኪዳን (ወንጌል) እስኪመጣ ድረስ ያገለገለና አሁን ግን ከመንገዱ የተወገደ ኪዳን መሆኑን ይመሰክራል።

ዮሐንስ አፈ ወርቅ በድርሳኑ ፦ «ሶበሰ ኢሀሎ ብሉይ ሕግ እም ኢይቤ አሠርዕ ሎሙ ሕገ ሐዲሰ፤ አጠየቀ ከመ ተአተተ አሐዱ ወተርፈ ካልዑ ሀየንተ ዘተአተተ። በከመ ቤት ብሉይ ሶበ ይወድቅ ይገድፍ ብእሲ ኵሎ ዘወደቀ፥ ወይትመየጥ ይሕንጽ መሠረተ



ወንሕነኒ ንብል ይእዜ ከመ ውእቱ ሐደሶ፥ ወቦ ዘገደፈ እምኔሁ ወቦ ዘኀደገ።»

ትርጓሜ ፦ « አሮጌው ሕግ (ብሉይ ኪዳን) ያለፈ ባይሆን ኖሮ ዐዲስ ሕግን (ዐዲስ ኪዳንን) እሠራላቸዋለሁ ባላለም ነበር። እንዲህ በማለቱ ብሉይ ኪዳን እንደ ተወገደና በተወገደው ምትክ ዐዲስ ኪዳን እንደጸና አስረዳ። ያረጀ ቤት በፈረሰ ጊዜ የወደቀውን ሁሉ በመተው መሠረቱን እንደሚያድስ፥ እኛም ሕጉን ዐደሰው እንላለን። ከሕጉ የጣለው አለ። የተወውም አለ።» (ድር. 14 ቍ.150-153)።

የመልክዐ ሥላሴ ደራሲም፡ - «አመ ወደይክሙ ሕገ ውሳጤ ነፍሳዊት ልቡና፤ ተአተተት ምስለ አይሁድ ሕገ ደብረ ጽልመት ሲና፤ ወለሕግክሙ ኀደገት መካና።» .

ትርጓሜ፡ - «ሥሉስ ቅዱስ ሆይ! በመንፈሳዊት ውሳጣዊ ልቡና ውስጥ ሕጋችሁን በሠራችሁ ጊዜ፥ በጨለማ የተከበበች የሲና ሕግ ከአይሁድ ጋር ተወገደች። ለሕጋችሁም ቦታዋን ለቀቀች።» ብሏል።

## 4.2 ዐዲስ ኪዳን

ዐዲስ ኪዳን አይሁድና አሕዛብ በመባባል ልዩነት ሳይደረግ በክርስቶስ ላመኑ ሁሉ÷ በእርሱ መካከለኛነት እግዚአብሔር የሰጠው የመጨረሻና ዘላለማዊ ቃል ኪዳን ነው፤ (ዕብ. 9÷15፤ 12÷24፤ 13÷20)።

በክርስቶስ መካከለኛነት የተሰጠው ይህ ኪዳን በደም መጽናቱ የሚጠበቅ ጉዳይ በመሆኑ÷ እንደ ብሉይ ኪዳን በእንስሳት ሳይሆን ክቡር በሆነው በክርስቶስ ደም የጸና ሆኗል፤ (ሉቃ. 22÷19-20)።

ዐዲስ ኪዳን የተሰጠው ብሉይ ኪዳን በተሰጠበት መንገድ÷ ወይም አሁን በቤተ ክርስቲያናችን እንደሚታየው ከብሉይ ኪዳን ጋር ተደባልቆ አይደለም። ያ የቀድሞው ለዚህኛው ጥላና ምሳሌ ስለነበር÷ በሚታዩና በሚዳሰሱ ቍሳቍሶች (ንዋያተ ቅድሳት) አማካይነት ተሰጥቷል። ይህኛው ግን ሁለንተናው መንፈሳዊ ስለሆነ በዐይን የሚታይና በእጅ የሚዳሰስ ቍሳቍስም ሆነ ሥርዐት የለውም።

የዕብራውያንን መልእክት በተረጐመበት ድርሳኑ ሊቁ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ይህን ሲያስረዳ: -

> «ብፁዕ ጳውሎስ ናሁ ከሠተ ይእዜ ከመ ሐዳስ ሕግ ትኄይስ እምሕግ ብሊት ... እስመ አልቦ ውስተ ሐዳስ ሕግ ምንትኒ ሥርዐተ ሥጋ÷ ወኢግብረ ትእዛዘ ኦሪት÷ ኢምኵራብ÷ ወኢቅድስተ ቅዱሳን÷ ኢካህን ዘከመዝ ሥርዐተ ክህነቱ÷ ወኢትእዛዘ ኦሪት ዘይትዐቀብ በከርሠ ታቦት÷ አላ ኵሉ ትእዛዛቲሁ ሉዓላዊ÷ ወአልቦ ውስቴቱ ምንትኒ ሕገ ሥጋ አላ መንፈሳዊ ኵለንታሁ።»

> ትርጓሜ: - «ብፁዕ ጳውሎስ እነሆ አሁን ዐዲሲቱ ሕግ ከአሮጌዋ ሕግ እንደምትሻል አስረዳ። በወንጌል ምንም ምን የሥጋ ሥርዐት የለምና፤ የትእዛዝ ሥራ የለም፤ ምኵራብ የለም፤ ቅድስተ ቅዱሳን የለም፤ የክህነቱ ሥርዐት እንደ ኦሪቱ የሆነ ካህንም የለም፤ በድንጋይ ጽላት ተጽፎ በታቦቱ ውስጥ ተቀምጦ የሚጠበቅ የኦሪት ትእዛዝም የለም፤ ሥርዐቱ ሁሉ ሰማያዊና ፍጹም ነው እንጂ። በውስጡም የሥጋ ሕግ ምንም ምን የለም፤ ሁለንተናው መንፈሳዊ የሆነ ሕግ ነው እንጂ።» (ድር. 8 ቍ. 2፤ 5-12)።

እግዚአብሔር ብሉይ ኪዳንን ከእስራኤል ልጆች ጋር ሲገባ የሰንበትን ቀን የቃል ኪዳኑ ምልክት አድርጎ ሰጥቶ እንደነበር ሁሉ÷ ቃል ኪዳኑ ሲለወጥ ምልክቱም ይለወጣልና ለዐዲስ ኪዳን ምልክት አድርጎ የሰጠው ጥምቀትንና ቅዱስ ቍርባንን ነው፤ (ማር. 16÷16፤ 1ቆሮ. 11÷23-26)።

የዘላለምን ሕይወት ተስፋ የያዘውና÷ ጥምቀትና ቅዱስ ቍርባን የተስፋው ምልክቶች ሆነው የተሰጡለት ዐዲስ ኪዳን÷ ብሉይ ኪዳንን ጨምሮ በዚያው ዘመን እግዚአብሔር ከተለያዩ ቅዱሳን ጋር በተለያየ ጊዜ ከገባቸው ቃል ኪዳኖች ሁሉ የተለየና የሚበልጥ÷ ሁሉም ነገር ፍጻሜን ያገኘበት ቃል ኪዳን ነው።



የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ራሳቸው እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ዐዲስ የሆነ ቃል ኪዳንን እንደሚገባ በመመስከራቸው÷ ብሉይ ኪዳንን ያረጀና ጊዜ ያለፈበት ኪዳን አድርገውታል፤ (ኤር. 31÷31)።

ሁሉም ሕግና ነቢያት የመሰከሩት ስለ ዐዲስ ኪዳን ብቻ ነው። ከዐዲስ ኪዳን በኋላ ግን ሌላ ቃል ኪዳን እግዚአብሔር እንደሚገባ አልተናገሩም፤ (የሐዋ. ሥራ 3÷21-24)።

የዐዲስ ኪዳን መጻሕፍትም እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ከገባው ዐዲስ ኪዳን በኋላ÷ ዐዲስ ኪዳንን የሚያስረጅ ወይም ደግሞ በዐዲስ ኪዳን ላይ ተጨማሪ የሚሆኑ ሌሎች ቃል ኪዳኖችን እንደገባ አልመሰከሩም፤ ለወደፊቱም ይገባል የሚል ትንቢት አይናገሩም፤ ተስፋም አይሰጡም።

በዚህ ኪዳን ጸንተን ባንኖርና ብናፈርሰው እንኳ÷ ሌላ ቃል ኪዳን ይገባል አይሉም፤ እንዲያውም «የእውነትን ዕውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኀጢአት ብናደርግ÷ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኀጢአት መሥዋዕት አይቀርልንምና፤ የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ።» ይላሉ እንጂ፤ (ዕብ. 10÷26-27)።

ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲያ የሚጠብቀን ፍርድ ነው እንጂ÷ ሌላ ከፍርድ የምናመልጥበት ኪዳን ፈጽሞ የለም። እግዚአብሔር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የወደደውን ሁሉ በዐዲስ ኪዳን በልጁ በኩል አከናውኖ ፈጽሟል። «በክርስቶስ ለማድረግ እንደ ወደደ እንደ ዐሳቡ÷ የፈቃዱን ምስጢር አስታውቆናልና፤ በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው ዐሳቡም÷ በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው።» (ኤፌ. 1÷9-10)።

የእግዚአብሔር የመጨረሻው መገለጥ በልጁ በኩል ስለሆነ÷ ከልጁ በኋላ የላከው ወይም ራሱን የገለጠበት መልእክተኛ የለም፤ (ማቴ. 21÷33-41፤ ዕብ. 1÷2)። ሐዋርያትና ሌሎች የወንጌል መልእክተኞችም ቢሆኑ÷ እግዚአብሔር ራሱን በልጁ የገለጠበትን የመጨረሻ መገለጥ ለሌሎች ሊገልጡ የተላኩ እንጂ÷ እግዚአብሔር ከልጁ በኋላ ራሱን የገለጠባቸው መልእክተኞች አይደሉም።

በዘመናችን ከተጻፉት የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት መካከል ስለ አስተርእዮተ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር መገለጥ) የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መሠረተ ሃይማኖትና የካህናት ተልእኮ የተሰኘው መጽሐፍ በገጽ 15 ላይ የሚከተለውን እውነት አስፍሯል: -

> «... ከዚህም ሌላ እግዚአብሔር አስቀድሞ በነቢያት÷ በመጨረሻም በአንድ የባሕርይ ልጁ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ገልጧል። ይህንንም በዕብራውያን 1÷1 በተጻፈው ቃል መረዳት እንችላለን። «ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዐይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ÷ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን

በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን።» ይህም የመጨረሻው የእግዚአብሔር መገለጥና መታወቅ ነው። ራሱ እግዚአብሔር ወልድ እኔን ያየ አብን አየ በማለት አረጋግጧልና፤ (ዮሐ.14፥9)።»።

ዐዲስ ኪዳን የዘላለም ሕይወት የተገኘበት፥ ርቀን የነበርነው ሁሉ ወደ እግዚአብሔር የቀረብንበት፥ የልጅነት መብት የተጐናጸፍንበት፥ እግዚአብሔር አምላካችን፥ እኛም ሕዝቡ የሆንበት፥ ኀጢአታችንና በደላችን ለዘላለም የተወገደበትና ዳግም ለዘላለም የማይታሰብበት ኪዳን ነው፤ (ኤር. 31፥33-34)።

በዚህ ኪዳን የሰውና የእግዚአብሔር ግንኙነት እንደገና መታደስና መቀጠል እንዲችል አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች ሁሉ ተሟልተዋል። አንድ ስንኳ የጎደለ ነገር የለም። በቃል ኪዳኑ የታቀፉትን ሁሉ የዘላለም ፍጹማን ያደረገ ዘላለማዊ ቃል ኪዳን ነው፤ (ዕብ. 10፥14፤ 13፥20)።



## 4.3 እግዚአብሔር ያልገባው ቃል ኪዳን

እግዚአብሔር የሰው ልጆችን የሚገናኘው በቃል ኪዳን አማካይነት በመሆኑ፥ በብሉይና በዐዲስ ኪዳን ዘመናት ከሕዝቡ ጋር የተገናኘባቸውን ቃል ኪዳናት እንደገባ ተመልክተናል። በተለይም ዐዲስ ኪዳን የመጨረሻውና ዐሳቡ ሁሉ የተፈጸመበት፥ የሰው ልጆችም በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ብቃት ያገኙበት ኪዳን ነው።

ከዐዲስ ኪዳን በኋላ እግዚአብሔር ኀጢአታችንን ስለማስተስረይና እኛን ወደ እርሱ ስለማቅረብ፥ ሌላ ኪዳን እንደገባ ምንም ዐይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ አይገኝም። ይኖራል ብሎ ማሰቡም ከሞኝነት ይቈጠራል። ምክንያቱም የዐዲስ ኪዳን በቸኛ አስታራቂ የሆነው ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ዋጋ ያልከፈለበት ኀጢአት የለማ! እርሱ ስለ ኀጢአት ሁሉ በቂ የሆነ መሥዋዕት አቅርቧል። «አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጓቸዋልና።» (ዕብ. 10፥14)።

የመጨረሻው ኪዳን የሚያመለክተውም፥ እግዚአብሔር በኪዳኑ የተገናኛቸውን ሰዎች ኀጢአት ደግሞ እንደማያስብና ስለ ኀጢአት ስርየት ድጋሚ ማቅረብ የሌለበት መሆኑን ነው። «ከዚያ ወራት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ። በልባቸው ሕጌን አኖራለሁ፤ በልቡናቸውም እጽፈዋለሁ፤» ብሎ ከተናገረ በኋላ፥ «ኀጢአታቸውንና ዓመፃቸውንም ደግሜ አላስብም ይላል። የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ ከዚህ ወዲህ ስለ ኀጢአት ማቅረብ የለም።» (ዕብ. 10፥16-18)።

የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ቢልም፥ እግዚአብሔር በልጁ በኩል ለመጨረሻ ጊዜ ከገባው ቃል ኪዳን ሌላ ከሌሎችም ቅዱሳን ጋር ቃል ኪዳን ገብቷል፤ በተገባውም ቃል ኪዳን መሠረት ኀጢአተኞች ቢማጸኑና ቃል ኪዳኑ የሚጠይቀውን ቢያሟሉ፥ ስርየተ ኀጢአትን ለራሳቸውና ለሌላውም ትውልዳቸው ያገኛሉ፤ መንግሥተ ሰማያትንም ይወርሳሉ፤ የሚሉና ከተሰቀለው መድኅን ከክርስቶስ ላይ የምእመናን ዐይን እንዲነሣ የሚያደርጉ የስሕተት ትምህርቶች፥ በቤተ ክርስቲያናችን ተስፋፍተው ይገኛሉ።

ምንጊዜም ቢሆን የስሕተት ትምህርቶች ተቀባይነት እንዲኖራቸው ከተፈለገ ከሚጠቀስላቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ጋር ይስማሙም ይጣሉም፥ ለጊዜው ስሕተትነታቸው እንዳይታይ የሚሸፈኑበት ቢያንስ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ይጠቀስላቸው ዘንድ የግድ ነው። ዛሬ ሙሉ በሙሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነው የሐዋርያት ትምህርት ያልተመሠረቱ የስሕተት አስተማሪዎች የህልውናቸውን ዕድሜ ያራዘሙት ከእግዚአብሔር ቃል በመጥቀስና ቃሉን እንደ ገዛ ፈቃዳቸው በመተርጐም ነው።

በቤተ ክርስቲያናችን ቃል ኪዳንን አስመልክቶ ያለውን የስሕተት ትምህርት ትክክለኛ ለማስመሰል ብዙ ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚጠቀሱ ይታወቃል። ይልቁንም በብሉይ ኪዳን ዘመን

እግዚአብሔር ከአጠቃላዩ የእስራኤል ሕዝብ ሌላ ከአንዳንድ ቅዱሳን ጋር በግል የተለያዩ ጉዳዮችን አስመልክቶ የገባቸው ቃል ኪዳናት በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሾች ናቸው:: የጥፋት ውሃን በምድር ላይ ዳግም ላለማምጣት ከኖኅ ጋር (ዘፍ. 9÷8-17)÷ ዘሩን እንደ ሰማይ ከዋክብትና እንደ ባሕር አሸዋ ስለማብዛትና የምድርን ነገዶች በዘሩ ስለመባረክ÷ ከነዓንንም ስለማውረስ ከአብርሃም ጋር (ዘፍ. 12÷3፤ 15÷5) የገባቸውን ቃል ኪዳናት ብቻ እንኳ በምሳሌነት መመልከት ይቻላል::

እግዚአብሔር ለኖኅና ለአብርሃም በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ምክንያቶች ቃል ኪዳንን ገብቷል:: ቃል ኪዳናቱ ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ነበሩ:: በተለይ ግን ከአብርሃም ጋር የገባው ኪዳን ምንም በወቅቱ የሚፈጸሙ ጉዳዮችን እንደያዘ ቢታወቅም÷ በቃል ኪዳኑ ውስጥ ዋና ተስፋ የነበረውና የምድር ነገዶች በዘሩ የመባረካቸው ነገር በክርስቶስ የሚፈጸም ነበር:: በመሆኑም ሐዋርያው በገላትያ መልእክቱ «ለአብርሃምና ለዘሩም የተስፋው ቃል ተነገረ፤ ስለ ብዙዎች እንደሚነገር ለዘሮቹም አይልም:: ስለ አንድ እንደሚነገር ግን ለዘርህም ይላል፤ እርሱም ክርስቶስ» በማለቱ የቃል ኪዳኑ ተስፋ ፍጻሜ ክርስቶስ መሆኑን አረጋግጦ ጽፏል፤ (ገላ. 3÷16)::

ለአብርሃም ቃል ኪዳን እንደገባ ሁሉ በዐዲስ ኪዳን ላሉት ቅዱሳንም ቃል ኪዳን ገብቷል የሚለው እንግዳ ትምህርት÷ ላይ ላዩን ለሚሰማው ሰው ትክክለኛ ነገር ይመስላል:: ይዘቱን÷ አፈጻጸሙንና የሚሰጠውን ተስፋ የተመለከትን እንደሆነ ግን ለአብርሃም ከተገባው ቃል ኪዳን ጋር በምንም መንገድ ግንኙነት የለውም::

ለአብርሃምና ለዘሩ የተገባውን ቃል ኪዳን ይዘቱን አፈጻሙንና ለቃል ኪዳኑ ከቃል ኪዳኑ ተቀባዮች የሚጠበቀውን ስንመለከት: -

1. እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ የሚያገለግለውን ቃል ኪዳን ከአብርሃም ጋር የገባው አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ለመግባት ብቁ ሆኖ በመገኘቱ አይደለም:: አብርሃምን እንዲሁ ስለወደደውና ስለመረጠው ከእርሱና ከዘሩ ጋር ቃል ኪዳንን አደረገ::

ስለ ዳዊት በሚናገርበት ስፍራ የእግዚአብሔር ቃል «ከመረጥሁት ቃል ኪዳኔን አደረግሁ::» መዝ. 88(89)÷3 በማለት መመስከሩ÷ እግዚአብሔር ቃል ኪዳንን ከሰው ልጆች ጋር የሚገባውና ወደ ራሱ የሚያቀርባቸው ከራሱ በጎ ፈቃድና ምርጫ አንጻር እንጂ÷ ከሰዎች ብቃት የተነሣ አለመሆኑን ያስረዳል::

«አለቃቸው ከእነርሱ ውስጥ ይሆናል፤ ገዥአቸውም ከመካከላቸው ይወጣል:: **እኔ አቀርበዋለሁ፤ እርሱም ይቀርባል፤ ይህስ ባይሆን ወደኔ** <u>**ለመቅረብ የሚደፍር ማነው?**</u>» (ኤር. 30÷21)::

2. በብሉይ ኪዳን ዘመን ከግለሰቦች ጋር የገባው ቃል ኪዳን÷ የነፍስን ድኅነት ከማሰጠት ጋር ምንም ዐይነት ግንኙነት አልነበረውም:: በአብዛኛው በወቅቱ ከነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ነበር:: ለምሳሌ ያህል ከኖኅ ጋር የገባውን ኪዳን ብንመለከት÷ በምድር ላይ የጥፋት ውሃ ዳግም እንዳይመጣ ተስፋ የሰጠ ሆኖ እናገኘዋለን እንጂ÷ ከነፍስ ድኅነት ጋር የተገናኘ



አይደለም:: ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠው ኪዳን ግን÷ የአብርሃም ዘር በሆነው በክርስቶስ ተፈጻሚ የሚሆኑ ተስፋዎችንም ያካተተ በመሆኑ÷ ከወቅቱ ጊዜያዊ ሁኔታዎች ጋር ብቻ የተያያዘ ነበር ለማለት አይቻልም፤ (ገላ. 3÷18)::

ስለሆነም ከአብርሃም ዘር ሰው የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ÷ የአብርሃምን የእምነት ፍለጋ ተከትሎ ያመነበትን ሕዝቡን በዐዲስ ኪዳን ወደ እግዚአብሔር አቅርቦ አስታረቃቸው:: መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን አስወግዶ÷ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን የሚያድል ሆነ፤ በጥቅሉ እንግዲህ ድኅነተ ነፍስን አስገኘ:: ከሰው ውደቀት በኋላ በዘመናት ሁሉ ውስጥ ድኅነተ ነፍስን ለመስጠት እግዚአብሔር የገባው ኪዳን ዐዲስ ኪዳን ብቻ ነው ማለት ነው::

3. እግዚአብሔር ቃል ኪዳንን ከሰዎች ጋር ሲገባ ሁሉን በፍቅሩና በፈቃዱ ያደረገው እንደመሆኑ መጠን÷ በቃል ኪዳኑ ለመሸፈንና የተስፋው ወራሽ ለመሆን ከሰዎች የተፈለገው ነገር ተስፋውን አምኖ መቀበልና እንደ ተስፋው ቃል መኖር ብቻ ነው:: ከዚህ በቀር ሌላ የተፈለገ የሕግ ሥራ የለም:: ያም ቢሆን በቃል ኪዳኑ የታቀፉ ሁሉ ቀጥተኛ ግንኙነት የሚያደርጉት ከቃል ኪዳን ሰጪው ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ እንጂ÷ ራሳቸውን ሆነውና ሌሎችንም ወክለው ቃል ኪዳኑን ከተቀበሉት ፍጡራን ጋር አይደለም::

ለአብርሃምና ለዘሩ ለተገባው ኪዳን ወራሾች የሆኑት እስራኤላውያን በመልካምም ሆነ በክፉ አጋጣሚ÷ እግዚአብሔርን ለማመስገንም ሆነ ለመለመን በጸሎት ይቀርቡ የነበረው ወደ ቃል ኪዳን ሰጪው ወደ እግዚአብሔር ነበር:: ሲቀርቡም ቃል ኪዳኑን በውክልና የተቀበሉትን ሰዎች ስምና ቃል ኪዳኑን ማውሳት ለተነሡበት የምስጋናም ሆነ የልመና ርእስ አስፈላጊ በመሆኑ ይህን መጠቀም የተለመደ ነገር ነው፤ (ዘፀ. 32÷13-14፤ መዝ. 104 (105)÷8-10፤ ሉቃ. 1÷54-55፤ 72-73)::

ቢሆንም ቅሉ እንዲህ ማድረጋቸው በቃል ኪዳኑ ተቀባዮች በኩል ዐልፈው ወደ እግዚአብሔር ቀረቡ የሚል አንድምታ አይሰጠውም:: ይህ እግዚአብሔር የገባውን ኪዳን የሚጠብቅ ታማኝ አምላክ እንደሆነ በመቍጠር÷ ቅዱሱን ኪዳን ዐስቦ የቸርነቱንና የምሕረቱን ሥራ እንዲሠራ እሱን ለመማጸን የተጠቀሙበት መንገድ ነው::

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው ሦስት ነጥቦች ቀጥሎ የምናየውን ከእግዚአብሔር ያልሆነውን ቃል ኪዳን ይዘትና አፈጻጸም የምንመዝንባቸው ይሆናሉ::

መናፍቃን እግዚአብሔር ከዐዲስ ኪዳን ሌላ ከቅዱሳን ጋር ቃል ኪዳን ገብቷል የሚለውን የስሕተት ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያናችን አሹልከው ያስገቡት÷ በአዋልድ መጽሕፍት የስርቆት በርነት በኩል ነው::

በሚታወቁና በማይታወቁ ቅዱሳን ስም የተደረሱት ገድላትና ድርሳናት÷ ቅዱሳኑ በተጋድሎአቸውና በመልካም ሥራቸው ቃል ኪዳንን እንደተቀበሉ÷ ይህም ቃል ኪዳን ነፍስን ማስማርና መንግሥተ ሰማያትን ማስወረስ እንደሚችል÷ ለዚህም በቅዱሳንና በቃል ኪዳናቸው በመማጸን በቃል ኪዳኑ ለመሸፈን የሚሻ ሁሉ÷ ለቃል ኪዳኑ አፈጻጸም የታዘዘውን ሥራ በቅዱሳኑ ስም ሠርቶ መገኘት እንደሚገባው ይተርካሉ።

ሁሉም ገድላትና ድርሳናት እንደሚናገሩት ለቅዱሳን ተገብቷል በሚለው ቃል ኪዳን ለመሸፈን መሠራት ካለባቸው ሥራዎች መካከል: - በቅዱሳኑ ስም የተሰየሙትን በዓላት ማክበር (በበዓላቱ ቀን ሥራ አለመሥራት)÷ በነዚሁ ቀናት በቅዱሳን ስም ድግስ ደግሶ ዝክር በመዘከር የተራቡትን ማብላትና ማጠጣት÷ የተደገሰውንም መብላትና መጠጣት÷ በቅዱሳኑ ስም የተገደሙትን ገዳማት ስፍራው ድረስ በመሄድ መጐብኘትና መሳለም÷ በየገዳማቱ ከሚዘጋጀው መብልና መጠጥ መቋደስ÷ ጸበል መጠጣት÷ ዐፈርና የመሳሰሉትን ነገሮች መተባበስና መቀባባት÷ በቅዱሳኑ ስም የገድል መጻሕፍትን መጻፍ÷ ማጻፍ÷ ማንበብ÷ መስማት÷ መተርጐም የሚሉት በብዛት የሚጠቀሱ ናቸው።

በጥቅሉ ጽድቅ በሥራ÷ ለዚያውም ከእምነት በሆነ መታዘዝ (ሮሜ 1÷5) የሚከናወነውን መልካም ሥራ በመሥራት ሳይሆን÷ ማንኛውም ሰው ቢታዘዝ ለመፈጸም የማይቸገርበትን አፍአዊ ተግባር በመፈጸም እንደሚገኝ የሚሰብኩ ናቸው።

ሕዝባችንም በአዋልድ መጻሕፍት ስብከት ልቡ በመማለሉና ለመዳን አቋራጭ መንገድ ያገኘ ስለሚመስለው÷ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ ከመጽደቅና በሕግ ያለውን ዋና ነገር ለመፈጸም ራስን አሳልፎ ከመስጠት ይልቅ÷ ገድላትና ድርሳናት በቃል ኪዳን ስም እንዲፈጸሙ የሚያዟቸውን አፍኣዊ ተግባራት መከወንን ይመርጣል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ትምህርት ከሆነ ግን በዚህ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘትና የዘላለምን ሕይወት ማግኘት አይችልም።

እግዚአብሔር ያዘዘውን ዋና ነገር ቸል ብለው በእንዲህ ዐይነቱ ሰው ሠራሽ አገልግሎት ተጠምደው የነበሩትን ጸሐፍት ፈሪሳውያንን÷ ጌታችን ወዮታ ያለበትን ወቀሳ ሰንዘረባቸው እንጂ አበጃችሁ ብሎ አላመሰገናቸውም። «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን÷ ከአዝሙድና ከእንስላል÷ ከከሙንም ዐሥራት ስለምታወጡ÷ ፍርድንና ምሕረትን÷ ታማኝነትንም÷ በሕግ ያለውን ዋና ነገር ስለምትተዉ ወዮላችሁ!» (ማቴ. 23÷23)።

እንግዲህ አዋልድ መጽሐፍት በገጾቻቸው ሰፊ ሽፋን ሰጥተው በአጽንዖት የሚሰብኩለት ይህ ቃል ኪዳን÷ በእግዚአብሔር ያልተገባና ሰዎች የፈጠሩት መሆኑ ከፍሬው ይታወቃል። በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ከላይ በተቀመጡት በሦስቱ ነጥቦች ስንመዝነው ከአንዱም ጋር ስምምነት የለውም፤ እንዲያውም ተቃራኒ ሆኖ እናገኘዋለን። ይኸውም: -

- ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳንን ለመግባት ሰው ምንም ብቃትና መብት እንደሌለውና÷ እግዚአብሔር እንዲሁ ከፍቅሩ የተነሣ የሚያደርገው



መሆኑ እየታወቀ÷ ቅዱሳን በተጋድሎ ብዛት ስለበቁ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ለመግባት እንደቻሉ ተደርጎ መቅረቡ፤

«ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳችን እንኳ ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንም።» (2ኛቆሮ. 3÷5)።

- ከዐዲስ ኪዳን በቀር ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚያስገባ ቃል ኪዳን÷ እግዚአብሔር በብሉይም ሆነ በዐዲስ ኪዳን ዘመን ከማንም ፍጡር ጋር እንዳልገባ ግልጽ የሆነ ክርስቲያናዊ ትምህርት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ራሱ ባቀረበበት በዐዲስ ኪዳን ዘመን የክርስቶስን ሞት ከንቱና ረብ የለሽ በማድረግ÷ ወይም በተጨማሪነት መንግሥተ ሰማያት ለመግባት የሚያስችል ኪዳን እግዚአብሔር ከፍጡራን ጋር ገብቷል መባሉና ቃል ኪዳኑ ከሕግ ሥራ ጋር የተያያዘ መሆኑ ይጠቀሳሉ።

ከጊዜ በኋላ የተነሡ የስሕተት አስተማሪዎች አዋልድ የተሰኙትን መጻሕፍት በመሣሪያነት ተጠቅመው÷ ሕዝቡን ከእውነተኛው ቃል ኪዳን እንዲወጣ ቢያደርጉትም÷ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው ጥንታዊው የቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ ቃል ኪዳንን አስመልክቶ÷ እግዚአብሔር ሁሉን በልጁ በኩል በገባው ዐዲስ ኪዳን እንዳከናወነና እኛም በቅዱሱ ኪዳን የታቀፍን የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ይገልጻል።

«ከመ ታእምሩ ፈቃዶ ለኢየሱስ ክርስቶስ÷ ወትሌብዉ ምስጢረ መድኀኒትክሙ፤ አ! አንትሙ እደው ወአንስት ቅዱሳት እለ ሀሎክሙ ውስተ ተመክሖ በክርስቶስ÷ ወኩኑ አሐደ ምስለ ብእሲ ዘውስጥ÷ አንትሙኬ እለአጽንዐ እግዚአብሔር ኪዳኖ ምስሌክሙ፤ ወሤመ መንፈሶ ውስቴትክሙ።» ።

ትርጓሜ : - «የኢየሱስ ክርስቶስን ፈቃድ ታውቁ ዘንድና የድኅነታችሁን ምስጢር ታስተውሉ ዘንድ÷ በክርስቶስ ትምክሕት ያላችሁ እናንተ ወንዶችና ቅዱሳት ሴቶች ሆይ! ከውስጣዊ ሰውነት ጋር አንድ ሁኑ፤ እግዚአብሔር ኪዳኑን ከእናንተ ጋር ያጸና÷ መንፈሱንም በውስጣችሁ ያሳደረ እናንተ ናችሁ።» (ሃይ. አበ. ም. 4 ቍ. 6-7)።

ይህን እውነት ቸል ብለው ከእግዚአብሔር ያልሆነውን ቃል ኪዳን የሚያደርጉትን ወገኖች የእግዚአብሔር ቃል: - «ለዐመፀኞች ልጆች ወዮላቸው! ይላል እግዚአብሔር፤ ከእኔ ዘንድ ያልሆነን ምክር ይመክራሉ÷ ኀጢአትንም በኀጢአት ላይ ይጨምሩ ዘንድ ከመንፈሴ ዘንድ ያልሆነውን ቃል ኪዳን ያደርጋሉ።» ይላል፤ (ኢሳ. 30÷1) ።

# ክፍል 5 - ሕግ

## 5.1 ሕግ በብሉይ ኪዳን

በዘመነ ኦሪት ሕግ በሙሴ እንደ ተሰጠ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፤ (ዮሐ. 1÷17) ። ሙሴ ሕዝበ እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ነጻ አውጥቶ ተስፋይቱን ምድር ከነዓንን ለመውረስ በጉዞ ላይ እያሉ ሲና ተራራ ሲደርሱ ሕግን ተቀብሏል፤ (ዘፀ. 19-20)።

ለሕዝበ እስራኤል ሕግን መስጠት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት፥ ለ400 ዓመታት ያህል በአሕዛብ መካከል ሲኖሩ፥ የነርሱን ርኩሰት የተሞላ ባህል፥ ሥርዐትና ልማድ ወርሰው ነበርና፥ እንደ ገናም በተስፋይቱ ምድር የእግዚአብሔር ሕዝብ ሆነው ሲኖሩ፥ በምድረ ከነዓን ዙሪያ ባሉት አሕዛብ ርኩሰት ሳይጠመዱ የእግዚአብሔር የቅድስናው ተካፋይ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው፤ ሕጉ በባሕርዩ እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን የሚያሳይ ነውና።

እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ የሰጣቸው ሕግ በሦስት ተከፍሎ ሊታይ እንደሚችል የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ያስረዳሉ። የመጀመሪያው ዐሠርቱን ትእዛዛትና ተመሳሳይነት ያላቸውን ትእዛዞች የያዘው የሕግ ዐይነት ነው። ይህ ሕግ እስራኤላውያን ጣዖትንና ማንኛውንም ተመሳሳይ የሆነ ባዕድ አምላክ እንዳይከተሉ የሚከለክልና እግዚአብሔርን ብቻ በማምለክ ለርሱ ታማኞች ሆነው እንዲኖሩ የሚያዝ ነው። ከዚህም ሌላ በባልንጀራቸውና በወገናቸው ላይ ማንኛውንም ክፋት እንዳያደርጉ ይከለክላል። በሌላው ስፍራ ይህ የሕግ ዐይነት እግዚአብሔርን በፍጹም ልብና ዐሳብ መውደድ፥ እንዲሁም ባልንጀራን እንደ ራስ አድርጎ መውደድ ተብሎ ተገልጿል፤ (ዘዳ. 6÷5፤ ዘሌ. 19÷18፤ ሉቃ. 10÷27)።

ሁለተኛው የሕግ ዐይነት ሌሎች የሕዝቡ መተዳደሪያ ሕጎች ናቸው። እነዚህም እስራኤላውያን በያንዳንዱ የኑሮ ዘርፍ እንዴት ባለ ሕይወት መመላለስ እንዳለባቸውና፥ እንደ አንድ የአገር ዜጋ የሚተዳደሩባቸው ሕግጋት ናቸው። ለምሳሌ: - የተለያዩ የሥጋ ሥርዐቶች፥ የወሊድና የእናትነት፥ ጋብቻን የተመለከቱ ሕግጋትም በዚህ ውስጥ ይካተታሉ።

ይህ ሕግ መስጠት ያስፈለገበትም ምክንያት ከላይ እንደተገለጸው ሕዝበ እስራኤል የእግዚአብሔር ሕዝብ በመሆናቸው፥ የአሕዛብን የኑሮ ፈለግ እንዳይከተሉ ለመገደብ ነው። ምክንያቱም በተሰጠው በዚህ ሕግ አንጻር በከነዓናውያን ዘንድ አጸያፊ የሆነ የርኩሰት ሥራ ይሠራ ነበር።

ሦስተኛው የሕግ ዐይነት ደግሞ አምልኮን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች የተካተቱበት ሕግ ነው። በዚህ ሕግ ውስጥ ስለ መገናኛው ድንኳን፥ ስለ ክህነት፥ ስለ መሥዋዕቶችና በዓላት ወዘተ... የተደነገጉ ሕጎችን እናገኛለን። እነዚህን ሦስት የሕግ ዐይነቶች እግዚአብሔር የሰጠው ለሕዝበ እስራኤል ብቻ ነው። «ቃሉን ለያዕቆብ፥ ሥርዐቱንና ፍርዱን ለእስራኤል ይናገራል። ለሌሎች አሕዛብ ሁሉ እንዲህ አላደረገም። ፍርዱንም አልገለጠላቸውም።» (መዝ. 147÷8-9) በተጨማሪ (ሮሜ 3÷2፤ 9÷4)።



ሕጉ የእግዚአብሔርን ቅዱስ ባሕርይ የሚያሳይ እንደ መሆኑ መጠን በራሱ ቅዱስ ነው፤ (ሮሜ 7÷12)። ስለዚህ ሕዝበ እስራኤል ሙሉ በሙሉ ፈጽመውት ቢገኙ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ሆነው ይቈጠሩበታል፤ ቢያፈርሱት ወይም ደግሞ ከፊሉን ጠብቀው ከፊሉን ቢተላለፉ ግን ሕግ ተላላፊ ወይም በደለኛ ይሆናሉ፤ (ያዕ. 2÷10)። ሕግ ተላላፊም ከእርግማን በታች መሆኑ ግልጽ ነው፤ (ገላ. 3÷10)።

ሕጉና የእግዚአብሔር ቃላት ዐደራ የተሰጧቸው እስራኤላውያንም፥ ከዚሁ አንጻር ሕጉን በሙሉ ፈጽመው በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ሆነው ሊቈጠሩ አልቻሉም። ሕግ ተላላፊዎች ተብለው ከተቀሩት አሕዛብ ጋር በኀጢአተኝነት ተከሰዋል፤ (ሮሜ 3÷9)።

ለምን ሕጉን መፈጸም ተሳናቸው? ቢባል አዳም በኀጢአት ከወደቀ በኋላ የሰው ዘር መንፈሳዊ ዐቅም ስላጣ ሕግን መጠበቅ የማይችል ሆኗልና ነው። ሕጉ ሲሰጣቸው መፈጸም የሚችሉበት ኀይልም አብሮ ስላልተሰጣቸው የሕጉ የበታች እንጂ የበላይ መሆን አልቻሉም። ስለዚህ ተቀብለው ያፈረሱት ሕግ ኀጢአተኝነታቸውን ገልጦ ይከሳቸው ነበር። ከዚህ አንጻር ሲታይ ሕግ በራሱ ምዉት የነበረውን ኀጢአትን ሕያው አድርጎ፥ ሰዎችን በኀጢአተኝነት ከመክሰስና ሞትን ከማስፈረድ በቀር የፈየደው አንዳችም ነገር የለም፤ (ሮሜ 7÷8-11)።

እንግዲህ ቅዱስ የሆነውና ለሕይወት ተሰጥቶ የነበረው ሕግ የሚፈጽመው ባለመገኘቱ ለሞት ሆኗል። ከዚህም የምንረዳው አንድ ነገር ሰው በሕግ ሥራ ሊጸድቅ የማይችል መሆኑን ነው፤ (ሮሜ 3÷20፤ ገላ. 2÷16)።

በእርግጥም ሰው የተሰጠውን ሕግ ሁሉ ፈጽሞና አለ ነቀፋ ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት በጻድቅነት ሊገኝ አልቻለም። የእግዚአብሔር ቃል «በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ፥ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉም።» ይላልና (ሮሜ 3÷12)።

መቼም ቢሆን አስቀድሞ የተሰጠው ሕግ መሻሻል እስካልተደረገበትና በሌላ ሕግ እስካልተተካ ድረስ ሁሉም እየተገዛለት መቈየቱ የግድ ነው። ለእስራኤላውያን የተሰጠው ሕግም እነርሱን ከሥሩ አድርጎ ሲገዛቸው፥ በኀጢአተኝነት ሲከሳቸውና ከሥጋ ደካማነት የተነሣ (ሮሜ 8÷3) ሊያጸድቃቸው ሳይችል ቀርቷል። ስለዚህ በሕግ ቀንበር ውስጥ የነበሩ ሁሉ፥ በኀጢአት ክሶ ለሞት አሳልፎ ከሚሰጠው ከሕግ ነጻ ለመሆን በራሳቸው ማድረግ የሚችሉት አንዳችም ዐቅም ስላልነበራቸው፥ በሕግ አፍራሽነት ለሞት ተላልፎ ከሚሰጠው ሰውነታቸው የሚያድናቸውን መፈለግ ግድ ሆነባቸው፤ (ሮሜ7÷24)።

ሕግ፥ ጽድቅ በሰው ጥረት እንደማይገኝ በማያዳግም ሁኔታ ያሳየ ታላቅ መምህር ነው። በመምህርነቱም በሥሩ የነበሩትን ሁሉ እንደ ሞግዚት ሆኖ በማስተዳደር፥ እርሱን ተክቶ ወደሚያገለግለውና ሰዎችን ሁሉ ለማዳን ወደሚችለው ወደ እምነት አድርሷል፤ (ገላ. 3÷23-24)።

## 5.2 ሕግ በዐዲስ ኪዳን

ሕግ በብሉይ ኪዳን በሰጠው አገልግሎት ማጽደቅ ካልቻለ፥ በዐዲስ ኪዳን ዘመን ያጸድቃል ብሎ መጠበቁ ከሞኝነት ይቈጠራል። የዐዲስ ኪዳን መጻሕፍትም የብሉይ ኪዳንን የመፈጸም ዜና ሲያበሥሩ፥ ይህን ሐሳብ ደግፈውት አናገኝም። ይልቁንም በሕግ ሥራ (ሕግን በመፈጸም) ለመጽደቅ የማይቻል መሆኑን አስረግጠው ይናገራሉ፤ (ሮሜ 3፥20፤ 28፤ ገላ. 2፥16)። አክለውም ክርስቶሳውያን ምእመናን ከሕግ እስራት ስለተፈቱ ለዐዲሱ የመንፈስ ኑሮ ካልሆነ በቀር፥ ለአሮጌው የፊደል ኑሮ (ለሕግ) ከመገዛት ነጻ መውጣታቸውን ያውጃሉ፤ (ሮሜ 7፥6)።

ይህን መሠረት ይዘው ክርስቲያኖችም እምነት ሊያጸድቅ በመጣበት በዐዲስ ኪዳን ዘመን፥ በሕግ ለመጽደቅ መፈለግ ከጸጋ እግዚአብሔር ተለይቶ የመውደቅን ኪሳራ እንደሚያከናንብ ስለሚረዱ ከዚህ እውነት ፈቀቅ አይሉም፤ (ገላ. 5፥4)።

ለብሉይ ኪዳን አማኞች ከሥጋ ደካማነት የተነሣ ሊያጸድቅ ወይም ሕያው ሊያደርግ የማይቻለው ሕግ (ሮሜ 8፥3፤ ገላ. 3፥21)፥ በመካከለኛቸው በሙሴ በኩል ተሰጥቶ እንደነበረ ሁሉ፥ በዐዲስ ኪዳን ላለው የእግዚአብሔር ሕዝብም በመካከለኛቸው በክርስቶስ በኩል የተሰጠው ያው ማጽደቅ ያልተቻለው ሕግ ሳይሆን፥ ጸጋና እውነት ነው፤ (ዮሐ. 1፥17)።

በክርስቶስ በኩል የተሰጠን የዘላለም ሕይወት፥ ሕግን ከመፈጸም ጋር በምንም መልኩ ግንኙነት የለውም። ድኅነታችን የሆነውና በራሱ በሕግና በነቢያትም ጭምር የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ የተገለጠው ያለ ሕግ ነው ተብሏል፤ (ሮሜ 3፥21)። ይህም የሆነበት ምክንያት ድኅነት (የዘላለም ሕይወት) የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ በመሆኑ ማንም በድካሜ አገኘሁት ብሎ እንዳይመካ ነው። «ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።» (ኤፌ. 2፥8-9፤ ሮሜ 3፥27-30)።

የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ ፈቃደኛ በሆነ ልብ አምኖ ለመቀበል የሚያስችለውን የድኅነትን መንገድ፥ ለአማኙ የሚያብራራውንና እውነት ወደ ሆነው ሁሉ የሚመራውን መንፈስ ቅዱስን መቀበልም ከእምነት ጋር በሆነ መስማት እንጂ በሕግ ሥራ አይደለም፤ (ገላ. 3፥2)። ሌላውም በክርስትና ሕይወታችን የምናገኘው ሰማያዊ በረከት ሁሉ ከእግዚአብሔር ምሕረትና ጸጋ የተነሣ የሚሆን እንጂ በግል ጥረትና ተጋድሎ የሚገኝ አይደለም፤ (ኤፌ. 1፥3-14)።

በመሆኑም ክርስቲያኖች ለብሉይ ኪዳን አማኞች ተሰጥቶ የነበረውን፥ በተለይም ደግሞ የሕዝቡን መተዳደሪያና የአምልኮ ሕጎችን ይፈጽሙ ዘንድ አይጠበቅባቸውም። በእነዚህ ሕግጋት ውስጥ በአብዛኛው ተካተው የምናገኛቸው ጥላና ምሳሌ የሆኑ ነገሮችንና አፍኣዊ የሥጋ ሥርዐቶችን ነው። እነዚህም የሚያመልከውን ሰው በኅሊና ፍጹም ሊያደርጉት አይችሉም፤ (ዕብ. 9፥10)።



እንደሚታወቀው ለአንድ ወቅት የተደነገገ ሕግ በሌላ ዐዲስ ሕግ እስካልተሻሻለ ወይም እስካልተተካ ድረስ፥ በሥራ ላይ መዋሉ የግድ ነው። ክርስቲያኖች የኦሪትን ሕግ ከመጠበቅ ነጻ እንዲሆኑና በእርሱ ከመፈረድ እንዲድኑ፥ ከእርሱ የተሻለና የበለጠ ሌላ ሕግ ያስፈልጋቸዋል። ይህም ውጫዊና የሥጋ ሥርዐት የሆነ ሕግ (የኦሪት ሕግ) ሳይሆን ከውስጥ መታዘዝ ጋር የተያያዘ መንፈሳዊ ሕግ ነው፤ ምእመናንን ከኀጢአትና ከሞት ሕግ አርነት ያወጣ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ (ሮሜ 8፥3)፥ ወይም የእምነት ሕግ (ሮሜ 3፥27)።

«ሕግ» የሚለውን ቃል ሐዋርያው ጳውሎስ እንደየዐውደ ምንባቡ የተለያዩ ሐሳቦችን ለመግለጽ ተጠቅሞበታል። በዚህም መሠረት በሮሜ 3፥27 የእምነት ሕግ ሲል «የእምነት መንገድ» ወይም «መመሪያ» ማለቱ ሲሆን፥ በሮሜ 8፥3 ደግሞ «በቍጥጥር ሥር የሚያውል መመሪያ» ማለት መሆኑን የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራን ያብራራሉ። በተለይም ሁለተኛው ሐሳብ ክርስቲያኖች በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ፥ በኀጢአትና በሞት ቍጥጥር ሥር ከሚያውላቸው አሮጌ ሥርዐት ወጥተው፥ የዘላለም ሕይወት ባለቤቶች ወደሚያደርጋቸው ዐዲስ ሥርዐት መሸጋገራቸውን የሚያስረዳ መሆኑን መምህራኑ አክለው ይናገራሉ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተራራው ስብከት ተብሎ በሚታወቀው ክፍል፥ በኦሪት ተሰጥቶ የነበረውንና በዐዲስ ኪዳን ዘመንም የጸናውን የሥነ ምግባር ሕግ፥ በውጫዊ ሕይወት ከመፈጸም ዐልፎ ይበልጥ ከውስጣዊ መታዘዝ ጋር በተያያዘ መንገድ ተፈጻሚነት እንዲኖረው የበለጠ ሲያጠናክረውና ሲያጠብቀው እንመለከታለን፤ (ማቴ. 5፥21-48)።

የሥነ ምግባር ሕግ እንኳን በጠነከረ መንገድ ከውስጣዊ መታዘዝ ጋር ተያይዞ ቀርቦ ይቅርና፥ እንዲሁም ቢሆን «ሕጉ አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበር።» (ሮሜ 7፥7) የሚል ምክንያተኝነት እንዲቀርብ ከማድረግና በኀጢአተኝነት ከመክሰስ በቀር፥ ሰው ይፈጽመው ዘንድ እንዳልተቻለው ከብሉይ ኪዳን ተሞክሮ እንረዳለን። ስለዚህ ይህን ሕግ የምንፈጽምበት ኀይል የግድ ያስፈልገናል።

ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሲመጣ ጸጋንና እውነትን ተመልቶ በኛ በማደሩ፥ ያመንበት ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናል፤ (ዮሐ. 1፥14፤16)። ይህም ጸጋ እኛን ያዳነ (ኤፌ. 2፥8)፥ ካዳነን በኋላም በዚህ በክፉው በተያዘው ዓለም ስንኖር ኀጢአተኝነትንና ዓለማዊ ምኞትን ክደን፥ የክርስቶስን ዳግም ምጽአት በተስፋ እየጠበቅን ሕጉንና ፈቃዱን እንድንፈጽም የሚያስችለንን ኀይል የሚሰጥ ነው፤ (ቲቶ 2፥11-13)። ምልልሳችንና ብቃታችን፥ በአጠቃላይም መንፈሳዊ እኛነታችን ሁሉ በጸጋው ላይ የተደገፈ ነው፤ (2ቆሮ. 3፥5፤ 1ቆሮ. 15፥10፤ 2ቆሮ. 12፥9-10)። ከዚህ የተነሣ የዐዲስ ኪዳን ምእመናን

«ከሕግ በታች» ሳይሆን «ከጸጋ በታች» ያሉ ተብሎ ሊነገርላቸው የተገባ ሆነ፤ (ሮሜ 6÷14)።

በኦሪት ሕግ መሠረት አንድ ሰው አመነዘረ የሚባለው ኀጢአቱን በገቢር ሲፈጽመው ብቻ ነበር። በዐዲስ ኪዳን ግን አንድ ሰው ወደ ሴት አይቶ በልቡ ቢመኛት÷ ምንም እንኳ በገቢር የፈጸመው ድርጊት ባይኖርም በልቡ አመንዝሯል። ይህ እንደ ሰው ሁኔታ ሲታሰብ÷ እንኪያስ ማን ሊድን ይችላል? የሚል ሌላ ጥያቄ ማስነሣቱ አይቀርም። በእርግጥም ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉ ይቻላል፤ (ማቴ. 19÷25-26)። ስለዚህ የሕጉ ጠብቆ መቅረብ ዐዲስ ኪዳን ሕግን መፈጸም የሚያስችል የእግዚአብሔር ጸጋ ለክርስቲያኖች የፈሰሰበት ዘመን መሆኑን ያመለክታልና የሕጉ መጠንከር ብዙም አያስገርምም።

እንግዲህ ክርስቲያኖች በእምነት ብቻ የጸደቁ ስለሆኑ ለመጽደቅ ሲሉ የአገልግሎት ዘመኑ ያበቃውን የኦሪትን ሕግ መፈጸም አይፈለግባቸውም ተብሏል፤ ነገር ግን ይህ የጸናውንም ሕግ ቢሆን ከመጠበቅ ነጻ ናቸው ወደሚል ድምዳሜ በጭራሽ አያመጣንም። ዛሬም ቢሆን የጸናውን ሕግ የሚጠብቁት የጸደቁ በመሆናቸው ነው እንጂ÷ በሥራቸው ለመጽደቅ ብለው እንዳልሆነ መታወቅ ይኖርበታል።

እግዚአብሔር እኛን እንዲሁ በእምነት ብቻ ያጸደቀን በጸጋው የእምነትን ሕግ ፈጽመን መልካሙን ፍሬ እንድናፈራ ነው። በሁለተኛው አዳም በክርስቶስ ዳግም የመፈጠራችን ዋናው ዐላማም÷ ሳይበድል በፊት ወደነበረው የአዳም ሕይወት ተመልሰን÷ እግዚአብሔር እንመላለስበት ዘንድ አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ነገር ለመድረግ እስከሆነ ድረስ (ኤፌ. 2÷10)÷ በእምነት ጸድቄአለሁ ብሎ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የማይጠብቅ ክርስቲያን መጀመሪያውኑ አልጸደቀም። የጸደቀ ከሆነ ግን መንፈሳዊ ፍሬዎች በሕይወቱ ተንጸባርቀው ይታያሉ።

እነዚህ የማይቃረኑ ዐሳቦች በመሆናቸው ተቃራኒዎች አስመስሎ ለማቅረብ ወይም ለማወሳሰብ መሞከር ትክክለኛ አመለካከት አይደለም። በሕይወታቸው መንፈሳዊ ለውጥ ያልመጣውንና በእምነት የጸደቀ ሰው ፍሬ የማይታይባቸውን የስም ብቻ ክርስቲያኖችን ሁኔታ አይተን÷ ጽድቅ በእምነት ብቻ ሊሆን አይችልም ወደሚል ድምዳሜ ብንመጣ÷ ወይም ደግሞ በእምነት ብቻ ስለጸደቅን የታዘዝነውን ባንፈጽም የዘላለምን ሕይወት የሚከለክለን የለም ወደሚል ጽንፍ ብናጋድል÷ ሁለቱም አስተሳሰቦች ትክክል አይደሉም።

ጽድቅ በእምነት ብቻ መገኘቱን አሌ የሚል ሊኖር እንደማይገባ ሁሉ÷ የጸናውን ሕግ በእምነት መሻርም ከተጠያቂነት አያድንም። «እንግዲህ ሕግን በእምነት እንሽራለንን? አይደለም፤ ሕግን እናጸናለን እንጂ።» (ሮሜ 3÷31)።



## 5.3 የወንጌል ኦሪታውያን

በቀድሞ የኦሪት ሕግና ሥርዐት ያለፉ አይሁድ÷ ክርስቶስ ሰው ሆኖ መመላለስ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ የእግዚአብሔርን ጸጋ በማጣጣል÷ በዐዲስ ኪዳን ዘመንም ሕግ ቀጣይነት ያለው አገልግሎት እንዲሆን የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል።

ከክርስቶስ ጋር ብዙ ጊዜ ይጋጩ የነበረውም ሕጋችንን አስቀረ÷ ወግ ሥርዐታችንን ሻረ በሚለው አቋማቸው ነበር። እርሱ ጌታችን ገና ከመጀመሪያው ጀምሮ «እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ÷ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።» (ማቴ. 5÷17) በማለት ቢናገርም÷ በእጃቸው የነበሩትን የብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ዐሳብ ካለማስተዋላቸው የተነሣ÷ ወይም በእልከኝነት መንፈስ በመያዛቸው÷ ለኦሪት ፍጻሜን ይሰጥ ዘንድ ሰው የሆነውን አምላክ ተቃውመው እስከ ሞት አደረሱት።

ይህ አፍራሽ ተልእኮአቸው በክርስቶስ ላይ ብቻ ሳይወሰን ወደ ተከታዮቹ ሐዋርያትም ተሸጋግሮ ብዙ መከራና ችግር አምጥቶባቸዋል።

የሚገርመው አጽራረ ወንጌል የሆኑት አይሁድ÷ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ሽንጣቸውን ገትረው ብዙ የተከራከሩለትና ሕጋችን የሚሉት÷ በሕግ ያለው ዋና ነገር÷ ማለትም እውነተኛ ፍርድ÷ ምሕረትና ታማኝነት ሳይሆን÷ በዘመነ ኦሪት ጥላና ምሳሌ ሆኖ እንዲያገለግል የተሰጠውንና እነርሱም በየጊዜያቱ የጨመሯቸውን ወግና ሥርዐቶች ነበር። ሰው እነዚህን በመጠበቁ ጻድቅ እንደሚሆን ያስባሉ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: - «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን÷ ከአዝሙድና ከእንስላል÷ ከከሙንም ዐሥራት ስለምታወጡ÷ ፍርድንና ምሕረትንም÷ በሕግ ያለውን ዋና ነገር ስለምትተዉ÷ ወዮላችሁ! ሌላውን ሳትተዉ ይህን ልታደርጉ ይገባችሁ ነበር። ዕውሮች መሪዎች÷ ትንኝን የምታጠሩ÷ ግመልንም የምትውጡ» በማለት ነቅፎአቸዋል፤ (ማቴ. 23÷23-24)።

በዘመነ ሐዋርያትም በክርስቶስ ፍጻሜ ያገኘው ሕግና በኋላ የተጨመረው ወጋቸው÷ ከወንጌል እኩል ስፍራ አግኝቶ በአንጻራዊነት እንዲራመድላቸው ጽኑ ፍላጎት ነበራቸው። ከዚህ የተነሣ ወንጌል ያለ ኦሪት÷ ጥምቀት ያለ ግዝረት አትረባም ይሉ ነበር። ከይሁዲነት ወደ ክርስትና የመጡት አይሁድም እንኳ ሳይቀሩ÷ ከአሕዛብ ወገን የሆኑት ክርስትናን ከመቀበላቸው በፊት÷ በይሁዲነት ውስጥ ማለፍ የግድ እንደሚያስፈልጋቸው በማመን የነርሱን ወግና ሥርዐት እንዲጠብቁ ያስገድዷቸው ነበር። «ከፈሪሳውያን ወገን ግን ያመኑት አንዳንዶቹም ተነሥተው÷ ትገርዟቸው ዘንድና የሙሴን ሕግ እንዲጠብቁ ታዟቸው ዘንድ ይገባል አሉ።» (የሐዋ. ሥራ 15÷5)።

ይሁን እንጂ ይህ ትክክለኛ አካሄድ ባለመሆኑ÷ ሐዋርያት ተሰብስበው በጉዳዩ በመምከርና ወሳኔ በማሳለፍ÷ ወንጌልን መሠረቷ ያደረገችው ቤተ ክርስቲያን የምትመራበትን ሥርዐት በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሠርተዋል:: ይህም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያው ሲኖዶስ እየተባለ የሚጠራውና በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ላይ የተጻፈው ነው::

በመጀመሪያው ሐዋርያዊ ጉዞ ጳውሎስና በርናባስ በተለያዩ የአሕዛብ ከተሞች የክርስቶስን ወንጌል በአስደናቂ ሁኔታ በመስበክ÷ ብዙዎችን እያሳመኑና አብያተ ክርስቲያናትን እያቋቋሙ ባሉበት ሰዓት÷ ሐዋርያት ያላዘዟቸው ሰዎች ከይሁዳ መጥተው በክርስቶስ አምነው ያሉትን አሕዛብ «እንደ ሙሴ ሥርዐት ካልተገረዛችሁ ትድኑ ዘንድ አትችሉም::» በማለት÷ ከወንጌል ወደ ኦሪት ሊመልሷቸው ከጀሉ:: ነገር ግን በዚህ ትምህርት ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ፈጽሞ ሊስማሙ አልቻሉም:: በመካከላቸው ጥልና ክርክር በሆነ ጊዜም ጉዳዩን በኢየሩሳሌም የሚገኙ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች እንዲያዩትና ውሳኔ እንዲሰጥበት ተወስኖ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ::

በኢየሩሳሌም የተሰበሰበው ሲኖዶስም ብዙ ውይይትና ክርክር ካደረገ በኋላ÷ ጴጥሮስ ከአሕዛብ ወገን የሆኑት ወንጌልን ሰምተው እንዲያምኑ÷ በመጀመሪያ እርሱ እንደ ተላከና እግዚአብሔር በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ልዩነት ሳያደርግ÷ ለአይሁድ የሰጠውን መንፈስ ቅዱስን ለአሕዛብም በመስጠት ማረጋገጡን በማስታወስ (የሐዋ. ሥራ 10÷44-47፤ 11÷1-18) ቀጠሎ እንዲህ አለ: - «አባቶቻችንና እኛ ልንሸከመው ያልቻልነውን ቀንበር÷ በደቀ መዛሙርት ጫንቃ ላይ በመጫን እግዚአብሔርን አሁን ስለምን ትፈታተናላችሁ? ነገር ግን በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እንደ እነርሱ ደግሞ እንድን ዘንድ እናምናለን::» (የሐዋ. ሥራ 15÷10-11)::

ሐዋርያው ያዕቆብም በበኩሉ የጴጥሮስን ዐሳብ በመደገፍ «ስለዚህ ከአሕዛብ ወደ እግዚአብሔር የዞሩትን እንዳናስቸግራቸው፤ ነገር ግን ከጣዖት ርኵሰትና ከዝሙት÷ ከታነቀም÷ ከደምም ይርቁ ዘንድ እንድንጽፍላቸው እቈርጣለሁ::» አለ፤ (ቍ. 19-20)::

ሐዋርያት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመሆን የወሰኑትን ውሳኔ በጽሑፍ አስፍረው ችግሩ ወደተነሣበት ቦታ በመላክ÷ በእምነታቸው የተናወጡትን ምእመናን አረጋጓቸው::

የተጻፈውም እንዲህ የሚል ነበር: - «ሐዋርያትና ሽማግሌዎች÷ ወንድሞችም÷ በአንጾኪያና በሶሪያ÷ በኪልቅያም ለሚኖሩ ከአሕዛብ ወገን ለሆኑ ወንድሞች ሰላምታ ያቀርባሉ:: ያላዘዝናቸው ሰዎች ከኛ ወጥተው ትገረዙ ዘንድና ሕግን ትጠብቁ ዘንድ ይገባችኋል ብለው ልባችሁን እያወኩ በቃል እንዳናወጧችሁ ስለሰማን÷ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነፍሳቸውን ከሰጡት ከምንወዳቸው ከበርናባስና ከጳውሎስ ጋር የተመረጡትን ሰዎች ወደ እናንተ እንልክ ዘንድ በአንድ ልብ ሆነን ፈቀድን:: ራሳቸውም በቃላቸው ያንኑ ይነግሯችሁ ዘንድ ይሁዳንና ሲላስን ልከናል:: ለጣዖት ከተሠዋ÷ ከደምም÷ ከታነቀም÷ ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ÷ ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ



ፈቅደናል:: ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ፤ ጤና ይስጣችሁ::» (ቍ. 23-29) ::

ያመኑ አሕዛብን ወደ ኦሪት የመመለሱ እንቅስቃሴ በዚሁ ብቻ ሊገታ አልቻለም:: በገላትያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥም በሌላ ጊዜ ችግር አስነሥቶ ነበር:: በጊዜው ከሐዋርያት መካከል ጴጥሮስ÷ እንዲሁም በርናባስ በዚህ ግብዝነት እስኪሳቡ ድረስ አሕዛብን በአይሁድ ሕግና ሥርዐት ውስጥ እንዲያልፉ ተጽዕኖ የሚያሳድር ተግባር ፈጽመዋል:: ይኸውም ጴጥሮስ አስቀድሞ በአሕዛብ ልማድ ከአሕዛብ ጋር እየኖረ ከእነርሱው ጋር ይበላ ይጠጣ ነበር፤ በኋላ ግን ከያዕቆብ ዘንድ የመጡትን አይሁድ ፈርቶ ለማፈግፈግ ከአሕዛብ ተለየ:: በዚህን ጊዜ ጳውሎስ ኬፋን (ጴጥሮስን) «አንተ አይሁዳዊ ሳለህ በአይሁድ ኑሮ ያይደለ በአሕዛብ ኑሮ ብትኖር÷ አሕዛብ በአይሁድ ኑሮ ሊኖሩ እንዴት ግድ አልሃቸው::» ሲል ተቃወመው፤ (ገላ. 2÷14) ::

የገላትያ መልእክት የተጻፈበት ዋና ዐላማ÷ በአብያተ ክርስቲያናት እየተስፋፋ የመጣውን «ወንጌል ያለ ኦሪት÷ ጥምቀት ያለ ግዝረት አትረባም» የሚለውን የቢጽ ሐሳውያን (ውሸተኞች ወንድሞች) አስተምህሮ በመቃወም እውነተኛውን የመዳን መንገድ ለማሳየት ነው::

አሁን ወደምንገኝበት ዘመን ተመልሰን ስንመለከትም÷ በተለይ በቤተ ክርስቲያናችን ከወንጌል በላቀ ሁኔታ ኦሪታዊ ነገሮች እየተፈጸሙ ይገኛል:: ስለዚህ የሚሰጠው ምክንያት «ኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና ከእስራኤል ቀጥሎ ኦሪትን የተቀበለች አገር ስለ ነበረች÷ ከኦሪት ይጠቅመኛል ያለቻቸውን ነገሮች በዐዲስ ኪዳን ዘመንም ትገለገልባቸዋለች፤» የሚል ነው::

በመሠረቱ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ኢትዮጵያ ከእስራኤል ቀጥሎ ኦሪትን ስለ መቀበሏ የተገለጸ ነገር የለም:: በሌላ በኩል ግን ብዙ ተብሎ ሊሆን ይችላል:: ይህም ኢትዮጵያን በሁሉ ነገር ሰማይ ለማድረስ በመፈለግ የሚደረግ መሆኑ ግልጽ ነው:: የኢትዮጵያ ያልሆኑና ለኢትዮጵያ የተሰጡ ብዙ ነገሮች አሉ፤ አንድ መጥቀስ ቢያስፈልግ እንኳ: - «መልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ ነው» የተባለውን እናገኛለን፤ (የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት ከአለቃ አያሌው ታምሩ ገጽ 66 ተመልከት)::

በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎና ለዘላለም ካህን ሆኖ እንዲኖር በእግዚአብሔር የታቀደው ይህ ሰው÷ ገና ለገና «አባትና እናት÷ የትውልድም ቁጥር የሉትም፤ ለዘመኑም ጥንት ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም÷ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል::» (ዕብ. 7÷3) ስለተባለ ብቻ የትም ውድቆ እንደተገኘና ጠያቂ እንዳጣ ንብረት ተቈጥሮ ኢትዮጵያዊ ተደርጓል:: ኢትዮጵያዊነታችን ባለን ነገር እንጂ ተቀስጦ በተገኘ ጥርቅምቅም ውሸት ሊደምቅ አይችልም:: «በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጕርጕርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?» (ኤር. 13÷23) ::

የእግዚአብሔር ቃል፥ ሕጉ ከእስራኤል ውጪ ኢትዮጵያን ጨምሮ ለሌሎች አሕዛብ እንዳልተሰጠና ፍርዱም እንዳልተገለጠላቸው በግልጽ ይመሰክራል፤ እንግዲህ የቱን እንመን? (መዝ. 147፥8-9፤ ሮሜ 3፥2፤ 9፥4)።

እርግጥ አገራችን ኢትዮጵያ የኦሪትን ሕግ ከእግዚአብሔር አትቀበል እንጂ፥ ከክርስቶስ ልደት በፊት በተለያዩ ስደቶች ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ የመጡ አይሁድ፥ እምነታቸውንና ሥርዐታቸውን ይዘው በመምጣት በሕዝባችን ሕይወት ውስጥ ማሥረጻቸው እሙን ነው። ዛሬ የኛ በምንለው ሥርዐታችንና ባህላችን ውስጥ በአብዛኛው የሚታየው ከአይሁድ የወረስነው ልማድ መሆኑም አይካድም።

የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሶ እስካልተገኘ ድረስ ለጽድቅ ይጠቅማል ባይባልም፥ ማንኛውም ባህል ለተቀበለው ሰው መልካም ነው። ከዚህ አንጻር የእኛም ለእኛ መልካም ነው፤ ነገር ግን ኦሪትና ወንጌል የተደበላለቁበት በመሆኑ፥ ከወንጌል ይልቅ ወደ ኦሪት የማመዘን ሁኔታ ስለሚታይበት በጽድቅ ሕይወት ለመመላለስ ዕንቅፋት እንጂ ጠቃሚ ሆኖ አልተገኘም። አብዛኛዎቹ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ምእመናን በዚህ ቀንበር ሥር ስለወደቁ ጎልቶ የሚታያቸው በሕግ ያለው ዋና ነገር ሳይሆን ያው ከአይሁድ የተወረሰው ጥላና ምሳሌ የነበረው ልማድና ወግ ነው።

ለምሳሌ ሴት ልጅ በወር አበባዋ ወቅት እንደ ርኩስ ነገር ትቈጠራለች፤ አምልኮተ እግዚአብሔር ወደሚፈጸምበት የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ወይም ቅጽር እንዳትገባ ትከለከላለች፤ ይህ ወግ ጠብቆ በሚሠራባቸው አካባቢዎች እንዲያውም በየትኛው መስፈሪያ እንደተለካ ባይታወቅም፥ አርባ ክንድ ትርቃለች፤ መስቀል አትሳለምም፤ የጸሎት መጻሕፍትን አታነብም፤ ወዘተ...።

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መምህራን ስሚ ባያገኙም፥ በዚህ ጉዳይ ርኵሰትና መተላለፍ እንደሌለ መናገራቸው አልቀረም። የሚበዙቱ ግን ይህን አሌ በማለት ሥርዐቱ ሕገ እግዚአብሔር ሆኖ እንዲጠበቅ አጽንተው ያስተምራሉ።

ለትምህርታቸው ሥረ መሠረት የሚያደርጉት የሔዋንን መረገም ነው። «ሔዋንን እግዚአብሔር ሲረግማት፥ ይህችን ዕፀ በለስ እንዳደማሻት አንቺም እንዲሁ በየወሩ ትደሚያለሽ፤» ብሏታል ይላሉ (ቅዳ. አትናቴዎስ ቍ. 30)። እንዲህ የሚሉት ወገኖች የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል አንብበው ያልተረዱና ከተፈጥሮ እንኳ ለመማር ያልቻሉ ናቸው። ነገር ግን የሚሉት እውነት የሆነ ቢሆን እንኳ፥ ክርስቶስ መድኀናችን ስለኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን የዋጀን መሆኑን ረስተዋል፤ (ገላ. 3፥13)።

እግዚአብሔር ሔዋንን በረገመበት ክፍል ውስጥ እነርሱ የሚሉትን ቃል ፈጽሞ አናነብም። «ለሴቲቱም አለ፤ በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ፤ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፤ እርሱም ገዥሽ ይሆናል።» (ዘፍ. 3፥16) ስለዚህ የወር አበባ የእርግማን ውጤት አይደለም።



ተፈጥሮአችን እንደሚያስተምረን ደግሞ፥ የወር አበባ አንዲት ሴት፥ ልጅ እንደትወልድ የሚያስችላት የተፈጥሮ ባለቤት የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። የኦሪት ሕግ በተሰጠበት ጊዜ ግን የወር አበባ የሚያረክስ ሕግ ሆኖ በሕዝቡ መተዳደሪያ ሕግ ውስጥ ተካተተ፤ (ዘሌ. 15፥19-33)። ሕጉ በብሉይ ኪዳን ለነበረው የእግዚአብሔር ሕዝብ (ለእስራኤል) ብቻ የተሰጠ ነው፤ የዐዲስ ኪዳን ምእመናንን ግን አይመለከታቸውም።

ስለ ወር አበባ በኦሪት ሕግ የተደነገገው ዛሬም እንዲፈጸም የሚሹት ክፍሎች፥ ዐሳባቸው በእግዚአብሔር ቃል የተደገፈ ባይሆንም፥ ከዚሁ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ የተሰጡትን ሌሎች ሕጎች ማለትም የለምጻምነትን፥ የሬሳንና ... የመሳሰሉትን ሕጎች እንዲጠብቁ ማድረግ ነበረባቸው። ነገር ግን ይህ ተፈጻሚ አልሆነም። ለምሳሌ ዛሬ ለምጻምነት በሽታ እንጂ እንደ ኦሪቱ ዘመን ከማኅበረሰቡ መገለልን የሚያስከትል ኀጢአት ተደርጎ አይወሰድም፤ (ዘሌ. 13፥45-46)።

እንዲሁም በዘመነ ኦሪት ሬሳን መንካት ያረክስ ነበር። በአጋጣሚ በማደሪያው ድንኳን ውስጥ ሞቶ የተገኘ ቢኖር እንኳን፥ ከእርሱ የተነሣ የማደሪያው ድንኳን የሚረክስበት ሁኔታ ነበር (ዘኍ. 19፥11-19)፤ ዛሬ ግን ይህ ሁሉ የለም።

የኦሪቱን ቤተ መቅደስ እንደተካ በሚያስቡት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ወስጥ ሰው ቢሞት መርከስ የለም። እንዲያውም በውጭ የሞተው ምእመን አስክሬን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል። ታዲያ የወር አበባ ከዚህ በምን ተለይቶ ነው በሴቶች እህቶቻችን ላይ መንፈሳዊ ተጽዕኖና የርኵስነት ስሜት የሚያሳድረው?

እነዚህን ኦሪታዊ ሥርዐቶች መጠበቅ እንደኛ ዐሳብ ለማምለክና ለትሕትና፥ ሥጋን ለመጨቈን የሚረዳን ቢመስለንም፥ ሥጋዊ ባሕርያችን ያለ ልክ እንዳያስቸግረን ለመከልከል አንዳች የሚጠቅመን ነገር የለም። ስለሆነም ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚነግረን እነዚህ የሥጋ ሥርዐቶች ሁሉ በመደረግ ሊጠፉ ተወስነዋል፤ (ቈላ. 2፥20-23)።

አብዛኛው ሰው የተሞላው የኦሪትን ወግና ሥርዐት ዛሬም በሚያስጠብቅ ስብከት በመሆኑ፥ ለነዚህ የሥጋ ሥርዐቶች ይጨነቃል እንጂ፥ በሕግ ላለውና ዛሬም ለጸናው ዋና ነገር ብዙም ግድ የለውም። ለምሳሌ በወር አበባቸው ሰዓት ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመግባት የሚከለከሉት፥ በሌላ ወቅት ዋና የሆነውን ሕግ ጥሰው ቢገቡ ወይም እዚያው ውስጥ ሆነው ቢጥሱ ምንም አይሰማቸውም። ለእነርሱ ኀጢአት የሆነው የወር አበባ እንጂ መስረቅ፥ መመኘት፥ ሐሜት፥ ክፋት፥ ተንኰል፥ ምቀኝነት፥ ጠንቋይ ቤት መሄድ፥ ወዘተ... አይደለም።

ክርስቶስ ሰው መሆን ያስፈለገው እነዚህን አፍአዊ ሥርዐቶች የሰው ልጅ ጠብቆ መጽደቅ ስላቃተው አይደለም። እንደ እነዚህ ያሉትን ሥርዐቶች መጠበቅ የፈሪሳውያን ዋና ተግባራቸው ነበር። እነዚህን ሥርዐቶች በመተላለፍም አብዛኛዎቹ አልተከሰሱም፤ ብዙ ጊዜ ጸሐፍት

ፈሪሳውያንም ራሳቸውን ጻድቅ አድርገው የሚመለከቱና ሌላውን በኃጢአተኝነት የሚፈርጁት፥ ወግ ሥርዐታቸው በመጠበቁና ባለመጠበቁ ነው:: ነገር ግን ጌታችን «እላችኋለሁና፥ ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም::» ሲል ዛሬ የቀረውን ወግና ሥርዐት ብቻ እንደ እግዚአብሔር ሕግ እጠብቃለሁ ማለት ለድኅነት እንደማያበቃ ተናገረ፤ (ማቴ. 5÷20)::

ስለዚህ: - «በአማንኬ ንንሣእ ወንጌለ፥ ዘቦ ውስቴቱ ትሕትና ወፍቅር፥ ወንኅድግ ኦሪተ፥ ዘቦ ውስቴቱ ፍትሕ፥ ወቀትል፥ ቤዛ ነፍስ ህየንተ ነፍስ::»

ትርጓሜ: - «ወንጌልን በእውነት እንያዝ፥ በውስጡ ትሕትናና ፍቅር ያለበትን፤ ኦሪትን ግን እንተው፥ በውስጡ ስለ ነፍስ የነፍስ ቤዛ የሚሆን የሞት ፍርድ ያለበትን::» (ቅዳ. አትናቴዎስ ቍ. 58)



# ክፍል 6 - ታቦት

## 6.1 ታቦት በብሉይ ኪዳን

ታቦት ከግራር ዕንጨት እንዲሠራ በእግዚአብሔር የታዘዘ ሲሆን፥ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል (175 ሳ.ሜ) ወርዱ አንድ ክንድ ተኩል (75 ሳ.ሜ) ሆኖ በሣጥን መልክ የተሠራ ነበር:: በዚህ መለኪያ መሠረት ከተሠራ በኋላ ውስጣዊና ውጫዊ አካሉ በጥሩ ወርቅ እንዲለበጥ፥ አራት ካህናት ለመሸከም እንዲችሉ አራት የወርቅ ቀለበቶችና በቀለበቶቹ ውስጥ የሚውሉ ከግራር ዕንጨት ተሠርተው በወርቅ የተለበጡ መሸከሚያ መሎጊያዎች እንዲሠሩ፥ እንዲሁም የታቦቱ ክዳን ሆኖ በስርየት መክደኛነትም የሚያገለግል ክዳን በታቦቱ ልክ ከጥሩ ወርቅ ተዘጋጅቶ፥ በላዩ ሁለት ኪሩቤል በትይዩ ክንፎቻቸውን ወደ ላይ ዘርግተው የስርየት መክደኛውን በሚሸፍንና ፊቶቻቸው ወደ ስርየት መክደኛው እንዲመለከቱ ሆነው እንዲሠሩ፥ የታቦቱን አጠቃላይ ንድፈ ሐሳብ ለሙሴ ነገረው፤ (ዘፀ. 25÷10-20)::

ሙሴም ከእግዚአብሔር ዘንድ በልቡ ጥበብ የተሰጠውን ሰው ባስልኤልን ጠርቶ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት ታቦቱ እንዲሠራ አደረገ፤ (ዘፀ. 36÷2፤37÷1-9)::

በዚህ ሁኔታ የተሠራው ታቦት ይቀመጥ የነበረው በቤተ መቅደሱ ውስጠኛው ክፍል ውስጥ ነው፤ (ዕብ. 9÷3-4፤ ዘፀ. 26÷33):: ታቦቱም በውስጡ ሁለት ጽላት፥ መና የነበረበትን የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትርን ይዞ ነበር፤ (ዕብ. 9÷4፤ ዘፀ. 25÷21፤ 40÷20፤ 16÷33-34፤ ዘኊ. 17÷10):: በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ግን ከሁለቱ የድንጋይ ጽላት በቀር በታቦቱ ውስጥ ምንም ምን እንዳልተገኘ ተጽፎአል፤ (1ነገ. 8÷9፤ 2ዜና. 5÷10)::

ጽላቱን የተመለከትን እንደሆነ በመጀመሪያ የእግዚአብሔር እጅ ሥራ ነበሩ:: ነገር ግን ሙሴ ጽላቱን ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ከተራራው ሲወርድ በአሮን መሪነት ሕዝቡ የጥጃ ምስል አቁሞ ሲያመልከው በመመልከቱ ተቈጥቶ ጽላቱን ከእጁ ጥሎ ሰበራቸው:: ከዚህ በኋላ ሙሴ እንደሰበራቸው ያሉ ሁለት የድንጋይ ጽላት ጠርቦ እንዲያመጣና የቀድሞዎቹን ዐሥሩን ቃላት እግዚአብሔር ራሱ እንደሚጽፍባቸው ነግሮት እንዲሁ አደረገ:: እግዚአብሔርም ጻፈባቸውና ለሙሴ ሰጠው፤ (ዘፀ. 31÷18፤ 32÷15-16፤ 19፤ 34÷1፤ ዘዳ. 4÷13፤ 10÷1-5) ::

ከዐሥሩ ትእዛዛት ውጪ እግዚአብሔር ኅቡእ የሚባል ስሙንም ሆነ የተገለጸ ስሙን፥ ወይም ሌላ ተጨማሪ ምስልና ሐረግ እንዳልጻፈና እንዳልቀረጸ ግልጽ ነው:: «እግዚአብሔር በተራራው ላይ በእሳትና በደመናው፥ በጨለማውም ውስጥ ሆኖ በታላቅ ድምፅ እነዚህን ቃሎች (ዐሥሩን ትእዛዛት ማለት ነው) ለጉባኤአችሁ ሁሉ ተናገረ፤ <u>ምንም ምን አልጨመረም:: በሁለቱም የድንጋይ ጽላቶች ላይ</u>

ጻፋቸው፤ ለእኔም ሰጣቸው።» (ዘዳ. 5÷22፤ እንዲሁም 10÷4ን ተመልከት)።

በጽላቶቹ ላይ የተጻፉት ዐሥሩ ቃላት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን የሚያሳዩ በመሆናቸው በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ምስክር ሆነው ቆመዋል፤ (ዘፀ. 34÷28፤ ዘዳ. 4÷13)። በመሆኑም ጽላቶቹ የምስክር ወይም የቃል ኪዳን ጽላት ሲባሉ÷ ታቦቱም የምስክር ወይም የቃል ኪዳን ታቦት ተብሎ ተጠርቷል፤ (ዘፀ.25÷21-22፤ 30÷6፤ 32÷15፤ ዘኍ.4÷5፤ ኢያ.3÷3፤ 6፤ 14፤ 4÷9፤ 15-18)።

የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት የጽላቶቹ ማስቀመጫ ከመሆኑ ባሻገር የሰጠው ዋና አገልግሎት÷ እግዚአብሔር ከእስራኤል መሪዎች ጋር በመገናኘት ትእዛዝና ረድኤትን ለሕዝቡ ለመስጠት እንዲችል÷ የሕዝቡንም ልመናና ጥያቄ መሪዎቻቸው ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርቡ ለማድረግ ነው፤ (ዘፀ. 25÷22፤ 30÷6፤ 32÷15፤ ዘኍ. 7÷89፤ መሳ. 20÷27-28)። ስለዚህ ታቦቱ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል መኖሩን አመልካች ነበር፤ (2ሳሙ. 7÷5-6)።

እስራኤላውያን ከምድረ ግብጽ ወጥተው በምድረ በዳ ተጓዦች ሆነው በኖሩበትና ተስፋይቱን ምድር እስኪወርሱ ድረስ ባለው ጊዜ ታቦቱን ተሸክመው ይጓዙ ነበር። የሚሸከሙትም ካህናት ናቸው (ዘዳ. 10÷8፤ ኢያ. 3፤ 1ዜና. 15÷2፤ 14-15፤)። ካህናት ታቦቱን የመሸከማቸው ተግባር ቀጣይነት የነበረው ግን እስራኤላውያን በአገራቸው መኖር ሲጀምሩና አንድ ቋሚ ቤተ መቅደስ እስኪታነጽ ድረስ ነበር። ይህ ከሆነ በኋላ ግን ታቦቱን ከመሸከም ዐርፈዋል፤ (2ዜና. 35÷3)።

ታቦቱ በቤተ መቅደስ ስፍራውን ከያዘ በኋላ በእስራኤላውያን ዘንድ÷ ለበዓላትም ሆነ በሌላ ምክንያት በዓለ ንግሥ ተደርጎ÷ በካህናቱ ተሸካሚነት ከመቅደሱ ወጥቶ÷ መቅደሱን ዞሮ ወደ ስፍራው የሚመለስበት ሥርዐት ፊጽሞ አልነበረም። እርግጥ አንዳንድ ጊዜ በጦርነት ወቅት ታቦተ ሕጉን ወደ ጦር ሜዳ ይዘውት ይወጡ እንደነበር አይዘነጋም።

ሌላው ነጥብ ታቦቱ በእግዚአብሔር ስም ብቻ እንጂ በሌላ በማንም ስም አለመጠራቱ ነው። ይህን ለማረጋገጥ ካስፈለገ ስለ ታቦቱ የተጻፈውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መመልከት ይቻላል። ለአብነት ያህል የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ብንመለከት ታቦቱ «የእግዚአብሔር ታቦት» ወይም «የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት» ተብሎ ተጠርቷል፤ (ኢያ. 4÷7፤ 1ሳሙ. 3÷3፤ 4÷4፤ 5÷11፤ 21-22፤ 2ሳሙ. 6÷1-17፤ 15÷24-29፤ 1ዜና. 13÷1-14)።

እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጠው በስሙ የተጠራውን አንድ ታቦት ብቻ ሲሆን÷ በዘመናቸው ሁሉ የነበረውም ያው አንዱ ታቦት ብቻ ነበር። ከዚህ ውጪ ያንን አስመስለው ብዙ ታቦታትን እንዲሠሩና እንዲያራቡ አልታዘዙም፤ እነርሱም ቢሆን ይህን አላደረጉም።

ከብዙ ዘመን በኋላ እስራኤላውያን በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል ምስክርና ቃል ኪዳን ሆኖ እንዲጠበቅ የተሰጠውን ሕግ አፍርሰው በመገኘታቸው÷ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ሌላ ዐዲስ ቃል ኪዳን



እንደሚገባና÷ የታቦቱም ሆነ የጽላቱ አገልግሎት ስለሚያበቃ ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ታቦት ብለው እንደማይጠሩት÷ ልብ እንደማያደርጉት÷ እንደማይሹትና ከእንግዲህ ወዲያ እንደማይደረግ በአጽንዖት ተናገረ፤ (ኤር. 3÷16)።

ቃል ኪዳኑን በማፍረሳቸው ምክንያት እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በባቢሎናውያን ሲያስማርክ÷ የታቦቱም ታሪክ እዚሁ ላይ ይደመደማል። የባቢሎን ንጉሥ ባሪያ የዘበኞቹ አለቃ ናቡዘረዳን ቤተ መቅደሱን በዝብዞ በውስጡ የነበሩትን የወርቅ÷ የብርና የነሐስ የተቀደሱ ዕቃዎች ሁሉ ወደ ባቢሎን ካፈለሰ በኋላ ቤተ መቅደሱን በእሳት አቃጥሎታል። ይሁን እንጂ በተማረኩት የተቀደሱ ዕቃዎች ዝርዝር ውስጥ ስለ ታቦቱ የተወሳ ነገር የለም፤ (2ነገ. 25÷8-17፤ 2ዜና. 36÷7)።

ሰባው የምርኮ ዘመን (ዘመነ ጼዋዌ) አብቅቶ ምርኮኞቹ የይሁዳ ሰዎች ወደ ምድራቸው ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለሱ÷ ወደ ባቢሎን ተማርኮ የነበረውን የእግዚአብሔርን ቤት ዕቃ ሁሉ ይዘው ተመልሰዋል። በተመለሱት የተቀደሱ ዕቃዎች ዝርዝር ውስጥ አሁንም ታቦቱ አልተጠቀሰም፤ (ዕዝ. 1÷7-11)። ይህም የሆነበት ምክንያት በኤር. 3÷16 የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ነው። ስለዚህ ከባቢሎን ምርኮ መልስ ቅሬታዎቹ የእስራኤል ልጆች በምድራቸው ላይ መርባትና መብዛት ሲጀምሩ÷ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ብለው አልጠሩም።

## 6.2 የዐዲስ ኪዳን ታቦት

እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በተለያዩ ስልቶችና መንገዶች ለብሉይ ኪዳን ሰዎች ተናግሮ ነበር፤ (ዕብ. 1÷1)። ከነዚህም መካከል በታቦቱ አማካይነት ራሱን ለእስራኤል መሪዎች ገልጦ ሕዝቡን ያነጋገረበት መንገድ አንዱ ነው ለማለት ይቻላል። ታቦት በብሉይ ኪዳን ዘመን የሰጠው ዋና አገልግሎት ይህ ነውና። ሆኖም ታቦት እግዚአብሔር እስከ መጨረሻው የሚናገርበት ብቸኛ መንገድ አልነበረም።

ስለዚህ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ታቦት አለመወሳቱ ሊያስገርመን አይገባም። ይሁንና ብሉይ ኪዳን በዐዲስ ኪዳን ለመተካት የተቀጠረለት ጊዜ ገና ሳያበቃ÷ ታቦት አገልግሎት መስጠት ማቋረጡ ጥያቄ ማስነሣቱ አይቀርም። ለዚህ ክሥተት ዋና ምክንያት የሚሆነው የእስራኤል ልጆች በጽላቱ ላይ ተጽፎ የተሰጣቸውን ቃል ኪዳኑን አፍርሰው መገኘታቸው ነው፤ (ኤር. 31÷32)። ነገር ግን ያም ባይሆን ታቦት ፍጹም የሆነው እስኪመጣ ድረስ ጥላና ምሳሌ ሆነው በጊዜያዊነት ከተሰጡት ነገሮች መካከል አንዱ በመሆኑ÷ ብሉይ ኪዳን ፍጻሜን ሲያገኝ የታቦትም አገልግሎት ማክተሙ አይቀርም ነበር።

የብሉይ ኪዳን ታቦት ከባቢሎን ምርኮ ጀምሮ አገልግሎት መስጠቱን እንደማይቀጥል የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ራሳቸው አስረግጠው መስክረዋል፤ (ኤር. 3÷16)።

ጊዜው ደርሶ ትንቢቱ መፈጸሙንና በዐዲስ ኪዳን ከተገለጠው የጽድቅ አገልግሎት የተነሣም÷ ታቦት ቀድሞ የነበረውን የአገልግሎት ክብር ማጣቱንና መሻሩን ደግሞ የዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መስክረዋል። «ዳሩ ግን የእስራኤል ልጆች ስለዚያ ስለተሻረው ስለፊቱ ክብር የሙሴን ፊት ትኩር ብለው መመልከት እስኪሳናቸው ድረስ÷ ያ በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀረጸ የሞት አገልግሎት በክብር ከሆነ÷ የመንፈስ አገልግሎት እንዴት ይልቅ በክብር አይሆንም? የኵነኔ አገልግሎት በክብር ከሆነ÷ ይልቅ የጽድቅ አገልግሎት እንዴት በክብር አብዝቶ ይበልጣልና። ያ የከበረ እንኳ እጅግ በሚበልጠው ክብር ምክንያት በዚህ ነገር ክብሩን ዐጥቷልና። ያ ይሻር የነበረው በክብር ከሆነ÷ጸንቶ የሚኖረውማ እጅግ ይልቅ በክብር ሆኗልና፤» (2ቆሮ. 3÷7-11)።

የታቦት አገልግሎት በዚህ ሁኔታ መሠረት ቢያበቃም÷ እግዚአብሔር ግን ሕዝቡን ማነጋገሩ አልቀረም። እንዲያውም በዐዲስ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ሕዝቡን ያነጋገረበት መንገድ በብሉይ ኪዳን ዘመን ካነጋገረበት መንገድ በእጅጉ የተሻለና የበለጠ ነው። ይኸውም ለሚመጣው አማናዊ ነገር ምሳሌ በሆኑ በተለያዩ መንገዶችና ስልቶች ሳይሆን÷ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚመሰክረው «ሁሉን ወራሽ ባደረገው÷ ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ÷ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለኛ ተናገረን።» (ዕብ. 1÷2)።

የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአባቱን መልእክት ለኛ በመናገሩ÷ የዐዲስ ኪዳን መካከለኛ መሆኑን ብቻ ሳይሆን



የታቦቱን አገልግሎት መተካቱን ጭምር ወይም ደግሞ የዐዲስ ኪዳን አማናዊ ታቦት መሆኑን ተገንዝበናል፤ (ዮሐ. 8÷26)።

ዛሬ ታቦት ባለመኖሩ ቀድሞ የነበረው የታቦት አስፈላጊ አገልግሎትና ስፍራ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መተካቱን የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ሳይቀሩ መስክረዋል። በምስክርነታቸውም ያ የቀድሞው ታቦት በምሳሌነት ኢየሱስ ክርስቶስን ለማሳየት እስከ ጊዜው የተሰጠ እንጂ÷ ራሱን ችሎ ለራሱ አገልግሎት የቆመ አለመሆኑን አስረግጠው ተናግረዋል።

> «ታቦት በወርቅ ልቡጥ እምኵለሄ ዘግቡር እምዕፀ ዘኢይነቅዝ፤ ይትሜሰል ለነ ዘእግዚአብሔር ቃለ፤ ዘኮነ ሰብአ ዘእንበለ ፍልጠት ወኢውላጤ።»
>
> ትርጓሜ፡ - «ከማይነቅዝ ዕንጨት ተሠርቶ÷ ሁለንተናው በወርቅ የተለበጠው ታቦት÷ ያለመለያየትና ያለመለወጥ ሰው የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል (ኢየሱስ ክርስቶስን) ይመስልልናል።» (ውዳ. ማርያም ዘእሑድ)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ታቦት መባሉን ሲገልጽ ደግሞ ሊቀ ቄርሎስ እንዲህ ብሏል፡ -

> «ወእምድኅረዝ ኮነ ሰብአ ተሰምየ ብእሴ÷ ወመሲሐ÷ ወኢየሱስሃ÷ ወታቦተ÷ ወዐራቄ÷ ወበኵረ ለዘሰከቡ÷ ወበኵረ ለዘይትነሣእ እሙታን÷ ወርእሰ ሥጋሃ ለቤተ ክርስቲያን።»
>
> ትርጓሜ፡ - «ሰው ከሆነ በኋላም ብእሲ÷ የተቀባ÷ ኢየሱስ÷ ታቦት÷ አስታራቂ÷ ለሙታን በኵር÷ ከሙታን ወገን ለሚነሣም በኵር÷ የቤተ ክርስቲያን ራስ ተባለ።» (ሃይ. አበ. ምዕ. 81 ክፍ. 51 ቍ. 8)።

በሌላም በኩል ነቢዩ ኤርምያስ ሕጉ በቀድሞው ጽላት ላይ ተጽፎ በታቦቱ ውስጥ መቀመጡ ስለሚያበቃ÷ እንደ ገና በሌላ ዐዲስ የድንጋይ ጽላት ላይ ሳይሆን በሕዝቡ ልብ ላይ ሕጉን እንደሚጽፈውና እንደሚያኖረው በተናገረው መሠረት÷ የዐዲስ ኪዳን ጽላት የምእመናን ልብ ሆኗል፤ (ኤር. 31÷31-34፤ መዝ. 39(40)÷8፤ 2ቆሮ. 3÷3)።

በመሆኑም ሐዋርያትም ሆኑ ተከታዮቻቸው ክርስቲያኖች÷ እንደ ብሉይ ኪዳን ሰዎች በጽላት የተጻፈን ሕግ አልተቀበሉም። ይህንንም ሲያስረዳ ሊቁ ዮሐንስ አፈ ወርቅ የዕብራውያንን መልእክት በተረጐመበት ድርሳኑ እንዲህ ብሏል፡ -

> «ወሐዋርያትሰ ኢነሥኡ ምንተኒ ወኢተወፈዩ ዘተጽሕፈ በረቅ÷ አላ ተወክፉ በሰሌዳ ልቦሙ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ»
>
> «ሐዋርያት ግን በብራና የተጻፈ ሕግ አልተቀበሉም፤ የመንፈስ ቅዱስን ሀብት በልቡናቸው ሰሌዳነት ተቀበሉ እንጂ።» (14ኛ ድርሳን ቁጥር 140-141 እንዲሁም 8ኛ ድርሳን ቍጥር 10ን ተመልከት)።

## 6.3 ጥላውንም አካሉንም የማይወክል ታቦት

የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ በዓለም ላይ ካሉት ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶም ሆነ ከሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ለየት የሚያደርጋት፥ በክርስትናዋ ውስጥ የኦሪት ነገሮችን ይዛ መገኘቷ መሆኑ በተደጋጋሚ ተገልጿል:: ይህም ከመጀመሪያው ጀምሮ ቤተ ክርስቲያኒቱን ኦሪታዊት እያሰኘ የሰላ ትችት ሲያሰነዝርባት መቆየቱን በመቅድሙ ላይ ተመልክተናል::

ታዲያ የወንጌልን መንፈሳዊ ጣዕም ያልቀመሱት ተከታዮቿ፥ በያዘቻቸው የኦሪት ነገሮች ልባቸው ነሁልሎ ሲኩራሩና ኦሪታዊነቱን ለቤተ ክርስቲያኒቱ ትክክለኛነት እንደ ዋና ነገር ሲጠቃቅሱት፥ የወንጌሉ ብርሃን በልባቸው የበራ ምእመናኖቿ ደግሞ ለእናት ቤተ ክርስቲያን ማፈሪያና አንገት ማስደፊያ በሆነው በዚህ ጉዳይ፥ እያዘኑና እየጸለዩ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሙሉ በሙሉ ከኦሪት ወደ ወንጌል ዘወር የምትልበትን ጊዜ በናፍቆት ይጠባበቃሉ::

አንዳንድ ጊዜ ግን እንዲያው ለስሙ የኦሪትን ነገሮች ይዛለች ይባላል እንጂ፥ አንዳንዶቹ የያዘቻቸው ነገሮች ከስማቸው በቀር ከኦሪቱ ጋር ምንም መመሳሰል የላቸውም:: ዛሬ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ይዛ የምትገኘው ታቦት ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ነው:: ታቦት በብሉይ ኪዳን እንደነበር ይታወቃል:: የዛሬው በቤተ ክርስቲያናችን የሚገኘውና «ታቦት» ተብሎ የሚጠራው ከብሉዩ ታቦት ጋር የሚመሳሰልበትን ነጥብ ለማግኘት ያስቸግራል::

ስለ ብሉይ ኪዳኑ ታቦት በማስረጃ አስደግፈን ካሁን በፊት በስፍራው ስለተመለከትን፥ እዚህ ላይ መድገሙ ወረቀት መፍጀትና አንባቢን ማሰልቸት ስለሚሆን፥ ከዋና ዋና ማነጻጸሪያ ነጥቦች በቀር ብዙውን ዝርዝር ሁኔታና አስረጂ ጥቅሶችን ትተንና የታለፉ ጉዳዮችን አንሥተን በንጽጽር ማየቱ፥ የነገሩን እውነተኛነት ስለሚያረጋግጥልን፥ የብሉይ ኪዳንን ታቦት ከኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ታቦት ጋር ቀጥሎ በማነጻጸር እንመለከታለን:: (የሁለቱን ልዩነት ለማነጻጸር «የብሉይ ኪዳን ታቦት» በሚለው ሥር የሚገኘውን ተራ ቍጥር «የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ» ታቦት በሚለው ሥር ካለው ተመሳሳይ ቍጥር ጋር ያነጻጽሩ)::

<u>የብሉይ ኪዳን ታቦት</u>

1. በቍጥር አንድ ብቻ ነበር
2. አራት ካህናት የሚሸከሙት ሆኖ እግዚአብሔር በሰጠው መለኪያ መሠረት በትልቅ ሣጥን መልክ የተሠራ ነው:: ለሁለቱ የድንጋይ ጽላት ማስቀመጫም ነው::
3. ጽላቶቹ ሁለት ብቻ ሲሆኑ ከድንጋይ የተጠረቡና በፊትና በጀርባቸው ዐሥሩ ቃላት ብቻ የተጻፉባቸው ነበሩ፤ የጻፈባቸውም ሙሴ ወይም ሌላ ፍጡር ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር ነው::
4. ካህናት የተሸከሙት እስራኤላውያን ተንዦች በነበሩበት ዘመን ብቻ ነበር:: ወደ ርስታቸው ገብተው መኖር ከጀመሩ በኋላ ግን ታቦቱ በበዓለ ንግሥ ስም ከስፍራው አልተንቀሳቀሰም::



በዔሊ ዘመን ግን ካህናቱ ወደ ጦርነት ይዘውት ወጥተው የነበረ ቢሆንም፥ በፍልስጥኤማውያን እንዲማረክ ሆኖ በኋላ በብዙ ክብር ተመልሷል፤ (1ሳሙ. 4-6):: ከዚያም በአሚናዳብ ቤት ለ20 ዓመታት (1ሳሙ. 7፥2)፥ በአቢዳራ ቤት ደግሞ ለ3 ወራት ተቀምጧል፤ (1ሳሙ. 6፥11፤ 1ዜና. 13፥14)::

ከዚህ በኋላ ዳዊት ድንኳን አስተክሎ በድንኳን ውስጥ እንዲኖር አደረገ፤ (1ዜና. 15፥1-15):: በመቀጠልም ሰሎሞን አባቱ ዳዊት ካስተከለለት ድንኳን ውስጥ ታቦቱን አስወጥቶ፥ ወደ አነጸው መቅደስ ውስጥ አስገባው፤ (1ነገ. 8፥1-11፤ 2ዜና. 5፥2-14)::

ከላይ በተዘረዘሩት የተለያዩ ምክንያቶች ዳዊትና ሰሎሞን ታቦቱ አንድ ስፍራ ይዞ እስኪቀመጥ ድረስ፥ ከቦታ ቦታ ለማዘዋወር ሲባል ካህናቱ እየተሸከሙ ልዩ በዓል የተደረገ ቢሆንም፥ ከዚያ በኋላ ግን ቀን ተወስኖለትና የታቦቱ በዓለ ንግሥ ተብሎ ሲከበር በእስራኤላውያን ታሪክ ውስጥ ፈጽሞ አልታየም፤ አልተሰማምም:: ሌላው ቀርቶ እስራኤላውያን እንዲያከብሯቸው በታዘዙት በዓላት ላይ እንኳ ታቦቱን እንዲያነግሡ የተሰጣቸው መመሪያ ባለመኖሩ ታቦቱን አላነገሡም:: የእግዚአብሔር ቃል እንዲያውም መቅደስ ከተሠራ በኋላ ካህናቱ ታቦቱን ከመሸከም ማረፋቸውን ይናገራል፤ (2ዜና. 35፥3) ::

5. ታቦቱ የተጠራው በእግዚአብሔር ስም ብቻ ነው::
6. የሰጠው ዋና አገልግሎት ሕዝቡን በመሪዎቻቸው (በካህናት) አማካይነት ከእግዚአብሔር ጋር ማገናኘት ነበር:: ከዚህ በቀር የኀብስት ገበታም ሆነ ሌላ መሠዊያ ሆኖ ያገለገለበት ሁኔታ ፈጽሞ የለም::

<u>የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ታቦት</u>

1. ቍጥሩ እጅግ ብዙ ነው፤ ይህን ያህል ይሁን ተብሎ የተወሰነ ቍጥር ባለመኖሩም ወደፊት ቍጥሩ እየጨመረ እንደሚሄድ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል::
2. አንድ ቄስ ብቻውን የሚሸከመው መሆኑ አንድ ልዩነት ሲሆን፥ እንዲሁ በልማድ ጽላት የሚባለው ዝርግ ሰሌዳ ታቦትም ተብሎ ይጠራል እንጂ፥ በታቦት ስም ለመጠራት የሚያበቃ የታቦት መልክና አሠራር ፈጽሞ የለውም::

   ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ በመጽሐፋቸው እንደሀ ብለዋል: - «... በአሁኑ ጊዜ የጽላት ማኅደር ታቦት ስለሌለ የጽላት ማኅደር የሆነው መንበር ነው:: «ወይዑዱ ታቦተ» ሲል መንበሩን እንደሆነ ያመለክታልና::» ካሉ በኋላ ይህም አገላለጽ ፈራሽ መሆኑን በሌላ አስረጂ ሲገልጹ: - «... ሆኖም መንበሩን ለይቶ መንበረ ታቦት፥ ምሥዋዕ ሲለው ይገኛል::» ብለዋል:: በመቀጠልም ልማዳዊውን ስያሜ ሲያስረዱ: - «... እንደ ደንቡ ጽላት ወይም ጽሌ መባል ይገባዋል:: ምክንያቱም ታቦት

የሚባለው የጽላቱ ማኅደር ነውና:: በአሁኑ ጊዜ ግን ጽላትም ሲሉ÷ ታቦትም ሲሉ ያኑ ጽላቱን ነው::» ብለዋል፤ (ትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጽሐፍ ገጽ 132)::

3. አንድ ጊዜ ታቦት በሌላ ጊዜ ጽላት መባሉ የሚያደናግር ቢመስልም÷ በሁለቱም ስም የሚጠራው ያው አንዱ ዝርግ ሰሌዳ ነው:: የሚሠራውም ዐልፎ ዐልፎ ከዕብነ በረድ÷ አብዛኛውን ጊዜ በተለይም ደግሞ በዘመናችን ከዕንጨት ነው:: የጽላቶቹን መጠን በተመለከተ አንድ ወጥ በሆነ መስፈርት ሳይሆን እንደ ሠሪው አለካክ በተለያየ መጠንና ውፍረት የተሠሩ ናቸው::

በሰሌዳው ላይ ዐሠርቱ ቃላት እንደተጻፈ አድርገው ብዙዎች በመናገራቸው ሕዝቡ ይህንኑ ተቀብሎ ይኖራል:: እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ነው፤ በአገራችን ጽላቶች ላይ ዐሠርቱ ቃላት የማይጻፍባቸው መሆኑን ስለአሠራሩ የሚያስረዳውን መጽሐፍ (የቅዳሴ ማርያም አንድምታ ትርጓሜ) በመመልከት ለማረጋገጥ ይቻላል:: የሚጻፉትና የሚቀረጹት ሌሎቹ ነገሮችም ቢሆኑ ሰው እንጂ እግዚአብሔር ያልጻፋቸውና ያልቀረጻቸው ናቸው:: የቅዳሴ ማርያም አንድምታ በአገራችን ጽላቶች ላይ የሚጻፈውንና የሚቀረጸውን አስመልክቶ የሚከተለውን ያትታል: -

**የሚጻፈው: -**

ሀ. ታቦቱ የማርያም÷ የኢየሱስ÷ የዮሐንስ ወንጌላዊ ከሆነ በመጀመሪያ አልፋ ወኦ የሚለው የጌታ ስም÷ ቀጥሎ የዮሐንስ ወንጌላዊ÷ በመጨረሻም ምስለ ፍቁር ወልዳ (ማርያም ከተወዳጅ ልጇ ጋር)::

ለ. ታቦቱ የሰማዕት÷ የጻድቅ ከሆነ በመጀመሪያ የጌታ÷ ከአጠገቡ የዮሐንስ ወንጌላዊ÷ ቀጥሎ የጽላቱን ባለቤት (የሰማዕቱን ወይም የጻድቁን ስም) በሦስተኛ ደረጃ ምስለ ፍቁር ወልዳ::

**የሚቀረጸው (የሚሣለው):** - ከላይ የሥላሴ÷ ዝቅ ብሎ የእመቤታችን÷ ከዚያም ሰማዕትም ጻድቅም ቢሆን የጽላቱ ባለቤት ይቀረጻል:: (ቅዳ. ማርያም በኀበ ኵሉ መካነ ርእስት አንቲ የሚለውን ሐተታ ተመልከት)::

በዚህ ውስጥ በመላእክት ስም ስለሚቀረጸው ጽላት የተባለ ነገር የለም::

4. የአገራችን ጽላት እልፍ አእላፋት እንደመሆናቸው መጠን÷ በቊጥራቸው ልክ በዓለ ንግሥ ተሠርቶላቸዋል፤ ባማሩና ባሸበረቁ መጐናጸፊያዎች አጊጠው÷ በቀሳውስት ተሸካሚነትና በሕዝቡ አጃቢነት ከየመቅደሶቻቸው ወጥተው ሕንጻውን ሦስት ጊዜ በመዞር ይዘመርላቸዋል÷ ይዘፈንላቸዋል÷ ይሰገድላቸዋል:: መቼም በዚህ ሁኔታ እየተመለከ ያለውን ታቦት ከኦሪቱ ታቦት ጋር ማመሳሰል ብርሃንና ጨለማ አንድ ናቸው ከማለት በምንም አይለይም:: እነዚህ የአገራችንን ታቦታት ከሚሰጣቸው አምልኮና ስግደት አንጻር እናመሳስል ከተባለ ግን÷



ሊመሳሰሉ የሚችሉት በኢሳ. 44÷12-20፤ ኤር. 10÷3-5፤ 8-9፤ 14-15 ላይ ከተገለጸው ጋር ነው::

5. በአምላክ ስም የተጠሩ ጥቂቶች ቢኖሩም÷ አብዛኛዎቹ በሚታወቁና በማይታወቁ ቅዱሳን መላእክትና ሰዎች ስም የተሰየሙ ናቸው::

6. አገልግሎቱ የሥጋሁ ወደሙ መፈተቻና ማስቀመጫ ነው:: ይህንንም የቤተ ክርስቲያን አባቶች በየመጽሐፎቻቸው አስረድተው ጽፈዋል::

ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ: - «የጻሕሉና የጽዋው ማስቀመጫ÷ የመሥዋዕቱ መክበሪያ ታቦት ወይም ጽላት ይባላል::» (ትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጽሐፍ ገጽ 132)

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስም: - «የደብተራ ኦሪት ጽላት እግዚአብሔር በደመና ተከናንቦ ሙሴንና አሮንን የሚያነጋግርበት÷ ለእስራኤል ብቻ በረድኤት የሚገለጽበት ዙፋን ነበር:: ይህ ግን (የአገራችንን ታቦት ማለታቸው ነው) የአምላክ ሥጋና ደም የሚፈተትበት ... የምሕረት ምሥዋዕ ነው::» (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 109)::

እንግዲህ ስሙ ብቻ ታቦት ወይም ጽላት ይሰኝ እንጂ÷ በአሠራር÷ በይዘትና በአገልግሎት ከኦሪቱ ታቦትና ጽላት ጋር ፈጽሞ አይመሳሰልም:: ይህን ባለማስተዋል ግን አንዳንድ ወገኖቻችን በስሙ ከተጠራ አይቀር ብለው ስለ ኦሪቱ የእግዚአብሔር ታቦት በብሉይ ኪዳን የተጻፈውን ሁሉ÷ ለዚህኛው ሰጥተው በመተርጐም ታቦታችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው በማለት ክርክር ያነሣሉ::

ያልተጻፈለትን እየጠቀሱ መከራከሩ ብዙ እንደማያዋጣ የተረዱት አልረታ ባዮች ደግሞ÷ ለታቦቱ የምንሰግደው የአክብሮት ስግደት ነው ከማለት ዐልፈው ተርፈው÷ በታቦቱ ላይ የተጻፈው የጌታ ስም በመሆኑ በፊልጵስዩስ 2÷10 መሠረት ታቦቱ ላይ ለተጻፈው ስሙ ነው የምንሰግደው ሲሉ ይደመጣሉ:: ይህን አባባል ገና ከእነርሱ ሰማን፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን እንዲህ አላስተማረንም:: ስሙን የሆነ ነገር ላይ ጽፈንና ከፊታችን አድርገን እንስገድ ከተባለ ለጌታ በእውነትና በመንፈስ መስገዱ ዋጋ ሊያጣ ነው፤ (ዮሐ. 4÷23-24)::

በፊል.2÷10 ላይ የምናነበው ቃል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዝቅ በማድረግ እስከ መስቀል ሞት ድረስ ታዛዥ በመሆኑ÷ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ እንዳደረገውና ከስም ሁሉ በላይ ያለውን ስም እንደሰጠው÷ በዚህም ምክንያት በሰማይና በምድር÷ ከምድርም በታች ያሉት ፍጥረታት ሁሉ በኢየሱስ ስም እንዲንበረከኩና መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር የኢየሱስን ጌትነት እንደሚመሰክር የሚናገር ነው::

ቃሉን እነርሱ በሰጡት ትርጉም መሠረት እንቀበለው ቢባል እንኳ÷ ስመ አምላክ ተጻፈበት የሚባለው ጽላት የሚገኘው በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ብቻ ስለሆነ÷ በሰማይና ከኢትዮጵያ ምድር ውጪ ባለው

ምድር፥ ከምድርም በታች ያለው ፍጥረት በኢየሱስ ስም መንበርከኩ ፋይዳ ላይኖረው ነው ማለት ነው።

ይህንና የመሳሰለውን ስንመለከት ታቦት እየተባለ የሚጠራው ዛሬ በሕዝቡ ልብ ትልቅ ስፍራን ያገኘው እንዲህ በቀላሉ አለመሆኑን እንረዳለን። የታቦቱ ፈጣሪዎች ተቀባይነትን እንዲያገኙላቸው የእግዚአብሔርን ቃል ትርጉም እስከ ማዛባት የደረሰ ሽፍጥ በመሥራት ብዙ ደክመውለታል። ከድካማቸው ውስጥ የማይዘነጋው በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረው የእግዚአብሔር ታቦት ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል በማለት የፈጠሩት ታሪክ ነው።

ለዚህ ታሪክ እንደ መነሻ የሚጠቀሰው ንግሥተ ሳባ ሰሎሞንን የመጐብኘቷ ታሪክ ነው፤ (1ነገ. 10፥1-13)። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ካስፈረው ታሪክ ውጪ ይህን ጫፍ ይዞ ክብረ ነገሥት የተባለው መጽሐፍ፥ ንግሥቲቱ ወደ ምድሯ ስትመለስ ከሰሎሞን ፀንሳ እንደተመለሰችና ቀዳማዊ ምኒልክን እንደ ወለደች፥ ቀዳማዊ ምኒልክም ሲያድግ አባቱን ሊተዋወቅ እንደ ሄደና በዚያ ቆይታ አድርጎ ሲመለስ፥ ከአባቱ ከተሰጡት ካህናትና ሌዋውያን ጋር በመመሳጠር የእስራኤላውያንን ታቦት በስርቆት ወደ ኢትዮጵያ እንዳመጡት ይተርካል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በቃል የሚነገር ታሪክም አለ። ይኸውም በኢየሩሳሌም መቅደስ ሁለት ታቦታት እንደ ነበሩና፥ አንደኛው ታቦተ ማርያም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ታቦተ ሚካኤል እንደ ሆነ፥ ንጉሡ ሰሎሞንም ከሁለቱ መካከል ለልጁ ለቀዳማዊ ምኒልክ እንዲሰጥ የፈቀደው ታቦተ ሚካኤልን እንደነበር፥ ነገር ግን ካህናቱ አለዋውጠው ታቦተ ማርያምን እንዳመጡ የሚተርክ ነው።

ባፍም በመጣፍም ሲነገር የመጣውን ይህን ትረካ እንዳንቀበል የሚያደርጉ ብዙ እውነታዎች አሉ። ዋናው መሠረታዊ ምክንያት ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት የሚናገረው ነው።

በሰሎሞን ዘመን ወደ ኢትዮጵያ መጣ የተባለው ታቦት፥ ከሰሎሞን በኋላ ብዙ ዓመታት ቆይቶ በነገሠው በኢዮስያስ ዘመን በዚያው በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ እንደነበረ 2ዜና. 35፥3 ያስነብበናል። «ቅዱሱን ታቦት የእስራኤል ንጉሥ የዳዊት ልጅ ሰሎሞን በሠራው ቤት ውስጥ አኑሩት።»።

እንደሚታወቀው ሰሎሞን ከ971-931 ዓ.ዓ የነገሠ የእስራኤል ንጉሥ ነው። ኢዮስያስ ደግሞ ከ639-609 ዓ.ዓ ድረስ የነገሠ የይሁዳ ንጉሥ ነው። በሰሎሞንና በኢዮስያስ መካከል የ332 ዓመት ልዩነት አለ ማለት ነው። ሰሎሞን ከሞተ ከ332 ዓመት በኋላ እንኳ ታቦቱ ከኢየሩሳሌም አልወጣም ነበር። ስለዚህ ከ332 ዓመት በፊት በሰሎሞን ዘመን ወደ ኢትዮጵያ መጣ የሚለው የክብረ ነገሥት ትረካና ሌላውም አፈ ታሪክ በቀጥታ ፈጠራ ነው ከሚሰኝ በቀር ስሚም ተቀባይም የለውም።

በተለይም በቃል የሚነገረው ታሪክ ዐይን ያወጣ ውሸት ለመሆኑ ምስክር አያሻውም፤ የታሪኩ አቀነባባሪዎች ግን ታሪኩን በዐላማ እንደ ፈጠሩት ፈጽሞ ልንዘነጋው አይገባም። ምክንያቱም በፈቃዳቸው በተለያዩ



ስሞች ታቦታትን አባዝተውና አራብተው ሕዝባችን እንዲቀበላቸው ለማድረግ የፈጠራው ታሪክ መንገድ ጠራጊ ሆኖ አገልግሏቸዋል።

በቤተ ክርስቲያናችን፥ በኦሪት ዘመን በእግዚአብሔር ስም ብቻ የተጠራውን ታቦት «ታቦት ጽዮን» ብሎ መጥራት የተለመደ ነገር ሆኗል። ታቦቱ በጽዮን ከተማ ያለ ታቦት መሆኑን ለመግለጽ ታስቦ የተሰጠው ስያሜ ከሆነ ከእውነታው ብዙም የሸሸን አንሆንም። ጉዳዩ ግን ሌላ ነው፤ እንዲህ ብሎ መጥራት ቀስ በቀስ ጽዮን፥ «ማርያም» ስለሆነች ታቦተ ጽዮን የማርያም ታቦት ነው ወደሚል ድምዳሜ አምጥቶናል። መቼም ቅድስት ድንግል ማርያም ባልኖረችበት ዘመን ለእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ስም የተሰጠውን ታቦት የማርያም ታቦት ነው በማለት ጤነኛ ሰው አይናገርም። የሆነው ሆኖ ከእግዚአብሔር ላይ ተቀምቶ በማርያም ስም ታቦቱ መጠራት ከጀመረ በኋላ፥ በዚሁ ብቻ ሳይወሰን ሌሎች ሰው ሠራሽ ታቦታት በሚታወቁና በማይታወቁ ስሞች መጠራታቸው ቀጥሏል።

እንግዲህ በታቦት ስም ምን እየተሠራና ወደ የት እያመራን እንደሆነ ልናስተውል ይገባናል።

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ያልሆኑትን ሌሎቹን አብያተ ክርስቲያናት ትተን፥ ከአገራዊ ባህልና ልማድ ውጪ በአስተምህሮ ከኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትን ከተመለከትን፥ እንደ አገራችን ያለ ታቦት የሌላቸው መሆኑ የታወቀ ነው።

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ግን በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ታቦት ተለመደ ነገር መሆኑን ጽፈዋል። (የኢ/ቤ/ክ/ታሪክ ገጽ 109) ይህ ምናልባት የአሁኑ ታቦት በሌሎቹ ሳይኖር በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ብቻ እንዴት ሊኖር ቻለ? የሚል ጥያቄ እንዳይነሣ ለማድረግ ሲባል የተነገረ ይመስላል። እሳቸው «ታቦት» የሚል ስያሜ የሰጡትን ንዋየ ቅድሳት አብያተ ክርስቲያናቱ ታቦት ነው ብለው የተቀበሉበትን ማስረጃ አናገኝም። ለምሳሌ ግብጻውያን «ሉሕ» ይሉታል። እርሱም የቍርባኑን ኅብስት የሚይዘው ጻሕልና ወይኑ የሚጨመርበት ጽዋዕ የሚቀመጡበት በተለያዩ ቀለማትና በሐረግ ያጌጠ ጠረጴዛ ነው።

የተቀሩትም የግሪክ፥ የሩስያ፥ የሩማንያና የመሳሰሉት አብያተ ክርስቲያናትም፥ የጌታ ስቅለት ወይም ግንዘት የተሣለበት የነጭ ሐር መጐናጸፊያ በጠረጴዛው ላይ ይዘረጋሉ። አገልግሎቱ ከግብጾች ሉሕ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ይሁን እንጂ በኛ ዘንድ እንደሚደረገው ታቦት ብለው ቀሳውስት ተሸክመው የሚያከብሩትና ወድቀው የሚሰግዱለት አይደለም። ምናልባት እንዲህ አድርገው ቢገኙ እነርሱም ስሕተተኞች ይባላሉ እንጂ፥ ተመስግነው አድራጎታቸው እንደ ትክክለኛ ማስረጃ ሊቀርብ አይችልም።

እንግዲህ እስካሁን የአገራችን ታቦት በብዙ መንገድ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ተመልክተናል። ሰዎች ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊና ታሪካዊ ለማስመሰል፥ ከተቻላቸውም ለማድረግ የተለየዩ ዘዴዎችን

ተጠቅመዋል:: ያም ቢሆን በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ፈራሽ ነው:: ሰዎች ለዐላማቸው መሳካት ሲሉ ያቀናበሩት ታሪክ ውሸት ነው ካልን÷ ስለ አገራችን ታቦት አመጣጥና አጀማመር የሚናገር ሌላ ተአማኒነት ያለው ትውፊታዊ ታሪክ መፈለግ የግድ ሊኖርብን ነው::

ትውፊታዊው ታሪካችን እንደሚያስረዳን ታቦት ወይም ጽላት የሚባለው ሰሌዳ÷ እንደ አምላክ ተቈጥሮ ስግደትና አምልኮ ወደሚቀበልበት ደረጃ ከመሸጋገሩ በፊት÷ አንድ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ለመትከል እንደ ፈቃድ መስጫ ሰነድ በመሆን ያገለግል ነበር:: ይኸውም አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለመትከል ሲታሰብ የአካባቢው ምእመናን ለመንበረ ጵጵስናው ጥያቄ ያቀርባሉ:: መንበረ ጵጵስናውም ቤተ ክርስቲያን ሊያሟላ የሚገባውን ማንኛውንም መስፈርት÷ ማለትም: - የአገልጋዮችን ብዛትና ብቃት÷ የምእመናኑን ብዛት÷ ምእመናኑ ለቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ የሚሆኑ ወጪዎችን መሸፈን የሚችሉ መሆናቸውንና መሰል ጉዳዮችን ካጣራ በኋላ÷ መስፈርቱን አሟልቶ ቢገኝ ፈቃድ ይሰጣል:: እንደ ፈቃድ ማስረጃ ይሰጥ የነበረውም ከዕንጨት ወይም ከድንጋይ የተሠራ ዛሬ ታቦት ወይም ጽላት ተብሎ የሚጠራው ሰሌዳ ነበር::

በሰሌዳው ላይ የሚጻፈውም : -

በ1ኛው ገጽ ላይ አህያ ሼር አህያ÷ («አህያ» የሚለው ስም ላልቶ ይነበብ) ኤልሻዳይ÷ አዶናይ÷ ጸባዖት የተባሉና በብሉይ ኪዳን የተገለጹት ሦስት መለኮታዊ ስሞችና÷ በተጨማሪም አልፋ ኦሜጋ (አልፋ ወዖ) የተባሉ ሁለት የዐዲስ ኪዳን ስሞች÷ እንዲሁም የውጣ ወይም የኢየሱስ ክርስቶስ የስሙ መጀመሪያ በግሪክ ፊደል ይጻፋል::

በ2ኛው ገጽ ላይ ደግሞ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ስም÷ የፈቃጁ ጳጳስ ስም÷ በዘመኑ የነበረው ንጉሥ ስም÷ አንዳንድ ጊዜም የዕጨጌው÷ የቤተ ክርስቲያኑ ገበዝና የክፍሉ ምስለኔም ታክለው ይጻፍ ነበር፤ (ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ቍ. 15 ገጽ 16)::

ምናልባት ቀደም ብለው በተተከሉት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በዚህ መልክ የተሠሩትን የቀድሞዎቹን ታቦታት እናገኝ ይሆናል እንጂ÷ በአሁኑ ሰዓት የቀድሞውን የታቦት ይዘት አናገኝም:: አሠራሩ ሁሉ ተለውጧል:: ዛሬ እንዲያውም በሐረግና በመስቀል ቅርጽ ብቻ ያጌጠ ታቦት መቀረጽ መጀመሩን እንረዳለን:: የተከበሩ አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ «የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል» በተሰኘው መጽሐፋቸው ገጽ 56 ላይ በዚህ ዘመን ያለውን የታቦት (የጽላት) አቀራረጽ ሁኔታ በተመለከተ÷ በቅርቡ ከቁሉ ዲምቱ የተገኘውን ጽላት ፎቶ ግራፍ አውጥተውታል:: አንባቢ እንዲያገናዝበው በማሰብ በዚህ መጽሐፍ ላይ ያው ፎቶ ግራፍ እንዲወጣ ተደርጓል:: ከዚህም በተጨማሪ የብሉይ ኪዳን ታቦት አሠራሩ ምን ዐይነት እንደነበረ የሚያሳየው ሥዕል ለንጽጽር ቀርቧል::

የአገራችን ታቦት በምን ዐላማ ተጀምሮ በዘመናት ጉዞ ውስጥ የአገልግሎቱን ዐላማና አቅጣጫ በመሳት÷ ዛሬ እንደ ቀድሞው የእግዚአብሔር ታቦት መቈጠርና ወደ መመለክ እንደ ተሸጋገረ እናስተውል!





በዚህ ፡ ዘመን ፡ ያለውን ፡ የታቦት ፡ ጽላት ፡ አቀራረጽ ፡ ይህ ፡ ሥዕል ፡ ያመለክ ታል ፡ (ከቁሉ ፡ ዲምቱ ፡ በቅርቡ ፡ የተገኘ ፡)